# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ
# የአንኮበርና የይፋት ትግል

አንኮበር፣ በታጁራ የባህር በር ወደ ማህል አገር ለሚያደርሰው መንገድ መገናኛ ስለነበረች፤ ከዚህም በላይ ለሸዋ ነገሥታት መናገሻ ስለነበረች፣ ከኢጣሊያኖች ዘንድ የታወቀችና ትኩረት የተደረገባት ከተማ ነበረች። ከዚህም የተነሣ አባ ማሣያ የተባለ ጣልያናዊ ቄስ በሀገሩ ሕዝብ ዘንድ ስሙን አባ ማስያስ አሰኝቶ ቀደም ብሎ ጥናት አካሄደ፣ የካቶሊክንም እምነት መሠረተ። መቀመጫውንም መጀመሪያ ልጥ ማሪፊያ፣ በኋላ ደግሞ ፍቅሬ ግንብ አደረገ። ይህንን ቄስ በመከተል እየገቡ ሌሎች ጣልያኖች ልዩ ልዩ የፖለቲካ ጥናት እያጠኑ ወደ ሀገራቸው ላኩ።[1]

የጣልያን መንግሥት በእነዚህ ጥናቶችና በሌሎችም በየጊዜው በሰበሰባቸው መረጃዎች እየታገዘ በ1928 ዓ.ም ወረራው ጊዜ ይህቺን ከተማ ለመያዝ ተፋጠነ። ከደብረ ብርሃን በስተምሥራቅ ያለውን አገር ለመያዝና በአንኮበር በታች ያለውን በረሃ ለመቆጣጠር፣ የአንኮበር መያዝ ለኢጣልያኖች ወሣኝ ሆኖ ተገኘ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ያሠራውና ጠላትም ተከትሎ የገባበት የመኪና መንገድ ይፋትን ከመንዝ ቆረጠው። ስለዚህ የይፋት ሕዝብ ትግሉን ከአንኮበር ጋር እንዲሆን አደረገ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውም በዚህ ዓይነት ነው።

የጠላት ጦር በኢትዮጵያ ሕዝብ ጉልበት በተሠራለት የመኪና መንገድ ሹማምንት በመኪናና በአውቶሞቢል፣ ካድሬዎች በሞተር ሳይክል፣ ሠራዊቱ በእግር ወደ ደብረ ብርሃን ይተማል። የይፋት አርበኞች ሁኔታውን በቁጭት ይመለከታሉ። እርስበርሳቸው እየተመራረጡ ይሿሿማሉ፤ ለሀገራቸው ነፃነት ለመሞት ይማማላሉ።

የአንኮበርና የይፋት ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ፣ የይፋት አርበኞች ግንቦት 2 ቀን 1928 ዓ.ም አንፆኪያ በተባለው ሥፍራ በጣልያኖች ላይ አደጋ ጥለው ብዙ የጣልያን የጦር መኰንንኖች ፈጁ። ሕዝቡ በዱላ ጭምር እየደበደበ ፈጃቸው። በዚህ ቀን ተኩሱን የከፈቱት አቶ ሞገስ ስሜና ባላምባራስ ሠይፉ መሆናቸው በታሪክ ተመዝግቦአል። የዕለቱ ጀግኖች መሆናቸው በሥርዓት ተረጋግጦላቸው የተቀቡት አቶ ገብረሕይወት ወልደ አማኑኤልና አቶ ማሞ አበበ ሆኑ። ረጅሙና መራራው የሸዋ የአርበኝነት ትግል በእንዲህ ተጀመረ።

ከጠላት ደም ተቃብቶ መዝናናት የለምና የይፋት ሕዝብ በዚያው ሌሊት ከየቤቱ ወጥቶ በሮቢ አካባቢ ከመንገዱ ግራና ቀኝ አንጥፎ ጠበቀ። የጠላት ወታደር ከካሚዮን እየተሣፈረ ወደ አዲስ አበባ ይገሰግሳል። ሰባ አምስት ካሚዮን ከደፈጣው ቦታ እንደገባ አርበኛው ተኩስ ከፈተ። ሁሉም በየግንባሩ ባለው ካሚዎን ተሳፍረው የነበሩትን የጣልያን ወታደሮች በጥይት



ጠዘጠዛቸው። አደጋ የተጣለባቸው በድንገት በመሆኑ የጠላት ወታደሮች ብዙም አልተፈናፈኑም አለቁ። ከሀዲም አልጠፋ። ዘውዴ ሙላት የተባለ ሰው አሥራ ሁለት ጣልያኖችን፣ አሥራ አንድ ቀን ሙሉ ደብቆ አካባቢው ሲረጋጋ ለወገኖቻቸው አስረክቦ ተሸለመባቸው።[2]

በጠላት ላይ ከባድ ችግር ከፈጠሩበት ጉዳዮች አንዱ ወደ ማህል አገር የሚጓዝበትን ይህንን መንገድ መጠበቅ ሆነ። ይህ መንገድ ከተዘጋ ወደ ማህል አገር ወታደር ለማስገባት፣ ለገባውም ስንቅና መሣሪያ ለማቅረብ አለመቻሉ በግልጽ ታወቀው። ብዛት ያላቸው አይሮፕላኖች እያስነሳ አካባቢውን በቦምብ ደበደበ። ለማስፈራራት ጭምር ብሎ መርዝ ረጨበት። ከግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ በዚያ አካባቢ ያለውን ኃይል አጠናከረ።[3]

ይህ ሁኔታ አርበኛውን አላስደነገጠውም። ይህንን መንገድ መቆጣጠር፣ ጠቅላላውን የጠላት ወረራ መግታት መሆኑን ስለተረዳ ትግሉን በይበልጥ አጠናከረ። ከግንቦት 10 እስከ 12 ቀን 1928 ዓ.ም በዚሁ ቦታ ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት፤ ጉዞውንም አገዱት።

የይፋት አርበኛ ሲያይልበት፣ ጠላት ከደብረ ብርሃን አንድ ባታሊዎን ጦር ወደ አንኮበር ላከ። ከይፋት እስከ ቡልጋ የተቀጣጠለውን እንቅስቃሴ ሽንጥ ለመቁረጥ፣ ጦሩ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ። የአንኮበር ጀግኖች እነባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ በጀግንነት ተከላከሉ። ነገር ግን ከተማይቱን ማዳን አልተቻላቸውም። ብዙዎች ጠላታቸውን እየጨፈጨፉ ወደቁ። ጠላት ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም የጎረቤላን ከተማ ያዘ።

አርበኞች በዙሪያው ባሉት ተራሮች ተሰማርተው ከደረሰባቸው ጉዳት ጥቂት ከአንሠራሩ በኋላ ሰኔ 3 ቀን፣ ከዚያም ሰኔ 20 ቀን ጀምረው ለአምስት ቀን ያለማቋረጥ ወጉት። አዝማች ሆኖ የመጣውን ጣልያናዊ ሻለቃ ገደሉት። ቢሆንም ጎረቤላን ማስለቀቅ አልቻሉም። ጠላትም ፈጥኖ ምሽግ ስለሠራ፣ ትንቅንቁ ጉዳት እንጂ ጥቅም የማይሰጥ ሆነ። አርበኞች ኰሎኔሉን ገድለው የመሳሪያና የስንቅ መጫኛ የነበሩትን አጋሰሶቹን ፈጁበት። አርበኞቹን ለማጥፋትና በሕዝብም ዘንድ ለማስጠላት፣ ጣልያን አካባቢውን በቦምብ ደበደበ። ።

የጐረቤላ መለቀቅ ለአርበኞቹ አስፈላጊ ሆነ። ስለዚህ እንደገና ለማጥቃት ተዘጋጁ። ሐምሌ 12 እና 13 ቀን 1928 ዓ.ም ልጅ አየለ ኃይሌ በጐረቤላ ምሽግ ላይ፣ ልጅ /ደጃዝማች/ ደስታ ሸዋርካብህ በጥዬ፣ ባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ በቆብ አስጥል ሆነው ሦስተኛ ዙር ጥቃት አካሄዱ። ጠላት አልተበገረም። እንዲያውም ብዙ ሰው ገደለባቸው። በባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ከሚመራው ቡድን ብቻ ስድሣ ሰው ወደቀ። ጠላት ሌላ ድጋፍ ሰጭ ጦር በጄነራል ትራኪያ መሪነት ከደብረ ብርሃን ወደ ጐረቤላ ማንቀሳቀሱ ተሰማ።

አርበኞች የጦር ሥልት ቀየሱ። አዲስ የሚመጣውን የጠላት ጦር በመንገድ ላይ እንደ አለ ለማጥቃት አሰቡ። በፍጥነት ተንቀሳቅሰው ወሎ ፋርዳ የተባለውን ጉራ ይዘው ጠበቁት። ጄነራል ትራኪያ አርበኞቹን መቋቋም እንደማይችል አውቆ ከሐር አምባ ወደ ደብረ ብርሃን በመመለስ የአየር ድብደባውን አጠናከረ። ጉረቤላን ለማስለቀቅ በአርበኞች በኩል የተደረገው ሙከራ በዚህ አበቃ። ባላምባራስ ይልማ ወደ ቡልጋ፣ በረከት ዞሩ።

በይፋት አርበኛውን በማስተባበር ይመሩ የነበሩት ባሻ /ደጃዝማች ተሰማ እርገጤ ቆስለው ነበርና ጣልያን ይህንን ሰምቶ ሐምሌ 12 ቀን 192 ዓ.ም በተኙበት፣ ወይራ አምባ በተባለው ቦታ ከበባ አደረገ። ብዙ አርበኞችን ገደለ፣ አቆሰለ። ነገር ግን አርበኞቹ በርትተው ስለተዋጉ፣ ቁስለኛውን እንኳ ለማዳን ሳይችል ወደ መጣበት ተመለሰ።

የደብረ ሲናና የአካባቢው አዛዥ የነበረው ሻምበል ጳጉሜ 2 ቀን 192 ዓ.ም ጦር አንቀሳቀሰ። ገሚሱን ወደ መንዝ፣ ሌላውን ገሚስ ወደ ይፋት አሠማራው። ወታደሩም ሕዝብ መጨረስ፣ ቤት ማቃጠል ያዘ። ይህንን ሀገር የማጥፋትና ሕዝብ የመፍጀት እርምጃ ለመግታት አርበኞች ተረባረቡ፤ በነጭዋ አምባ የወረደውን መንዞች፣ በገደልጌ የመጣውን ይፋቶች ደረቅ ለደረት ገጠሙት።

በዚህ ጦርነት ያስቸገረው የጠላት ጦር ብቻ አልነበረም፤ የባንዳው ጥርቅም አስቸግሮ ነበር። በባሻ /ደጃዝማች/ ተሰማ እርገጤ የሚመራው ቡድ የአቡነ አረጋዊን ነጋሪት ከአደባባይ አውጥቶ እያስጐሸመ አዋጅ ነገረ። አዋጁም "...ተው ያገር ልጅ እንዴት እናት ሀገርህን ትዋጋለህ? ሃይማኖትህንስ ለም ታፈርሳለህ?" ብሎ የሚጠይቅና ንጉሠ ነገሥቱ መምጣታቸውን የሚገል ደብዳቤ መድረሱን የሚያበስር ነበር። ደብዳቤው እዚያው በአርበኞቹ የተዘጋ እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም። በዚህ አዋጅ ልባቸው የተነካ ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ባንዶች ከጠላት ወደ አርበኞች ዞረው ትግላቸውን ቀጠሉ።

ጦርነቱ በማግሥቱ ጳጉሜ 3 እና 4 ቀን 1928 ዓ.ም ቀጠለ መላቅጡ ጠፋ፤ ጣልያን በአይሮፕላን ቢቀጠቅጥም፣ ውጤት አላገኘም የጣልያንን የጦር አዛዥ ሲለፈልፍ አርበኞቹ በአፉ ጥይት ስለከተቱበት ፀ አለ። አቶ መኩሪያ የጣልያኑን ባንዲራ በጉራዴ ቆርጦ በማምጣት ሰለባ ጣለ ከሦስት ቀን ጦርነት በኋላ ጣልያን ስለተሸነፈ፣ የተንቀሳቀሰበትን ዓላማ ት ወደ ደብረ ሲና ተመለሰ። ከጠላት ወገን እጅግ ብዙ ሠራዊት አለቀ ከአርበኞችም ብዙ ጀግና ወደቀ።

የ1928 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1929 ዓ.ምቱ ቀጠለ የጣልያን ጦር ግፋይታ በተባለው አካባቢ የነበረውን አርበኛ ለማጥቃ ተንቀሳቀሰ። እንደ ተራ ሽፍታ በመቁጠር ጠላት እምብዛም ባለመጠንቀቁ በሽምቅ ጠብቆ ግንባር ለግንባር በመግጠም አነከተው። የጠላት ጦር እየሮ



ከደብረ ሲና ምሽግ ሲገባ፣ አርበኛው እየገሰገሰ አብሮ ከምሽጉ ውስጥ በመግባት ጋርቺሊ የተባለውን ምሽግ አስለቀቀው። በዛውም ምሽጉን ዘረፈ።

በብዙ ሺህ የሚቆጠር አዲስ ጦር ሮቤ ገባ። የተጣላ ታራርቆ፣ አርበኛው ለፍልሚያ ተዘጋጀ። ለማስረጃም ያህል መራራ ጥል ተጣልተው ለመጋደል ይፈላለጉ የነበሩት አቶ ሰብስቤ የተባሉ ሽማግሌና በላይነህ ይፍሩ የተባለ ሰው "...ስለምን ከቂም እንሞታለን" ተባብለው ታረቁ። በልጅ በላይነህ ይፍሩ የጉበዝ እልቅና ጠላታቸውን መስከረም 16 ቀን 1929 ዓ.ም እንጭኔ ከተባለው ቦታ ገጥመው ብዙ ጉዳት አደረሱበት።

ጠላት በያለበት ሰላይ አስቀምጦ ነበርና ከእነዚህ ሰላዮች አንዱ ጉዝ አምባ ከተባለ ቦታ አርበኞች እንደሚወጉት ነገረው። ጣልያን ይህቺን በር ለመያዝ ከሌሊቱ በአሥር ሰዓት ተንቀሳቅሶ በአሥራ አንድ ሰዓት ተኩስ ከፈተ። ይፋት በሞላ ተነቃነቀ። ሰንቄ አምባ፣ ከራባ፣ ወይራ አምባ፣ ገፋይታ፣ ወጀ ከተባሉት ቦታዎች ወጋው። ጣልያን መሸሽ ያልቻለውን ሴት፣ ሽማግሌና ሕፃን ፈጀ። በቤት እያጐረም አቃጠላቸው። በዚህ ውጊያ ሁለቱም ወገን ስለደከመ፣ ተኩስ አቁመው ከመስከረም 15 ቀን ጀምሮ ሲሞት የሰነበተውን ሰው ሬሣ ቀበሩ።

ጣልያን ለጦርነቱ ሕዝብ ማስተባበር ያዘ። በዚህ ጉዳይ የሚረዱት ለአንኮበር አስተዳዳሪ ረዳት ሆነው በጠላት የተሾሙት ደጃዝማች ደምስሰው ነበሩ። ለጠላት ይህ ሥራ በመጠኑ ተቃናለት። ከበረከት እስከ ጨኖ ያለውን፤ በተለይም በፊታውራሪ አቡ ሳሊሰህ ባላባትነት ውስጥ የነበረውን የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ነዋሪ፣ እንዲሁም ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖትን ጭምር አስተባበረ። በጄነራል ትራኪያ መሪነት ከደብረ ብርሃን ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም መከቱ። ታህሣሥ 19 እና 20 ቀን 1929 ዓ.ም ውቲ በተባለው ቦታ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ ሰው ከማስጨረስ በስተቀር ሌላ ውጤት አለማስገኘቱን በመረዳት፣ አርበኞች ቦታውን ለቅቀው ጥር 1 ቀን ወደ ተጉለት ዞሩ።

ቡልጋ፣ በረከት ታህሣሥ 28 እና 29 ቀን 1929 ዓ.ም ስለተካሄደው ጦርነትና ስለ እነ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ መያዝ ቀደም በዬ ገልጫለሁ። በዚህ የአርበኞች ቡድን ውስጥ የአንኮበር ከተማን በጠላት ላለማስያዝ በጀግንነት ተዋግቶ ብዙ ሰው ከአለቀበት በኋላ ወደ ቡልጋ የዞረ ሠራዊት ነበረበት። የሚመራውም በባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ነበር። ይህ ቡድን ከተማረከ በኋላ በደብረ ብርሃን ዞሮ ጥር 10 ቀን 1929 ዓ.ም አንኮበር ገባ። ይህ ሁኔታ ለጣልያን ታላቅ ዕድል ሆነለት። ተይዘው የመጡትን አርበኞች በሙሉ ጥር 11 ቀን 1929 ዓ.ም፣ የጥምቀትን በዓል ለማክበር ሕዝብ ከተሰበሰበበት በአደባባይ፣ በመትረየስ ረሸናቸው። ይህ ድርጊት ለአንኮበር ሕዝብ የማይረሳ ትምህርት ሰጠው።

ጣልያን በአንድ ወገን ጦር እያቀረበ፣ በሌላ ወገን ወደ እሱ እንዲገቡለት ያባብል ጀመር። አርበኞቹ ግን አልተታለሉለትም። ተዘጋጅተው በር፣ በር ይዘው ጠበቁት። እሱም በአንድ ጀነራል የሚመራ የሶማሌ ጦር በደብረ ሲና፣ አንድ ባታሊዮን በቡሎፋርዳ፣ ሌላ ባታሊዮን በጐበር፣ አንድ ባታሊዮን በቁንዲ፣ ከደብረ ብርሃን ደግሞ በጀነራል ማሊቲ የሚመራ ጦር አመጣ። አርበኞቹ በየበሩ በጥይት ጠዘጠዙት። በቡሎፋርዳ በኩል የመጣውን ድል አድርገው አባረሩት። ነገር ግን ከደብረ ሲና የመጣው የሶማሌው ጦር አርበኞቹን ድል አደረጋቸው። ይህንን ሲሰማ ሸሽቶ ደብረ ብርሃን የገባው ጀነራል ማሊቲ እንደገና ተመልሶ በግስጋሴ ደረሰ። አርበኞቹም እንደ መጋቢት 7 ቀን 1929 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥመው በመውጋት ድል አደረጉት። ኮሎኔሉንና አንድ መቶ አለቃ ከብዙ ወታደር ጋር ገደሉበት። አሥራ ሁለት መትረየስና ከአምስት መቶ የሚበልጥ ጠመንጃ ከእነ ጥይቱ ማረኩበት። ቀደም ብሎ አቶ ሸንቁጤ ወልደማርያምና አባ ረታ የተባሉትን አርበኞች ራስ ቆርጦ ተጫውቶበት ነበርና፤ የመቶ አለቃውን ጭንቅላት ቆርጠው ጊጤ ተጫወቱበት።

ጠላት በይፋት በኩል ሌላ ጦር አመጣ። አርበኞቹም በመላላት ተሰባስበው ሚያዝያ 15 ቀን 1929 ዓ.ም አጋም በር በተባለው ቦታ ገጥመው በመውጋት ወደ መጣበት መለሱት።

ከዚህ በኋላ የጠላት የማጥቃት ሥራ ለጥቂት ጊዜ ታገሰ። በ1929 ዓ.ም የክረምት ወራት የቡልጋው አርበኛ ያልተጠበቀ ጥንካሬ ስለአሳየና ባላምባራስ /ራስ/ አበበም ወደዚያው ስለዞሩ፣ የጠላት የማጥቃት ኃይል ወደዚያ አዘነበለ። ቢሆንም የይፋት አርበኛ ሥራ አልፈታም። ጠላትን በየቦታው ማስጨነቁንና ሲቻለው ማጥቃቱን ቀጠለ።

ጠላት አሥራ ሁለት ባታሊዮን ጦር አሰማርቶ የቡልጋን አርበኞች በሚወጋበት ጊዜ፣ የይፋት አርበኞች የበኩላቸውን ጥቃት በጠላት ላይ አካሄዱ። ግንቦት 11 ቀን 1930 ዓ.ም በድንገት በርዬ ከተባለው ቦታ ደርሰው ጠላት ወደ ቡልጋ ሊልክ አዘጋጅቶት የነበረውን ጦር መቱት። የቡልጋ ጉዞውንም አሰናከሉበት።

አርበኞች ወደ ባሶ ሄደው በርዮ በተባለው ምሽግ ላይ አደጋ መጣላቸውን ሲሰማ፤ ጣልያን አካባቢው ነፃ እንደሆነ ቆጥሮ ከአንኮበር ምሽግ በመውጣት ሕዝብ መፍጀትና ከብት መዝረፍ ያዘ። አርበኞቹ ይህንን እንደ ሰሙ ገስግሰው በመድረስ፣ ግንቦት 12 ቀን 1930 ዓ.ም ወግተው ድል በማድረግ እስከ ምሽጉ ድረስ አባረሩት። ዘርፎ በአንድ ቦታ አጉሮአቸው የነበሩትንም ከአምስት መቶ የሚበልጡ የቀንድ ከብቶች ለገበሬዎቹ ተመለሰላቸው።

አርበኞቹ ሰፍረውበት የነበረውን ሐር አምባ የተባለውን ቦታ ለማስለቀቅ ፈልጎ ጠላት ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም እንቅስቃሴውን ቀደም



አድርገው አጢነውት ነበርና፣ ሰኔ 22 ቀን 1930 ዓ.ም ወ/ሮ አትላ አባ ዘማርያም አገር ገጥመው ተዋጉት። ጦርነቱም ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ቆየ። ጣልያንን ድል አድርገው በማባረር፣ ለቁጥር የታከተ ቦምብና ጥይት ማረኩበት።

ኰሎኔል እሩሶ በሚባል አዛዥ የሚመራ ሌላ አራት ባታሊዮን ጦር መጣ። አርበኞችም ሰኔ 26 ቀን 1930 ዓ.ም ተዋጉት። ነገር ግን ሊመልሱት አልቻሉም። ስለዚህ አካባቢውን ተቆጣጠረ። አንድ ባታሊዮን ቁንዲ፣ አንድ ሌላ ባታሊዮን ውቲ ላይ ምሽግ አስመሽጐ አስቀመጠ። በዚህ አድራጐቱ የልብ ልብ ስለተሰማው "ግቡ! ያለዚያ ልታልቁ ነው" እያለ የማስፈራሪያ ወረቀት በተነ። የማባበያ ደብዳቤዎች ለአርበኞች መሪዎች ፃፈ። አርበኞችም ጊዜ ለማግኘት ሲሉ "እሺ እንገባለን" አሉት። በይፋትና በቡልጋ፣ በመንዝና በተጉለት ያሉ ጓደኞች ይዘው ለመግባት ረዘም ያለ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠየቁት። እሱም እውነት መስሎት ተስማማ፤ እነሱ ግን ሥራቸውን ቀጠሉ።

ውትወታው እንዳልያዘለት በተረዳ ጊዜ ጉጉፍና ዘምቦ የሚባሉትን አምባዎች ለመያዝ ሞከረ። ከውቲ ጦር አንቀሳቀሰ። ቁንዲና ውቲ የተባሉት ቁልፍ ቦታዎች የተያዙባቸው አርበኞች ነሐሴ 10 ቀን 1930 ዓ.ም አደጋ ጥለው አሣሩን አሳዩት። እሱም ተመልሶ ወደ ምሽጉ ገባ።

ጣልያን አካባቢውን ከቁጥጥሩ ሥር ለማስገባት የነበረው ፍላጐት ጠንካራ ነበርና እመ ምህረት የተባለውን ቦታ ለመያዝ ከቁንዲ ሌላ ጦር አንቀሳቀሰ። እሱንም ደግሞ አርበኞቹ ነሐሴ 15 ቀን 1930 ዓ.ም ወግተው ወደ መጣበት መለሱበት። ሁለቱም ሙከራዎቹ ሲከሽፉበት ጣልያን አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበው። ድብደባው አርበኞቹን ያደከመለት መስሎት አንድ ባታሊዮን ጦር አምጥቶ እመ ምህረት ላይ አሠፈረ። ለአርበኞች ይህቺ ቦታ አስፈላጊ ነበረችና ነሐሴ 18 ቀን 1930 ዓ.ም ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ገጥመው በመውጋት አባረሩት። እሱም ቀድሞ ከነበረበት ከቁንዲ ምሽግ ሸሽቶ ገባ።

በእነዚህ ጦርነቶች መሳካት አርበኛው ልቡ ደነደነ። አዳዲስ ምሽግ እንዳይመሽግ መከላከል ብቻ ሳይሆን፣ የያዘውንም ምሽግ የማስለቀቅ ሙከራ ተጀመረ። እሱም ታረቁ በከንቱ አትለቁ እያለ ስብከቱን አፈራረቀ። የአርበኞቹ መልስ አይለወጥም። ሠራዊታቸው ብዙ እንደሆነና የሚዋጋውም በያለበት እንደሆነ፤ ለመመላለስና ለመመካከር ረጅም ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው፤ ከጓደኞቻቸው ተነጥለው ብቻቸውን መታረቅ እንደማይችሉ የሚገልፁ ነበሩ። እሱም እውነት እየመሰለው መጓጓቱ አልቀረም። ነገር ግን አርበኞች ከዓላማቸው ፈቀቅ አላሉም። የወሎ ፈርዳን ለማስለቀቅ ከነሐሴ 28 እስከ 30 ቀን 1930 ዓ.ም ታላቅ ውጊያ አካሄዱ። ጣልያን በዚሁ ጊዜ በስድስት ምሽጐች ላይ ጦርነት እያካሄደ እንደነበር ይታወሳል። እሱም በእግር ጦር ሲያቅቱት፣ አይሮፕላን እያስመጣ አስደበደባቸው፨

ጠላት ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይን ለማጥፋት ያካሄደውን ጦርነት፣ እንደምን ወደ አንኮበር እየተጠጋ እንደሄደ፤ ምንም በሕመም ምክንያት ቢሆን እሳቸውም የሞቱት በዚያው አቅራቢያ እንደ ነበርና የተቀበሩትም ሐርአምባ እንደነበር ቀደም ብለን ተመልክተናል። ይህ ሁኔታ በይፋት አርበኞች ላይ የጠላትን ተፅዕኖ እንደ አበዛባቸው የታወቀ ነው። እነሱም በብርታት ተከላከሉ። ለራሳቸው ከመከላከልም አልፈው ወደ ፍቅሬ ግንብ የተጠጉትን የቡልጋ አርበኞች ደገፉ።

ጣልያን በርካታ ጦር አምጥቶ አካባቢውን አሰሰው አስቀጠቀጠው። በየቀኑ አይሮፕላን እያስመጣ በቦምብ አስደበደበው። ውጊያው ከመስከረም 25 እስ 30 ቀን 1931 ዓ.ም በየቦታው በፍቅሬ ግንብ፣ በለውቲ፣ በአይብስ፣ በቁንዲ፣ በሐር አምባ፣ በቆቦ፣ በእመ ምህረት፣ በዲቤ፣ በይረፎ ተካሄደ። አርበኞች ጠላታቸውን በየቦታው ረፈረፉት፤ ከእነሱም ብዙ ሰው ወደቀባቸው። ነገር ግን ጠላት እንደ አሰበው ድምሳሴ አልደረሰባቸውም፤ ተረፉ። የቡልጋው አርበኛ ወደ ቡልጋ ሲመለስ፣ የይፋቱ በወፍ ዋሻ በኩል ጥሶ ወደ ተጉለት ተዛወረ።

ህዳር 20 ቀን 1931 ዓ.ም ዝንጀሮ ገደል ከተባለው ቦታ ጠላት ከበባ አደረገባቸው። ሙሉ ቀን ቢዋጉም፣ ሊበትኑት አልቻሉም። ስለዚህ ህዳር 21 ቀን በሙሉ ኃይል ተንቀሳቅሰው በማጥቃት ክቡን ሰብረው ወጡ። ነገር ግን የአርበኞቹ መሪና አስተባባሪ ልጅ /ደጃዝማች/ ደስታ ሽዋርካብህ ቆስለው ወደቁ። ጓዶቻቸው እሳቸውን በቃሬዛ ይዘው ሌሊቱን ወፍ ዋሻ ገቡ። ጠላትም ተከታትሉ ትንሽ ተታኩሶ ወደ ኂላው ተመለሠ። እነሱም ወደ ኂላ ሄዱ። እየተከታተለ ለማጥቃት ቢሞክርም፣ አርበኛው እየተዋጋ መለሰው።

ሌላ ጦር አዘጋጅቶ መጣ። ጠላት አርበኞችን ከሚያጠቃባቸው ሥልቶች አንዱ መሪዎቻቸው በታመሙና በቆሰሉ ጊዜ በመውጋት ነበር። በዚሁ ሥልት መሠረት በዚህ ቡድን ላይ ታህሣሥ 10 ቀን 1931 ዓ.ም ጥቃት አካሄደበት። አርበኛውም እየተከላከለ ወደ ዲቤ፣ ደጋጊ ወረደ።

ጠላት ደጋጊ ድረስ በመሄድ ታህሣሥ 28 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣለባቸው። አርበኞቹም የነበሩበትን ቦታ በመልቀቅ አደጋውን ከአሳለፉ በኂላ፤ ሲመለስ በመንገድ ላይ ጠብቀው አደጋ በመጣል ከባድ ጉዳት አደረሱበት። ብዙ የጦር መሣሪያም ማረኩበት። ከጠላት ጋር በመተባበር የወጋቸውን ባንዳም ጥር 5 ቀን ዋጋውን ከፈሉት።

ጣልያን ሌላ ጦር በማምጣት ሊያጠቃቸው ሞከረ። አርበኞች ቦታ በመለዋወጥ ከሚያዝያ 2 እስከ 15 ቀን 1931 ዓ.ም ድረስ ወጉት። እሱም የአጥቂነት ስሜት አድሮበት ነበርና ከደጋጌ እስከ ወሲል ድረስ እየተከታተለ ከወጋቸው በኂላ ከምሽጉ ገባ።

ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ.ም ጠላት አሉበት ድረስ መጥቶ አደጋ ጣለባቸው። አመጣጡ ከባድ ነበርና እየተከላከሉ ወደ አዳል በረሃ ገቡ።



አጠቃሁ ብሎ ተመልሶ ወደ ምሽጉ ሲገባ ሲጓዝ ጌታ ገደል ከሚባለው ሥርጥ ላይ አድፍጠው ጠብቀው ሰኔ 27 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። ከባድ ጉዳትም አደረሱበት።

ጌታ ገደል እስከተባለው ቦታ ድረስ መጥቶ ጠላት አርበኞችን ለማጥቃት ሞከረ። አርበኞችም ሰኔ 30 ቀን 1931 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥመው በመውጋት አባረሩት። ክረምቱ በመግባቱ ላይ ነበርና አካባቢውን ጥሎ ከመሄድ በስተቀር አማራጭ ስለአልነበረው ወደ አንኮበር ገሠገሠ።

በዚህ የጦር ግንባር በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም ጥቃቅን ግጭቶችም ቢደረጉ፣ በአርበኞች ላይ እምብዛም ጉዳት አላደረሱም። እነሱ ግን ጠላትን ማጥቃታቸው አልቀረም። ነሐሴ 30 ቀን 1931 ዓ.ም ቆቦ ተሻግረው ጳጉሜ 1 ቀን ከጠላት ጋር ተዋጉ። ጳጉሜ 2 ቀን ወደ ጌታ ገደል ተመልሰው ለአዲሱ ዘመን ትግል እየተዘጋጁ ሳለ፤ መስከረም 2 ቀን 1932 ዓ.ም እርቅ መያዙን የሚያበስር ወረቀት ከራስ አበበ ደረሳቸው። ወረቀቱ "...ስምምነት ጀምረናል። እሱ ጦር እንዳያመጣ አድርገናልና እናንተም የዚህን ስምምነት ነገር ተጠባበቁ..." የሚል ነበር። እውነትም ጣልያን በዚያ አካባቢ ጦር ሳያመጣ ቀረ። የይፋትና የአንኮበር አርበኞች ከመስከረም 2 እስከ መጋቢት 23 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ እፎይታ አገኙ። ሆኖም የእርቁ ጉዳይ እምብ ዛም ስለአልጣማቸው ከጠላት ጋር አልተቀራረቡም። በአንፃሩ ደግሞ ጠብ አልጫሩም፤ ዝም ብለው ተቀመጡ። የቆሰለው ዳነ፤ የታመመው አገገመ።

መጋቢት 5 ቀን 1932 ዓ.ም ከራስ አበበ ሌላ ደብዳቤ ደረሰ። የሚጠብቁት ነገር ነበርና ወዲያውኑ ሥራቸውን ቀጠሉ። ጣልያንን ከአሰሎ ተነስተው እስከ አልተኪ በር ወጥተው ጦርነት ገጠሙት። ድል አድርገው አበረሩት። መጋቢት 23 ቀን 1932 ዓ.ም አኩኩ አለሉ ከተባለው ቀበሌ ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር ገጥመው ከፍ ያለ ጦርነት አደረጉ። አደጋም አደረሱበት።

ከራስ አበበ ላይ ጦር ጠንክሮ ነበርና የይፋትና የአንኮበር አርበኞች እሳቸውን ለመርዳት ተንቀሳቀሱ። በዚህ ወቅት እነሱን ለማጥቃት ከወደ ጨኖ ከሚጓዝ ሌላ የጠላት ጦር ጋር በድንገት ተገናኙ። እሱ እነማን እንደሆኑ ባለማወቅ፣ እነሱ ባልተዘጋጁበት ቦታና ጊዜ በመሆኑ ሰላምታ ተሰጣጥተው ተላለፉ። የጠላት ጦር በመዘናጋት ሲሠፍር አርበኞቹ አደጋ ጥለው ውርደት አደረሱበት።

ከዚያም ወደ ወርቄ አገር ጉዞአቸውን በመቀጠል፣ ከፍ ሲል እንደተገለጣ በራስ አበበ ጓዝ ላይ መጋቢት 27 ቀን 1932 ዓ.ም የተጣለውን አደጋ ተከላከሉ። የጠላት ሐሳብ አርበኞችን ጠራርጎ ማጥፋት ነበርና መጋቢት 30 ቀን 1932 ዓ.ም ከሠፈሩበት ልብአርጌ ከሚባለው ቦታ ድረስ መጥቶ ወጋቸው። እነሱም ቦታ በመለወጥ ከአደጋው ከዳኑ በኂላ፣ ወደ ምሽጉ

ሲመለስ ከመንገድ ላይ አድፍጠው አደጋ በመጣል ብዙ መሣሪያና ጥይት ማረኩበት።

ከዚያም አርበኞች ሚያዝያ 7 ቀን 1932 ዓ.ም ሰዴ ወደሚባለው የአዳል በረሃ ወረዱ። ጠላትም እየተከታተለ ወጋቸው። ቀድሞም ውሃ ያለበትን ቦታ ያዘባቸው። ለማስለቀቅ ቢሞክሩም የማይበገር ሆነ። ሌላ ውሃ ሲፈልጉ ሌላ ጦር አጋጠማቸውና ተኩስ ከፍተው ሲዋጉ ጦርነቱ ከፊትና ከኋላ ሆነባቸው። ሥልታቸውን በመለወጥ በፍጥነት ሾልከው በመውጣት ሁለቱን የጠላት ጦር እርስ በርሱ አዋጉት። እስኪተዋወቁ ድረስ ከሁለቱም ወገን የተረፈው የጠላት ጦር ከውሃው ላይ ሠፈረ። ሠራዊቱ ውሃ ለመፈለግ ተበታተነ፤ የውሃ ጥሙን አርክቶ የሞቱትን ለመቅበር ሲሰበሰብ አሞራ በልቶአቸው አገኘ። ታላቅ ሀዘን ሆነ።

በአርበኞች ላይ ረሃብ ፀና፤ በዚህ ምክንያት በጠላት ምሽግ ላይ እየወደቁ ስንቅ መንጠቅ ግድ ሆነ። ለማጥቃት የተዘጋጀው የጠላት ጦር ራሱን መከላከል አስፈለገው። አርበኞች ሚያዝያ 14 ቀን 1932 ዓ.ም የቆቦን ምሽግ አጥቅተው ከዘረፉ በኋላ ወደ አይገብር ዞሩ። ጠላት ከዚያ ከበባ ለማድረግ ሲሞክር፣ ጋቺኔ ከተባለው ቦታ ተዋግተው ወደ አርቦዩ ሄዱ። አርቦዩ የነበረውን ወግተው ዘርፈው ወደ ጌታ ገደል፣ ከዚያም ወደ ወፍ ገደል ሄዱ። ጠላት የሚጥል የሚይዘውን፣ የሚጨብጥ የሚለቀውን አጣ። ወዲያና ወዲህ መራወጡን ቀንሶ ከምሽጉ ተሰበሰበ።

ከምሽጉ ውስጥ ተሰባስቦ መቀመጡ ደግሞ ይበልጥ ለጥቃት አጋለጠው። አርበኞች ሚያዝያ 20 ቀን 1932 ዓ.ም ካራመገን የተባለውን ምሽግ አጥቅተው በመግባት ዘረፉት። ብዙ ወታደርም ፈጁበት። ግንቦት 8 ቀን 1932 ዓ.ም ደግሞ ቆቦ ምሽግ ገብተው አተራመሱት። ድል አድርገው እዚያው ተቀመጡ።

ይህ ሁኔታ ጠላትን አስመረረው። ጥቂት መሆናቸውን ስለሚያውቅ ጨርሶአቸው ሊገላገል ፈለገና ታላቅ ጦር አዘጋጀ። ከዚያም ጋቺኔ ከተባለው ቦታ ግንቦት 15 ቀን 1932 ዓ.ም ከበባ አደረገባቸው። አርበኞች ጨነቃቸው። ሁላቸው አብረው በአንድነት በመጋፈጥ ፈንታ ከሁለት ተከፍለው ከበባውን ሠብረው ለመውጣት ሞከሩ። አልሆነላቸውም፤ እንዲያውም ብዙ ሰው አለቀባቸው። ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ሆነ። ጊዜ መውሰድ ደግሞ ትርፉ እልቂት ነበር። ስለዚህ ተፏክረው በኃይል ገቡበት፤ ጥሰውትም ወጡ። ወደ አዳል በረሃ የወረዱ መስለው፣ ቀን ሲመሽ ተመልሰው ሳንተ ከሚባለው አገር ገብተው ተቀመጡ።

ከሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ጀምሮ የሀገራቸው የፖለቲካ አቅዋም ስለተለወጠ፤ ይህ ጊዜ ለጣልያኖች ከወትሮውም የበለጠ ከባድ እንደነበር እውቅ ነው። ሌላው ቢቀር እስከ አሰብ የነበረውን በር ለራሳቸው ክፍት ማድረግ ነበረባቸው። ይህም የሚቻለው በአንኮበርና በይፋት አካባቢ



የነበሩትን፣ እንደነሱ አስተሳሰብ ሽፍቶች፣ በማጥፋት ነበር። ስለዚህ ኃይላቸውን አጠናክረው አርበኞችን ማባረርና መፍጀት ያዙ።

ሰኔ 15 ቀን 1932 ዓ.ም ጣልያን አርበኞች አሉበት ድረስ መጥቶ ወግቶ ወደ አዳል በረሃ አባረራቸው። እነሱ ግን የውሃ ችግር እንዳያጋጥማቸው የቀበናን ወንዝ ተከተሉ። እንደገና ሰኔ 30 ቀን 1932 ዓ.ም ዱቤ ላይ ወጋቸው። ድል አድርጕም ወደ አዳል አገር አባረራቸው። ምንጊዜም አርበኞችን ተተናኩሎ የማያውቀው የአዳል ሕዝብ በዚህ የጭንቅ ጊዜ በይበልጥ ተባበራቸው፡ ረዳቸው። ስለዚህ በክረምቱ ትንሽ እፎይታ አገኙ። ነገር ግን ረሃቡ ከባድ፣ የወባው ንዳድ ጠንካራ ነበር። ቢሆንም አርበኞች በመጠኑ አገገሙ። ዘመን ተለወጠ።

አርበኞች መስከረም 7 ቀን 1933 ዓ.ም የቆቦን ምሽግ መትተው ስንቅ አገኙ። ያንን እየበሉ መስከረምና ጥቅምትን አዳል በረሃ ሰነበቱ። ጥቅምት 15 ቀን 1933 ዓ.ም ላንቶ ከሚባለው ሀገር ጠላት ቢመጣም፣ እምብዛም ጉዳት አላደረሰባቸውም። ወደ ወሲል ተሻገሩ።

ጋቺኔ ዋና የፍልሚያ ቦታ ሆነች ህዳር 10 እና 16 ቀን 1933 ዓ.ም በዚች ቦታ ጦርነት ተካሄደ። በሁለቱም ጦርነት አርበኞቹ ቀናቸው። ከዚያም በኋላ አሳብረው ወደ ጀሉሌ ሄዱ።

ከዚህ በኋላ ከጠላት ጐን የቆመው የባንዳ ጦር እየተናደ ሄደ። ታህሣሥ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ሠላሣ ባንዶች ከጠላት ከድተው ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። ጠላትም የቻለውን ያህል ተፍጨረጨረ። ታህሣሥ 30 ቀን 1933 ዓ.ም ጀሉሌ ድረስ መጥቶ ወጋቸው። አርበኞችም ከበባውን ሰብረው አደሌራ ወደተባለው ቦታ ሄዱ። ከዚያም ጠላት ተከታትሎ ስለመጣ ጥር 16 ቀን 1933 ዓ.ም ሳለ ደናሬ ላይ ታላቅ ጦርነት ተካሄደ። መሸናነፍ ስለአቃታቸው ሁለቱም ወገኖች ወደ ኋላቸው አፈገፈጉ።

የካቲት 4 ቀን 1933 ዓ.ም ዲቤ ድቁሰ ላይ ጠላት ከበባ አድርጐባቸው ነበር። ከበባውን ያለብዙ ችግር ሰብረው ወጡ። መጋቢት 12 ቀን 1933 ዓ.ም ቆቦ ወሌንሶ ጠላት ድጋሚ ከበባ አድርጐ፤ ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት አንስቶ እስከ ሰባት ሰዓት ተዋግተው ከበባውን ሰብረው ወጡ። አርበኞች በብዙ ድካም ወደ ዲቤ ተሻገሩ፤ ከዚያም ወደ ቀበና። ከመካከላቸውም ስምንት ሰዎች ሞቱ፤ አምስት ቆስለው ሌሎች ሰባት ሰዎች ተማረኩባቸው። ከዚያ ቁጥሩ አነስተኛ ሠራዊት መካከል፣ ይህንን ያህል ሰው በአንድ ጊዜ መውደቁ ቀላል አልነበረም። በተለይም የተማረኩትና የቆሰሉት ዕድል መጥፎ ሆነ።[1]

የጠላት ጦር እየቀለለ ሲሄድ አርበኞች ማጥቃት ያዙ። በፍጥነት ተንቀሳቅሰው መጋቢት 17 ቀን ማጭዶ ከተባለው አገር ወጥተው ሠፈሩ። መጋቢት 27 ቀን ሳለ ጀናሞሬን፣ ከዚያም መጋቢት 28 ቀን አምባ ላይ የነበረውን የጠላት ጦር አባረሩ። ወዲያው ዕለቱኑ ዱዋይ ሜዳ የነበረውን

የጠላት ጦር አባረው ምሽጉን በመያዝ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቅለው ሠፈሩ፡፡

መጋቢት 29 ቀን 1933 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ መግባታቸውንና የኢትዮጵያ ረዳት ጦር አዲስ አበባ መድረሱን የሚያበስር ደብዳቤ ከውስጥ አርበኞች ተላከላቸው፡፡ ይህንን ሰምተው ወደ ደብረ ብርሃን ሲወጡ በለድ ላይ የጠላት ጦር ገጠማቸው፡፡ እሱን አብርረው ከዚያው ሠፍረው አደሩ፡፡ ሚያዝያ 30 ቀን 1933 ዓ.ም ደብረ ብርሃን ገቡ፡፡ ከዚያም ወደ ሰላሌ ሄዶ ንጉሠ ነገሥቱን የመቀበሉ ሥራ ቀጠለ፡፡

በዚህ ሁሉ የትንቅንቅ ዘመን በመሪዎች መካከል የመረዳዳትና የመተባበር መንፈስ እንጂ የግጭት እና የጠብ መንፈስ አልነበረም፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በይፋትና በአንኮበር የተካሄደው የአርበኝነት ሥራ የተከናወነው በአንድ አስተባባሪ ሥር በተጠቃለለ መልክ አልነበረም፡፡ ከልጅ /ደጃዝማች/ ሽዋርካብህ በስተቀር ወደ ንጉሠ ነገሥት መልእክ ፀሐይ እያሱ የቀረበ የለም፡፡ ይህ ሁኔታ የሰጠውም ጥቅም ያስከተለውም ችግር ነበር፡፡ ጥቅሙ፡- ሁሉም በፍላጐቱና በአቅሙ መጠን መሥራቱ ሲሆን፤ ጉዳቱ፡- ከህብረት ሊገኝ የሚችለውን ጥንካሬ መቀነሱ ነው፡፡


## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባላሽኝ ዘመን*፣ ገጽ 27-31፡፡
2. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 271-272፡፡
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 151፡፡




# ምዕራፍ ሠላሣ
# የመንዝና ተጉለት ተጋድሎ

በሸዋ ዋናው የትግል ጉራ መንዝ ነበር፡፡ ተጉለትም በጥሩ ሁኔታ ተጋድሎአል፡፡ የአካባቢው ታዋቂ ሰዎች ከማይጨው ጦርነት እንደተመለሱ፤ ሕዝቡን በማስተባበር የጠላትን አመጣጥና የመከላከያውን ዘዴ ማስተማር ጀመሩ፡፡ በክብረ በዓል ቀን ታቦት እያቆሙ፣ በዕለተ ሰንበት መስቀልና ሥዕለ ማርያም እያቆሙ ተማፀኑ፡፡ ሀገር እንዳትጠፋ፣ ሕዝብ እንዳይዋረድ፣ ኃይማኖት እንዳይረክስ ለመኑ፡፡ በዚህ ጉዳይ ታላቁን ሚና የተጫወቱት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አልፈዋቸው የሄዱት ደጃዝማች አበበ አውራሪስ ነበሩ፡፡ የልጅ ግዛቸው ኃይሌ ቅልቅልም፣ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጐአል፡፡

ሕዝቡ ተባበራቸው፡፡ ጀግኖች ለሀገራቸው፣ ለወገናቸውና ለኃይማኖታቸው ደማቸውን ለማፍሰስ ተነሱ፡፡ አንዱ ችግር ለሚሰበሰበው አርበኛ ምግብ የማግኘት ጉዳይ ሆነ፡፡ ቀድሞ ለዘማቹ ተዘጋጅቶ አማካይ በሆነ ቦታ እንዲከማች ተደርጐ የነበረው ለሠራዊቱ ተሰጠ፡፡ ከዚያም በላይ ሰው እንደፍላጐትና ችሎታው እንዲያዋጣ ተደረገ፡፡ የተደረገውም አስተዋጽኦ ከስንቅ ተርፎ ለመሣሪያና ትጥቅ መግዣ ጭምር አገልግሎአል፡፡ ግና ተባባሪና ደጋፊ የመገኘቱን ያህል፣ ከሐዲም አልጠፋም፡፡ እሱንም በታሪኩ ሂደት ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

የመጀመሪያው ግጭት የተነሣው ጠጅ ሣር፣ ግንቦት 28 ቀን 1928 ዓ.ም ነበር፡፡ ለጠላት የቆመ ባንዳ እየተኈጐደጐደ መጣ፡፡ ሐሳቡ በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመራውን አርበኛ ለማጥቃት ነበር፡፡ ሁኔታው እንደታወቀ በአርበኞች በኩል አስፈላጊው ጥንቃቄ ተደረገ፡፡ ይህ ጉዳይ በህዝቡ መካከል የርስበርስ መቃቃር የሚያስከትል ስለነበር፣ ደም እንዳይፈስስ በአርበኞቹ በኩል ጥረት ተደረገ፡፡ ሆኖም ከአጥቂዎቹ ወገን ተኩስ ስለተከፈተ፣ ጥረቱ ውጤት ሳያገኝ ቀረ፡፡ አርበኞቹ በወሰዱት እርምጃ፣ ባንዶቹ አለቁ፡፡ በዚህ ዓይነት አምስት ዓመት የፈጀው ትግል በርስበርስ ግጭት ተጀመረ፡፡

የ1928 ዓ.ም ክረምት ለመንዝና ለተጉለት አርበኞች የመዘጋጃና የመመካከሪያ ጊዜ ሆነ፡፡ የአርበኞቹን ሁኔታ ይከታተል የነበረው ጣልያንም ለማጥቃት ተዘጋጀ፡፡ ቀኛዝማች አጐናፍር የተባለውን ባንዳ ፊታውራሪ ብሎ መሪ እንዲሆንለት አደረገ፡፡ ሐሳቡ ሰላድንጋይን ለመያዝ ነበር፡፡ ይህ እንደታወቀ፣ መንዝ ተንቀሳቀሰ፤ ተጉለት ደገፈ፤ ይፋት ተባበረ፡፡ ከሦስቱም አካባቢ የመጣው ጀግና ጳጉሜ 3 ቀን 1928 ዓ.ም የጠላትን ጦር ጣርማ በር ላይ ግንባር ለግንባር ገጠመው፡፡ በጥይት አርጩሜ ሸነቆጠው፡፡ ጣልያን በመድፍና በመትረየስ ቢከላከልም፣ አርበኛው አየለ፡፡ አንድ ሻምበልና ሁለት ባለሌላ ማዕረግ ጣሊያኖች ገደለ፡፡ ብዙ የጦር መሣሪያ ማረከ፡፡ ጣልያን እስከ ሦስት ቀን ሬሣና ቁስለኛውን ሲያነሱ፞ከረመ፡፡

አርበኞች አያያዛቸው ስለአስደነገጠው ጄነራል ትራኪያ ደብደቤ ፃፈ፡፡ ደብዳቤው አድራሻው ለልጅ ግዛቸው ኃይሌ ሆኖ፣ "...ሳደረስክብን ጉዳት ጀግንነትህን አመስግነን አልፈነዋል፡፡ ነገር ግን ወደፊት ይህን የመሰለ ብልግና ሥርተህ ብትገኝ..." ይልና የድንፋታ መዓት ያወርዳል፡፡ ከዚያም አልፎ አርበኛው መስከረም 19 ቀን 1929 ዓ.ም ለጣልያን እንዲገባ ያዛል፡፡ አርበኛው ደብዳቤው ተነብቦለት ሁኔታውን ከተገነዘበ በኋላ፣ ለሚቀጥለው ፍልሚያ ዝግጅቱን ቀጠለ፡፡ ጣልያን ቀን ቆርጦ፣ የሰጠውን ቀጠሮ ሳይጠብቅ፣ ጦር አዘጋጅቶ ሊመጣ መሆኑን ጠረጠረ፡፡

ጠላት ደብረ ሲናና ደብረ ብርሃን የሚገኘውን ጦሩን አስከትቶ አንቀሳቀሰ፡፡ አርበኞችም ከየአሉበት ተጠራርተው መስከረም 18 ቀን 1929 ዓ.ም ምቹ ምቹ ቦታ ያዙ፡፡ መሶቢት የተባለውን ኬላ በቃፊር አስጠበቁ፡፡ ከዚያም ጣልያንን መስከረም 19 ቀን 1929 ዓ.ም ጥዋት ገጠሙት፡፡ ዋናው ቡድን ከግንባር ሲዋጋ፣ ሌላ ፈጣን ቡድን ከጀርባ ዞሮ በጥይት ጠዘጠዘው፡፡ ጠላት ከጀርባው የመጣበትን አርበኛ ደምስሶ ወደ ኋላው ለመመለስ ሞከረ፡፡ ከጀርባ ታዝሎበት የነበረው አርበኛም በር ለቀቀለት፡፡ ነገር ግን ከግንባር የገጠመው በኃይል እየተጠጋ አጠቃ፡፡ ጠላት እየተከተለ ሲያፈገፍግ፣ ከጀርባ ታዝሎበት ከነበረው ጦር ደጀን ላይ ወደቀ፡፡ በዚህ ዓይነት ከመሐል አስገብተው በጣልያን ጦር ተጫወቱበት፡፡ በጥይትም፣ ገደል በመግባትም ያለቀው አልቆ የተረፈው ወደ ገደል ላይ ተከማቸ፡፡

ጦርነቱ በማግስቱ ጥዋት ቀጠለ፡፡ ከንጋቱ እኩል ሰዓት እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ውጊያ ተካሄደ፡፡ ድሉ ባማያወላውል ሁኔታ የአርበኞች ሆነ፡፡ ብዙ ኢጣልያውያን ሞቱ፡፡ ከሦስት መቶ በላይ መሣሪያ ተማረከ፡፡ ብዙ ባንዳ አለቀ፡፡ በአርበኞች የደረሰው ጉዳት በጠላት ላይ ከደረሰው ጋር ሲመዛዘን አነስተኛ ነበር፡፡

ጠላት ይህንን ውርደት ለመሸፈን አፋጣኝ እርምጃ አልወሰደም፡፡ አዲስ ጦር ወዲያውኑ አልላከም፡፡ ይህም የሁኔታውን አደገኝነት ለመገንዘብ፣ የሕዝቡን ልቡና ለማለዘብና ምቹ ጊዜ ለመጠበቅ፣ በቂ ዝግጅትም ለማድረግ አስቦ ሳይሆን አልቀረም፡፡ ነገር ግን የአርበኞቹ አቅዋም እየጠነከረ እንጂ እየላላ አልሄደም፡፡ ስለዚህ ብዙ ጦር አዘጋጅቶ ተንቀሳቀሰ፡፡ አርበኞቹም ጥር 23 ቀን 1929 ዓ.ም ጣርማ በር ላይ ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት፤ ድል አድርገውም ወደ መጣበት መለሱት፡፡[1]

በጣርማ በር አካባቢ የሚካሄደውን ጦርነት ከመደገፍ ጋር፣ የተጉለት አርበኞች ራሳቸውን ማጠናከር ያዙ፡፡ ከሽም በተባለው ቦታ፣ በጕተራ የነበረውን የመንግሥት እህል በሕግና በሥርዓት ተከፋፈሉ፡፡ ይህም ሁለት ታላቅ ጥቅም ነበረው፡፡ አንደኛው ጥቅም፡- ለአርበኛው ድጋፍ መስጠት ሲሆን፣ ሁለተኛው፡- ከጠላት እጅ አለመውደቁ ነበር፡፡



በተጉለት ውስጥ የአርበኝነት ሥራዎች ከተካሄዱባቸው ቦታዎች አንዱ ጂም ጉዳና ስጋጥ ነበሩ፡፡ ፍልሚያው፡- ጣልያን ሰላድንጋይን ለመያዝ፣ አርበኞች ደግሞ ላለማስያዝ ሆነ፡፡ ምክንያቱም ይህቺ ቦታ ወደ መንዝም ለመሻገር ሆነ ተጉለትን ለመቆጣጠር ምቹ በመሆንዋ ነው፡፡ ጣሊያን ለአድዋ ጦርነት (1888 ዓ.ም) በተዘጋጀ ጊዜ ኮንትአንቶኔሊ ባልታወቀ መንገድ ሰላድንጋይ ድረስ መጥቶ፣ ሰልሎ ሄዶ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ጣልያኖች በዚች ቦታ ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርገው ነበር፡፡[2] ይህቺን ከተማ ለመያዝ የተደረገው ትንንቅ ከባድ ነበር፡፡ ከተጉለት አርበኞች አንድ ፊታውራሪ ወንድምነህ ብቻ ከመሞታቸው በፊት፣ ሃያ ሦስት ጊዜ ከጠላት ጋር ውጊያዎች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህም ውጊያዎች ከግማሽ የሚበልጡት በሰላድንጋይና በአካባቢዋ የተካሄዱ ነበሩ፡፡ ጠላትም ይህቺን ከተማ ለመያዝ ከአንድ ዓመት ያላነሰ መዋጋት ነበረበት፡፡

ሰላድንጋይን በመያዝ ቀደም ብሎ የደረሰበትን ሽንፈት ለመሸፈን ጠላት አዲስ ጦር ሠርቶ መጣ፡፡ አርበኞች የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠሙት፡፡ መከራ ሥቃዩን አሳይተው ወደ መጣበት መለሱት፡፡ ጣልያንም ይህቺን ከተማ መያዝ የግድ ስለሆነበት ደጋግሞ ተዋጋ፡፡ ለአርበኞቹም የሞት ሽረት ሆነባቸው፡፡ የካቲት 23 ቀን ታላቅ ውጊያ አካሂደው እንደገና መለሱት፡፡

ጠላት አዳዲስ ጦር ማቅረቡን ቀጠለ፡፡ በኃይል ጥሶ ለመግባት ቁርጠኛ ሆነ፡፡ በከሀዲዎች ምክር እየታገዘ ማጥቃቱን ቀጠለ፡፡ የቀረበው ሲያልቅ፣ ሌላ አዲስ ጦር ይተካ ቀጠለ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ተተኪ የሌለው እየሞተ፣ እየቆሰለ፣ አንዳንዱም እየከዳ ስለሄደ፣ የአርበኛው ሠራዊት በመዳበር ፋንታ መሳሳት ጀመረ፡፡

ጣልያን ከጉር፣ ከጣርማ በር፣ ከደብረ ሲና፣ ከደብረ ብርሃን፣ ከአሥመራም ሳይቀር ከፍተኛ ጦር አመጣ፡፡ መጋቢት 1 ቀን 1929 ዓ.ም አስከትቶ ሌሊቱን ተንቀሳቀሰ፡፡ ነቅተው ይጠብቁ የነበሩት አርበኞችም ከንጋቱ አንድ ሰዓት ላይ ገጠሙት፡፡ ጠላት ሲጨንቀው ወደ ደብረ ምጥማቅና ወደ ነጩ አገር አዘቀዘቀ፡፡ ሌላው ቡድን በጣርማበር፣ በበጐች ጋጥ ወደ ጉንች አምባ ሄደ፡፡ አርበኞች በየበሩ እየጠበቁ ደበደቡት፡፡ ሞቱም በመጥቀም ፈንታ ጐዳው፡፡ ጥቃት ስለበዛበት ወደ ኋላው ተመለሰ፡፡ ከጠላትም፣ ከወገንም ብዙ ሰው ሞተ፡፡ አርበኞች ግን ድሉን እንጂ ሞቱንና ቁስለቱን ከቁም ነገር አልቆጠሩትም፡፡

ይህም ሆኖ ጣልያን ሰላድንጋይን ለመያዝ መጣጣሩን አልተወም፡፡ አንድ ጊዜ በአንዱ፣ ሌላ ጊዜ በሌላው ቦታ ለማጥቃት ሞከረ፡፡ ቤት እያቃጠለ ይጓዝ ጀመር፡፡ ጉሬን ዋሻ ከተባለው ዳገት ላይ ሲደርስ ገጠሙት፡፡ ዳገቱን በአሳር በመከራ ሲወጣ በጥይት በመደብደቡ፣ በጉልበቱ እየዳኸ የወጣውን ዳገት፣ በጐኑ እየተንደባለለ እንዲወርደው አደረጉት፡፡

በመላጥና በከስካሽ ወንዝ ገብቶ እንደዚህም የዓሊ ልጆች የአለቁበት ቦታ፣ ማለትም በሶስት ቦታ በማጥቃት ሰላድንጋይን ለመያዝ ሞከረ። አርበኞችም መሣቆ፣ አሞራ ወይራ ሆነው ጠበቁት። ሌላው ቡድን ደግሞ በጠሞሬ አፋፍ ሄዶ በመለጥ በኩል የመጣውን ገጠመው። በሦስቱም በር መልካም ሥራ ተሠራ። በመለጥ የመጣውን መንገዱን አጠሩበት። እሱም በበኩሉ ዘዴውን ለወጠ። የዛለን ገደል መከታ እየሰጠ በሽምሽምና በቁርቆር ወረደ። አርበኛው ደግሞ በኋላ ዋሻ በኩል አቋርጦ በጠላት ጀርባ በመታዘል ተጨማሪ ጦር እንዳያገኝ አገደበት። ሌላው ቡደን ደግሞ በመስቀሌ በር በኩል አጠቃ። የበጐች ጋጥ እስከሚባለው ቦታ ድረስ ወጥተው ገጠሙት። በበጐች ጋጥ በኩል የመጣው በመጫን አርበኞችን አስለቀቃቸው። የዛለን ገደል መከታ እየሰጠ በሽምሽም፣ በቀረጥ በኩል ወረደ። አርበኞችም ከቀለበት እንዳያስገባቸው ድርግሚት የተባለውን ቦታ ቀድመው ለመያዝ ሞከሩ። ከጠላት ወታደር ጋር እኩል ደርሰው የጨበጣ ጦርነት ሆነ። ከጨበጣው ጦርነት የደነገጠ ኢጣልያዊ ወታደር ጠመንጃውን ረስቶ ድንጋይ በመወርወር የአንዱን አርበኛ ጠመንጃ ሰይፍ ሰበረባቸው። ሽማግሌው አርበኛ ደግሞ የገዛ ጠመንጃውን ነጥቀው እሱ ራሱ አጉርሶ ረስቶት በነበረው ጥይት ገደሉት። አርበኛው ተገድዶ የመጣውን ወታደር መጨረስ ትቶ፣ መሪዎቹን መግደል ያዘ። ፊታውራሪ አጐናፍር፣ ቀኛዝማች አውላዬ አቶ አድምቄ የተባሉትን ቀንደኛ ባንዶች በቅጽበት ረፈረፋቸው። ጠላትም ከሞት የተረፈውን ወታደሩን ይዞ በበጐች ጋጥ በኩል በመግጠሙ ከጣልያንም ከአርበኞችም ብዙ ሰው ወደቀ። ይህ ሁሉ ተጋድሎ ሰላድንጋይን ሳያድን ቀረ። መጋቢት 1 ቀን 1929 ዓ.ም በጣልያን እጅ ወደቀች። አርበኞችም የሞተውን ቀብረው፣ የቆሰለውን በቃሬዛ እየተሸከሙ ወደየሠፈራቸው ሄዱ። ጠላትም የሰላድንጋይ ካህናትን ገደለ። መጋቢት 4 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ ጣልያን ግዮት ድረስ ተሻግሮ፣ ዝማሞ ድረስ ያለውን አገር አቃጠለው።

ጣልያን ሚያዚያ 26 ቀን 1929 ዓ.ም ከሰላድንጋይ ወደ መንዝ ለመግባት ተንቀሰቀሰ። ሞፈር ውሃን ተሻግሮ መንዝን ረገጠ። ሴቶች ኡኡ አሉ። አርበኞች ከባሬንታ፣ ከደንገዜ፣ ከአጉን፣ ከየአካባቢው ተሰበሰቡ። እመወይታ ደረሱና በየቦታው ተሠራጩ። ጠመንጃ ያላቸው መሣሪያቸውን ይዘው፤ ጠመንጃ የሌላቸው ጉራዴአቸውን፣ ጦራቸውን፣ አንካሴአቸውን ይዘው ተነሱ፤ ሴቶች በበኩላቸው ዘነዘናቸውን ይዘው ተነሱ። ጣልያን ከእስተየ ዳገት ሲደርስ ያዙት። ገሚሶቹ ግንባር ለግንባር ገጠሙት፤ ገሚሶቹ ደግሞ ከምዕራብ በኩል ዞረው በስተጐን ቆረጡት። በጥይት ቆሉት፤ በጐራዴ ጨፈጨፉት። በድንጋይ ውርወራ ራሱን እየነደሉ ጣሉት። ሴቶች አናቱን በዘነዘና ፈረከሱት፤ በመጥረቢያ ቆራረጡት። ጣልያንም ወደ መጣበት ወደሰላድንጋይ ተመለሰ። በሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ ማረኩ።



ይህ ሁሉ ሲሆን ሰላድንጋይ ያለው የጠላት ጦር ለወገኑ እርዳታ ማሰጠት አልቻለም። እስከ ገና መምቻ ወረደ። ሲያቸፈችፍ ውሎ ወደ ምሽጉ ተመለሰ። ጣልያን ይህንን የመሰለ ውርደት የደረሰበት በአርበኞቹ ብርታት ብቻ አይደለም። ከሰላድንጋይ ወደ መንዝ የሚያሻግረው የሞፈር ውሃ ወንዝ መልካ አንድ ብቻ በመሆኑና፣ ያውም በቀጭን መንገድ፣ ጥልቀት ባለው ቁልቁለት ወርዶ፣ በጠባብ መልካ ወንዙን ተሻግሮ፣ እንደገና በቀጭን መንገድ ረጅም ዳገት የሚያስወጣ ከመሆኑ ጋር፤ የመንገዱ ግራና ቀኝ በአጋም፣ በቀጋና በቀንጠፋ የታጠረ በመሆኑ ጭምር ነው። የሞፈር ውሃ ወንዝ እንደውሃው የሰው ደም ያናብልበታል እየተባለ ይነገር የነበረው ትንቢት ተፈፀመ። ሚያዝያ 26 ቀን 1929 ዓ.ም የጠላት ደም ከውሃው ጋር ተቀላቅሎ አናበለበት።

መንዝን በቀላል መያዝ እንዳይችል ጣልያን በውል ተረዳ። ጄነራል ትራኪያ ሌሊቱን ሌላ ጦር አንቀሳቀሰ። ደብረ ሲና ያለው ጦር ሰላድንጋይ እንዲገባ አደረገ። እሱ ራሱ የደብረ ብርሃንን ጦር ይዞ ከስካሽ ወንዝ ድረስ በመውረድ ሬሣና ቁስለኛውን አሰባሰበ። በዚህ ጊዜ አርበኞች ሌላ ጥቃት ለማካሄድ አላመቻቸውም። ምክንያቱም በአንድ በኩል ሠራዊቱ ከሚያዝያ 26 ቀን ጦርነት ገና ባለማገገሙ ሲሆን፤ ሌላው ምክንያት ደግሞ ጣልያን ላሎ ምድርና ሞላሌ ምሽግ እንዲሠራ የሚፈልጉ ወገኖች ስለነበሩ ከጀርባቸው ጥቃት እንዳያደርስባቸው ጥንቃቄ በማድረግ ነበር።

ጣልያን መንዝን ለመያዝ ከአራት ማዕዘን ሲንቀሳቀስ ዋናው አዛዥ ጄነራል ትራኪያ ነበር። እሱም የደብረሲናንና የደብረ ብርሃንን ጦር ሰላድንጋይ ከነበረው ጋር ቀላቅሎ አዘመተ። ሁለተኛው ጦር ደግሞ ከማማ ምድር፣ በላሎ ምድር መጥቶ ሰፌድ ሜዳን ያዘ። ሦስተኛው ወገን ከወረይሉ ታቹን መጣ። አራተኛው ወገን ከጅሩ በአንባይ ተሻግሮ ጌራ ምድርን ከበበ። ሞፈር ውሃ በፈሰሰ ዋያት በመለሰ መንዝን አጥለቀለቀው። ብዙ አይሮፕላኖች እያስነሳ አሥራ ሦስት ቀን ሙሉ ሀገሩን አስደበደበው። አርበኞችም በየወንዙ፣ በየተራራው፣ በየጉጡ ተጋደሉ። በጠላት ላይ ብዙ ብዙ ጉዳት አደረሱ፤ ብዙዎች በጀግንነት ወደቁ። ነገር ግን የጠላትን እርምጃ ሊያግዱት አልቻሉም። ነገ ለመሰለፍ፣ ዛሬ ማምለጥ አስፈለገ። ስለዚህ ከቦሩ ሜዳ ወጥተው ሄዱ። በሸህ ሱልጣን የሚመራውን የአዘቦ ራያ ጠላት አምጥቶ፣ ሽማግሌና ሕፃን ሳይቀር ወንዱን አሰለበው፤ አሮጊትና ሕፃናት ሳይል ሴቱን ጡቱን አስቆረጠው። በሴቶች ላይ የተካሄደው ድፍረት ብዙዎችን የዕድሜ ልክ ህሙማን አድርጐ በአረማዊነቱ ሲታወስ ይኖራል። ጣልያን ይህንን በመሰለ ጭካኔ ሰውን ፈጅቶ ሚያዝያ 29 ቀን 1929 ዓ.ም መንዝ ገባ።

ጠላት መንዝ እንደገባ ሥራውን ቀጠለ እንጂ ድል አገኘሁ ብሎ አልተዘናጋም። ቃፊሩን አስተያ ላይ አቆመ፤ የሞላሌን ምሽግ ገንብቶ

አጠናከረ። መንዝን ለመያዝ የረዱት ከሐዲዎች ውሎ አድሮ እንደማይተኙለት በማወቅ እያስከሰሰ በየምክንያቱ ፈጃቸው፤ የተረፉትን እያሠረ አንገላታቸው።

ምንጊዜም ቢሆን ሀገሩን፣ ወገኑን የከዳ በማንም ዘንድ ታማኝነትን አያገኝምና፣ በተራው ከሐዲ የሚጠፋው በከሐዲ እጅ ነው። በዚህ ዓይነት ጣልያን መንዝን ለመያዝ የረዱትን ከሐዲያን በልዩ ልዩ ዘዴ ካስገለለ በኋላ፦ ሞላሌ ያለው ጦር አገሩን ለመዝረፍ፣ ቤቱን ለማቃጠልና ሰዉን ለመፍጀት በሁለት ረድፍ ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም በአንድ ወገን እመወታን፣ በሌላ ወገን ደንገዜ፣ ከዚያም ሲያልፍ ይሞድ ላይ ወጉት። ቤት ማቃጠሉን ለማስጣል፣ አርበኞች መሐል ለመሐል ጥሰው እየገቡ በጥይት ጠዘጠዙት። የጠላት ወታደሮች ጭንቅ ሲይዛቸው፣ ከአርበኞቹ ጥይት ለማምለጥ ራሳቸው ከለኮሱትና ከሚነደው ቤት እየገቡ ሲቃጠሉ እንደታዩ በታሪክ ተመዝግቦአል። ለርዳታ የመጡት የጠላት አይሮፕላኖች በዚህ ትርምስምስ ውስጥ መለየት እያቃታቸው የገዛ ወታደራቸውን በቦምብና በመትረየስ ደበደቡት። አርበኞች በሚያስደንቅ ሥልት ወታደሩን ስለፈጁበት፣ ጣልያን ወደ ተነሣበት ወደ ሞላሌ ምሽግ ተመለሰ። የተመለሰውም የሞቱበትን ወታደሮች ሬሣ፣ ቁስለኛውን ሳይቀር በእሳት እያቃጠለ ነበር።

አርበኞችን ለመደምሰስ ጠላት አዲስ ጦር ማምጣቱ ተሰማ። አርበኞች በበኩላቸው ደንገዜ ላይ ተሰብስበው ምክር አደረጉ። በምክሩም ላይ ሁለት ሐሳብ ቀረበ። አንደኛው ሐሳብ፦ የጠላትን ጦር መክበድና የሀገሩን መጐዳት እያመዛዘነ፣ ቦታ ለውጠን ብንከላከል ይሻላል የሚል ነበር። ሁለተኛው ደግሞ፦ መንዝና ተጉለትን፣ ይፋትን ለቅቀን አንሄድም፤ የሕይወታችን ፍፃሜ ከዚህ ይሆናል አለ። ሁሉም እንደየፍላጐቱ ለሀገሩ እንዲከላከል ስምምነት ተደረገ። ቦታ መለወጥ የመረጠው ቡድን፣ በአቶ ወልደመስቀል ተሸበሩ መሪነት ወደ ጅሩ ሄደ። የዓደባይን ኸረት ይጠብቅ የነበረውን የጠላት ጦር ሰብሮ ግንቦት 3 ቀን 1929 ዓ.ም እነዋሪ ላይ ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ ጋር ተቀላቀለ። በመንዝና በተጉለት ተጋድሎዉን መቀጠል የመረጠው ሠራዊት፣ በልጅ ግዛቸው ኃይሌ መሪነት በነበረበት ቆየ።

የአርበኞች መለያየት ለጣልያን ደስታ ሆነለት። በደቡብ ያሉ አርበኞችን ጨርሶ ሀገሪቱን በሙሉ መያዙን የሚገልጽና ከሞት የተረፈው የመንዝ ሕዝብ በየአመዱ እንዲገባ የሚጋብዝ የጥሪ ወረቀት በመንዝና በተጉለት በአይሮፕላን በተነ። ፉከራው ክባድ ስለነበረ፣ መልስ መስጠትም ስለአስፈለገ፣ መልስ ተሰጠው። የተሰጠው መልስ ማስታወቂያዎቹ ደርሰው እንደታዩ፣ መላዋን ኢትዮጵያ ይዤአለሁ የሚለው ውሸት እንደሆነና ከአሥመራ እስከ አዲስ አበባ በመኪና የሚንቀሳቀሰው በመሸማቀቅ እንደሆነ ገልፆ "...እኛ የሸዋ ልጆች ስለውሸትህ የጥይት ሽልማት እናጐናጽፍሀለን..." የሚል የተስፋ ቃል የሚሰጠው ሆነ።



ጠላትም የመንዝን ሕዝብ ቁርጠኝነት ከተረዳ በኋላ ከባድ ጦር አንቀሳቀሰ። አርበኞችም ከሐምሌ 19 ቀን እስከ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ደንገዜ ላይ ገጥመው፣ አሳሩን አሳይተው፣ ወደ መጣበት ወደ ሰላድንጋይ ምሽግ መለሱት። የጥይት ሽልማት ሊሰጡት የገቡለትን ቃል ኪዳን ፈፀሙ።

አርበኞችን ለመደምሰስ የተማመነበት ጦር አምጥቶ እየደጋገመ አዘመተ። ነገር ግን ሰባት ጊዜ ከአካሄደው ስብሰባ በአንዱም አርኪ ውጤት ሳያገኝ ቀረ። የጦርነቱ ድግግሞሽ አርበኞች አዲስ ስልት እንዲቀይሱ አስገደደ። ስለዚህም እርስበርሳቸው ቃል ኪዳን ተግባቡ። ቃል ኪዳኑም ሁሉም በየግንባራቸው የተመደቡበትን ሥራ እንዳይለቁ የሚገድብና ከመካከላቸው አንዱ ቢሞት ሌላው የሟቹን ቤተሰብ እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ድረስ እንዲከላከል የሚያስገድድ ነበር። በዚህ ዓይነት ቃል የተገባቡት የመንዝ ጀግኖች ከአሉበት ቦታ ፍቅቅ ሳይሉ ጠላትን አምስት ጊዜ ወጉት። እየደጋገመ የሶማሌ ጦር ቢያመጣም አልተበገሩለትም። የተግደረደረ መስሎት፣ ጠላት ከመሐል ቦታ ድንኳን አስጥሎ መዝናናት ያዘ። አርበኞች በሰላይ ከአጠሩ በኋላ በመነፅር ተመልክተው ማን ማንን እንደሚመታ ተከፋፍለው ከሩቅ በማነጣጠር፣ አንድ ላይ ሮምታ በመተኮስ፣ ሲዝናኑ የነበሩትን ከፍተኛ የጠላት የጦር መኰንኖች በአንድ ጊዜ ጨረሱአቸው።[3]

በመንዝና በተጉለት፣ በ1929 ዓ.ም የተካሄደው ጦርነት ከሞላ ጐደል ይህንን ይመስል ነበር። ጠላት ይቀዘቅዘልኛል፣ አርበኞችም ይደክማሉ የሚል ሐሳብ አድሮበት ነበር። ነገር ግን የ1930 ዓ.ም ሁኔታ የባሰ ሆነ። በዚህ ጊዜ ከቡልጋ ወገን መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ስለመንገሡ በመንዝና በተጉለት አዲስ ወሬ ተሰማ።

በዚሁ ሰሞን፣ ቀደም ብለው በድንገት ተማርከው የነበሩት ፊታውራሪ ወንድምነህ ጓደኞቼን አባብዬ አመጣልሀለሁ የሚል ቃል ለጣልያን በመስጠት ከተለቀቁ በኋላ እንኳንስ ሌላ ሊያመጡለት፣ እሳቸው ራሳቸው የአርበኝነት ትግላቸውን ቀጠሉ።

በሰላይ አማካይነት ከሚያገኙት መረጃ አንዳንድ እየሳተ ስለአስቸገራቸው አርበኞች ራሳቸው ወደ ምሽግ እየቀረቡ ማጥናት ያዙ። በተጉለት አካባቢ የነበሩ አርበኞች በደብረ ብርሃን አካባቢ የነበረውን ሁኔታ እየቀረቡ አጠኑ፤ መስከረም 26 ቀን 1930 ዓ.ም እስከ ዘንዶ ጉር ድረስ ተጠግተው አጠኑ። አንደኛው ጥቅም፦ በአንድ የባንዳ መሪ ቤት የተደበቁ ሠላሣ አፈድስት መውዜር ከነጥይቶቻቸውና ሌላም ለአርበኛው የሚያገለግሉ ጥሪቶች ማግኘታቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥቅም ደግሞ፦ የጠላትን ሁኔታ በቅርብ ማወቃቸው ነበር።

አርበኛው ከዚህ ጥናት በኋላ ወደ ዘንዶ ጉር አመራ። ገጦ ከተባለ ቦታ ጣልያንን ግንባር ለግንባር ገጠመው። ጣልያን በመድፍ ድብደባ የሚያካሂድበትን መሥመር በልዩ ልዩ ዘዴ እያለፈ በመጠጋት፣ ብዙ ጉዳት

አደረሰበት። ምርኮው ግን የሚያረካ አልሆነም፤ ልብስም ቢገኝ ብል የበላው ሆነ።

የገጠን ጦርነት ለመበቀል፣ በመስከረም ወር መጨረሻ 1930 ዓ.ም ጠላት ሌላ ጦር በሣጋ በኩል አመጣ። አርበኞች ለመቁረጥ እንዲመቻቸው ግንባር ቀደሙን ጦር ወደ እነሱ ወደራሳቸው ትተው ከመካከለኛው ጦር ላይ አደጋ ለመጣል ተማከሩ። ይል ከተባለ ቦታ አድፍጠው ጠብቀው እንደዚሁ አደረጉ፤ እየነጣጠሉ ደበደቡት። የጠላት ጦር ወደ መጣበት ወደ ሣጋ ሩጫውን ቀጠለ። አንድ ግራ የገባው የጠላት ወታደር መትረየሱን ትቶ እግሩን ተሸክሞ ሮጠ። አርበኞችም የእንጨት እግር ሠርተው በመትረየሱ ተጠቀሙበት። ጠላት ከወገኑ ብዙ ሰው ስለሞተበት፣ ሬሣውንና ቁስለኛውን ሳይቀር ከቤት ውስጥ እያገባ በማቃጠል ሸሽቱን ቀጠለ። ከአርበኞችም ብዙ ሰው ቆሰለ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይም እጃቸው ላይ ቆሰሉ።

ጠላት እንደገና በአርበኞች ላይ ሳያስቡት አደጋ በመጣል ለማጥቃት ተንቀሳቀሰ። በራያው /ደጃዝማች/ ከፈለው ወልደፃድቅ የሚመሩ አርበኞች ሁኔታውን በቅድሚያ በማወቅ ምቹ ቦታ ይዘው ጠበቁት። ጥቅምት 16 ቀን 1930 ዓ. ም ቀያ ከተባለው ቦታ ገጥመው ደበደቡት። ጠላትም ወታደሩን አስፈጅቶ ሸሽቱን ቀጠለ።

ህዳር 18 ቀን 1930 ዓ.ም ደንገዜ ቆሎ ማርገፊያ ከጠላት ጋር ከፍተኛ ጦርነት ተደረገ። በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመሩት አርበኞች የጠላት ጦር ወደፊት እንዳይገፋ፣ ወደ ኋላውም እንዳይመለስ ሰግጠው በመያዝ ከህዳር 18 እስከ 22 ቀን ድረስ አራት ቀን ወጉት። በአይሮፕላን ቢያስደበድባቸውም፣ አልተበገሩለትም። እንዲያውም በአይሮፕላን የተጣለለትን ሰባት ሣጥን ስንቅና መሣሪያ እየተሽቀዳደሙ በመልቀም ወሰዱበት። ከጦሩም ብዙ መሣሪያ ማረኩበት።

በደጃዝማች አውራሪስ የሚመራው አርበኛ፣ እዚያው ደንገዜ ሬንቻ ከተባለው ቦታ የነበረውን የጠላት ጦር ከብቦ አስጨነቀው። ውሃ እንዳይቀዳና ለስንቁ ማብሰያ እንጨት እንዳይሰብር ከልክለው ከህዳር 18 ቀን እስከ 24 ቀን 1930 ዓ.ም አሰቃዩት። በመጨረሻም ህዳር 28 ቀን ጦርነት አድርገው ጉዳት አደረሱበት፤ በአይሮፕላን እያስደበድባቸውም ብዙ ገደሉበት። ጠላትም ከጦርነቱ የተረፈውን ወታደሩን ይዞ ከከበባውን በማምለጥ ሰላድንጋይ ገባ።

ሁኔታው ሲከብድበት ጣልያን በጄኔራል ማሊቲ የሚመራ ጠንካራ ጦር ላከ። አርበኞቹ ደንገዜ ላይ ታህሣሥ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ደረት ለደረት ገጥመው ለአራት ቀን ወጉት። ብዙ ወታደር ፈጁበት። ጄኔራል ማሊቲ የተቀመጠበት በቅሎ ተመትቶ ሲወድቅ፣ እሱ ለጥቂት አምልጦ ደብረ ብርሃን ገባ። የአርበኞች ልብ ደነደነ፤ አንዳንድ ባንዳም ከጠላት ወደ እነሱ ዞረ።[4]

የደንገዜ ጦርነት በዚህ አላበቃም። ለጣልያን ይህንን አካባቢ ከአርበኞች ማስለቀቅ አስፈላጊ ነበር። ለአርበኞቹም ደንገዜ ወሳኝ ቦታ ነበረች።



ስለዚህ ጣልያን አዲስ ጦር አመጣ። ከታህሣሥ 20 እስከ 26 ቀን 1930 ዓ.ም ብርቱ ጦርነት ተደረገ። ጣልያን ለማጥቃት አርበኞች ለመከላከል በብርታት ተፋለሙ። ከጠላትም፣ ከወገንም ብዙ ሰው ወደቀ። ጦርነቱን መቀጠል ሰው ማስጨረስ መሆኑ ስለታወቀ፣ አርበኛው ሸሽ /ላሎ ምድር/ ተሻግሮ ተቀመጠ። ሁለቱም ወገን ስለተዳከመ፣ ኩራኩሬ ያለው የጠላት ጦርና ሸሾ የሠፈረው አርበኛ ማዶ፣ ለማዶ እየተያዩ ሳይተነኳኰሉ ሁለት ሣምንት ያህል ተቀመጡ።

ጣልያን መንዝን የመያዝ እርምጃውን ቀጥሎ መሂ ደረሰ። ይህ መሂ የተባለው አካባቢ ደጋ ነው። በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዳምጠው መሸሻ የሚመራው አርበኛ ጥር 28 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠመው። ሲወጋው ውሎ፣ ሲወጋው አደረ። በማግስቱ በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመራው አርበኛ ለእርዳታ ደረሰ። በጠላት ላይ ተከነበለበት። የጠላት ወታደርም እንዳይተኩስ ቆፈን፣ እንዳይሸሽ ብርክ ያዘው። ሁለት ነጮች ከጥቂት ወታደር ጋር ሲያመልጡ፣ አብዛኛው በጥይትና በጉራዴ አነከቱት። ጣልያንም የተረፈውን ጦር ይዞ ወደኋላው ተመለሰ የመሂ እልቂት በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ሲታወስ ይኖራል።

ጣልያን ተደጋግሞ በደረሰበት ውርደት ተቆጨ። በቂ ጦር ለማዘጋጀት ጊዜ ፈጀበት። ስለዚህ በየካቲት፣ በመጋቢትና በሚያዝያ በዚህ አካባቢ ጦርነት ማካሄድ አልቻለም። አርበኞች እረፍት አደረጉ፤ የቆሰለው አገገመ። ጠላትም አስተማማኝ የመሰለውን ጦር አዘጋጅቶ የወሎን ጦር በሰፌድ ሜዳ፣ የራያንና የጥሙጋን በምችግ፣ የጀሌንና የወረይሉን ባይገም አሳልፎ በአፍቅራ ላይ ሊያዘምት ተንቀሳቀሰ። የአርበኛው ቁጥሩ እጅግ ብዙ ስለነበር፣ ባለመተዋወቅ እርስበርሱ እንዳይጐዳዳ በበኩሉ ጥንቃቄ አደረገ። ጠላት አስቀድሞ መጥቶ ከላውን፣ ምችግን፣ ከወደኋላም የዱገምን በሮች እንዳይዝበት ተሽቀዳደመ። ከመድረሱም ገጥመው፣ ግንቦት 30 ቀን 1930 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ጣልያን የአርበኛውን መጠንከር ሲያይ ከምድር በመድፍ፣ ከሰማይ በአይሮፕላን በቦምብ ደበደበው። አርበኛው ተጠግቶ የጨበጣ ውጊያ ተካሄደ። ከሁለት ቀን ፍልሚያ በኋላ የጠላት ጦር ከወዲያ ወዲህ ተራወጠ። ድሉ ለአርበኞች ሆነ።

በዚህ ጦርነት በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት ደረሰ። ከአርበኞችም ወገን ብዙ ሰው ሞተ፤ ሌላም ብዙ ቆሰለ። ቢሆንም ድል የእነሱ በመሆኑና ብዙ ምርኮ በማግኘታቸው ተጽናኑ። የምርኮን ነገር ስንመለከት በዚህ ጦርነት ላይ ከተከናወኑት ሥራዎች የአንድ የአርበኛንና የአንድ ባንዳን ጉዳይ ማውሳት ይገባናል። አንድ ወጣት አርበኛ ከአንድ ባላገር ቤት ገብቶ ባካሄደው ዝርፊያ ተከስሶ ጥፋቱ ከተመረመረ በኋላ ይቀጣል፤ መሣሪያውንም ይገፈፋል። ጀሌውን እንዳለ ይህ ከላይ የተገለፀው ጦርነት ይካሄዳል። ወጣቱ በደረሰበት ቅጣት ቅሬታ፣ ባዶ እጁን በመሆኑም ፍርሐት ሳይሰማው ከጦርነቱ ገባ። በድንጋይ ውርወራ ጠላቱን ገድሎ መውዜር ጠመንጃ ማርኮ ስለመጣ፣

በጓደኞቹ ዘንድ ተደነቀ፡፡ በዚህ ዓይነት የወንድ ሥራ በመሥራት፣ የዜግነት ግዳጁን ለመወጣት በቃ፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ጦርነት የተገኘው ምርኮ በሚሰበሰብ ጊዜ፣ አንድ ባንዳ ከስድስት መቶ ሬሣ ውስጥ ተሸጉጦ ተገኘ፡፡ ጤነኛ ነበር፡፡ አርበኞቹ ይዘው ሲመረምሩት ማንነቱ ታወቀ፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ ምክር ተሰጠው፡፡ ወደ ዘመዶቹ ሄዶ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ሰብስቦ፣ እንዲመክር ተነገረው፡፡ ቢሆንላቸው የሀገራቸውን ጠላት እንዲወጉ፣ ይህም ባይሆን አርፈው እንዲቀመጡ እንዲያደርግና የአርበኞችን ዓላማና ጥንካሬ እንዲነግር ታዘዘ፡፡ እሱም ተስማምቶ ወደ ሀገሩ ሄደ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ በእሱ ትውልዶ ቦታ የነበሩ ሰዎች በመንዝ ላይ አልዘመቱም፡፡

ከዚህ ጦርነት በኋላ አርበኞች ስብሰባ አድርገው ተማከሩ፡፡ "…በአንድ ላይ ተከማችተን ብንቀመጥ በስንቅ እንጐዳለን፤ ብንበታተን በጠላት እንጠቃለን፡፡ ስለዚህ በየቦታችን ሆነን ነቅተን እንጠብቅ፡፡ ጠላት በመጣ እንረዳዳ" ተባባሉ፡፡ እንደዚሁም አደረጉ፡፡

በመንዝና በተጉለት የ1930 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1931 ዓ.ምቱ ተጀመረ፡፡ የአካባቢው ሁኔታ አስግቶት ነበርና፣ ጣልያን ክረምቱ እንደወጣ ማጥቃት ጀመረ፡፡ መስከረም 7 ቀን 1931 ዓ.ም ሲመጣ ሐሳቡ በአካባቢው ያሉትን አርበኞች አስደንግጦ በማባረር፣ ሣሲት አሻል ላይ ምሽግ ለመሥራት ነበር፡፡ አርበኞቹ ሐሳቡን አውቀውበት ነበርና፣ እነሱ ከአሉበት ድረስ እስኪመጣ ድረስ መጠበቃቸውን ትተው እሱ አለበት ድረስ ሄደው ገጠሙት፡፡ ውጊያው፡- ከምድር በመድፍና በቦምባርድ፤ ከሰማይ፡- በቦምብ እየተደገፈ በከባድ እግረኛ ጦር ከሐሙስ እስከ እሑድ፣ ለአራት ቀን ተካሄደ፡፡ ከግራ፣ ከቀኝ ብዙ ጠላት ወደመጣበት፣ ወደሰላድንጋይ ሸሸ፡፡ አርበኞች ለማሸነፍ የቻሉት የኋላኛው እንዳይጠጋና ለእርዳታ እንዳይደርስ በጥይት በማገድ፤ ከጦር ግንባር የገባው ደግሞ ወደፊት እንዳይገፋ እንዲሁም ወደኋላው እንዳይመለስ በጥይት ቆልፎ በመያዝ ነበር፡፡ ጭንቅ ሲሆንበት ያለቀው እያለቀ ወደኋላ መመለስን መረጠ፡፡ አርበኞች ብዙ መሣሪያ አገኙ፡፡[5]

ይህ በእንዲህ እንደአለ ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ መሞታቸው በዚያ ተሰማ፡፡ ራስ አበበም ወደ ተጉለት ዞሩ፡፡ ጠላት የማጥቃት ሥራውን በማጠናከር ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ሌላ ጦር አምጥቶ ሣሲትን ለመያዝ ሞከረ፡፡ ሣሲት ላይ ምሽግ በመመሸግ በመስከረም 7 ቀን የደረሰበትንም ውርደት መሸፈን ነበረበት፡፡ አርበኞቹም እንደልማዳቸው ከየአሉበት ተሰባስበው ገጠሙት፡፡ ሙሉ ቀን ውጊያ ተካሂደ፤ ስመጥር አርበኞች እዛ ወደቁ፡፡ ከጠላትም ወታደር ብዙ አለቀ፡፡ አንዱም ወገን ሳያሸንፍ ወደየቦታቸው ተመለሱ፡፡

ራስ አበበ ከቡልጋ ወደ ተጉለት በጥቅምት ወር 1931 ዓ.ም ዞሩ፡፡ በተጉለት ቆይታቸው የሠራዊቱን አንድነት ለማስተባበር ስለሚቻልበት መንገድ



ላይ ምክር ተደረገ፡፡ ቀደም ብሎ አምቦ ላይ ተመሳሳይ ምክር ተደርጐ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ የጣልያን ሐሳብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፈጅቶ፣ የራሱን ሕዝብ አምጥቶ ማስፈር መሆኑ በዚህ ወቅት ለቁል ጭምር ግልጽ ሆኖ ነበር፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አርበኞች የሚጋደሉት ስለሀገር ነፃነት፣ ስለሃይማኖት ስለ ወገን ክብር መሆኑ ለከሀዲያን ጭምር እየታወቀ ሄዶ ነበር፡፡ በሦስተኛው ወገን የአርበኛውን አንድነት የሚያጠናክር አንድ አሰባሳቢ አካል ማስፈለጉ እውን ሆነ፡፡ በአራተኛው ወገን ደግሞ አርበኛው ሲሞት፣ ሲቆስል፣ ሲታመም የትም ወድቆ መቅረቱና ስሙም መታሰቢያ አለማግኘቱ ዕለት፣ ዕለት የሚታይ ጉዳይ ነበር፡፡ ስለዚህ አንድ የመተባበሪያና የመረዳጃ ማህበር መመሥረት አስፈላጊ ሆነ፡፡ አርበኞች እነዚህን ጉዳዮች በመመልከት ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ተጉለት አንቀላፋኝ ላይ የጀግኖች ማህበርን መሠረቱ፡፡ የመተዳደሪያ ደንብም አወጡ፡፡

የመተዳደሪያ ደንቡ ሃያ ሦስት አንቀጽ ያለው ሆኖ ዋና ዋና ነገሮችን የሚያመለክት ነበር፡፡ ከሚደርስባቸው ችግርና አደጋ እርስበርሳቸው እንዲረዳዱ፣ የሞተውን ለመቅበር፣ የቆሰለውና የታመመውን ለማስታመም፣ አርበኞችም ምንም ዓይነት ችግርና መከራ ቢያገኛቸው ሕይወታቸው እስኪያልፈ ከመከራከር በቀር ለጠላት እንዳይገዙ ወይም ወገናቸውን እንዳይከዱ፣ አንዱ አንዱን እንደ እናት ልጅ እንዲያየው፣ በደረሰበት አደጋ አይቶት ጥሎ እዳይሄድ በሰልፍም /በጦርነት/ ውስጥ ትቶት አጋልጦት እንዳይሸሽ፣ ማህበሩ የሚያወጣውን ምልክት እንዲይዝ፣ ሹማምንቶች እንዲመረጡና በዚሁ ደንብ መሠረት እንዲሠሩ፣ ሹማምንቱንም አርበኛው በፈለገ ጊዜ እንዲለውጣቸው፣ ማህበርተኛው በፍፁም ልቡ የማህበሩን ደንብ እንዲፈጽም፣ ከአሥር አንድ እንዲሰጥ፣ እርዳታ መቀበል የሚገባውን የተመረጡት ሹማምንት እንዲመርጡ፣ አጥፊን ማህበሩ በመሰለው እንዲቀጣ፣ የሟቾች ቤተሰቦች እንዲረዱ፣ ማህበሩ ደንቡን በመጨመር፣ በመቀነስ ወይም በማደስ እንዲያሻሽሉ፣ ማህበሩ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሚሰጠውን ሕግና ደንብ፣ ትእዛዝም እንዳይቃወም፣ ማህበሩም "የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኞች ማህበር" እንዲባል የሚወሰን ሆነ፡፡[6]

ከማህበሩ መቋቋም ጋር አብሮ መጤን ያለበት የጊዜው ሁኔታ ነው፡፡ ከወቅቱ ሁኔታዎች ዋና ዋናዎቹን ስንመለከት፡- ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ሞተው አርበኛው መሪ ያጣበት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ቀቢፀ ተስፋ የተቃረቡበት፣ ጣልያን በእርቅ ስም የሰውን ልቡና ለመከፋፈል የሚራወጥበት፣ አውሮፓውያን የኢጣልያን ትብበር ለማግኘት ሲሉ የኢትዮጵያን ጉዳይ ቸል ያሉበት፣ የዓለም መንግሥታት ማህበር ለመውደቅ የሚንገዳገድበት፣ የጀርመንና የጃፓን ኃይል የገነነበት ጊዜ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የማህበሩ መቋቋም የአርበኝነትን ሥራ አጠናክሮአል፡፡ አሁን ስለአለው ማህበርም መነሻ ሆኖአል፡፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንም ሥልት አርበኛው

መልሶ እንዲቀበል በማድረግ ረድቶአል። ስለዚህ ማህበሩን ያቋቋሙ አርበኞች በታሪክ ክብርም ምስጋናም ይገባቸዋል።

ምንም እንኳን በተደጋጋሚ በተካሄዱት ጦርነቶች ጉዳት ቢደርስበት፣ ጣልያን አርበኞችን ለማጥቃት የሰነዘረውን ክንዱን ሳያጥፍ እርምጃውን ቀጠለ። በራስ አበበ የሚመራው ሠራዊት ህዳር 27 ቀን 1931 ዓ.ም ምሑይ ላይ ለሦስት ቀን ውጊያ አካሄደበት። አንድ ኢጣልያዊ ከፍተኛ መኮንን ሞተ። ከበባው ጠንካራ ስለነበር ጣልያን ለወታደሩ ጥይትና ስንቅ በአይሮፕላን አምጥቶ ጣለ። ነፋስ አቅጣጫውን ለውጦ ነበርና ስንቁ ለአርበኞች ደረሰ። በውጊያው ላይ ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ከአርበኞችም ጀግኖች ወደቁ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ ማረኩ።

የሸዋ አርበኞች ሐሳብ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ዓይነት ተጠቃሎ እያለ የጠላት ጦር መጣ። አርበኛው ህዳር 5 ቀን 1931 ዓ.ም ዲርማ ከተባለው ቦታ ገጠመው። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ወደቀ። ራስ አበበም ከጉንጫቸው ላይ በጨረፍታ ቆሰሉ። የጠላት ኃይል አይሎ ነበርና ወደ ዋዩ፣ ከዚያም ወደ ገደማ ሄደው ሰጠ ሰገድ በተባለው ቁልልታ ላይ ሰነበቱ። ከዚያም በታህሣሥ ወር 1931 ዓ.ም ወደ ቀያና ዘረት ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

ከዚያ እንደደረሱ ምክር ተጀመረ። ዋናው ሐሳብ ጀማ ላይ መሽጐ ተቀምጦ የነበረውን ጦልያን ለመውጋት ነበር። የዚህ ምሽግ መሰበር፣ ስንቅና ትጥቅ ለማግኘት፣ ቅዝቃዜ የታየበትን የወሎን ትግል መልሶ ለማቋቋም እንደሚረዳ ታስቦበት ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ሐሳቡ በመንዝና በተጉለት አርበኞች ዘንድ ሥጋት ፈጠረ። ዋናው ጥያቄ፦ ከሆነስ ደግ ሳይቃናስ ቢቀር? የሚል ነበር። ሃምሣ አለቃ ታደሰ ባላይነህ እና መምሬ ኀሽሜ ወልደጊዮርጊስ ቀያ ድረስ በመሄድ የተሠማቸውን ሥጋት ገለፁላቸው። ቢቀር እንደሚሻል አስረዱአቸው። ራስ አበበም ይህንን ምክር ሰሙ። የጀማን ምሽግ ለማጥቃት የነበራቸውን ሐሳብ በመተው ወደኋላ ተመልሰው መረው ላይ ሠፈሩ።

ጠላት በራስ አበበ በሚመራው አርበኛ ላይ ጥቃት ለማካሄድ በማሰብ፣ ከሞላሌ ተነስቶ በቆሎ ማርገፊያ በኩል አድርጐ ማያ ከተባለው አጠገብ፣ ፈረስ መጋለቢያ ሠፈረ። ወደስጥ ለመሄድ ያሰበ በማስመሰል ሠራዊቱን ለማዘናጋት ትንሽ ከተጓዘ በኋላ አቅጣጫውን ለውጦ ራስ አበበ ወደ ነበሩበት ወደ ቀያ ገሠገሠ። ሐሳባቸው አወናብደው ክብ ለመሥራት ነበር። ውግር ማልቀሻ ከሚባለው መልካ፣ ሞፈር ውሃ፣ ከወንዝ ገባ። ውሃ ሲጠጣና ሲታጠብ፣ አርበኞቹ ድንገት ደርሰው አደጋ ጣሉበት። በጥይት ሲጨፈጭፉት ተርበተበተ። አንዳንዱም ከባሕር እየዘለለ እየገባ በገዛ እጁ ሞተ። የሚበዛው አርበኛ፣ ጥይት አለቀበት።

ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደብዳቤ መምጣቱ በሕዝብ ጆሮ አስቀድሞ ተሞልቶ ነበርና፣ ወረው እተባለው ቦታ ድረስ እንዲሰበሰብ ለሕዝቡ ጥሪ ተላለፈ። ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ፣ ሳይል ሕዝብ ተሰበሰበ።



ከንጉሠ ነገሥቱ የመጣውን ደብዳቤ ራሳቸው አነበቡ። እልልታው ቀለጠ፤ መትረየስ በብዛት ተተኮሰ። ታላቅ ደስታ ሆነ። ከደስታቸው ጽናት የተነሣ ያለቀሱ ብዙዎች ነበሩ።[7]

ይህ ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥቱ፣ ከለንደን ታህሣሥ 27 ቀን 1931 ዓ.ም በቁጥር 69 የተፃፈው ሳይሆን አልቀረም። እሱ ከሆነ ንገሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ የመንግሥታት ሕግ እንዳይጐድልባት ለዓለም መንግሥታት ለማስታወቅ አውሮፓ እንደሚገኙ ይገልፃል። ቀደም ብሎ ከአርበኞቹ የተፃፈላቸው ደብዳቤ፦ ከጠላት ጋር በጀግንነትና በመተባበር የሚከላከለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላትን እስከመጨረሻው በመቃወሙ ቆርጦ፣ ለነፃነቱ የሚታገል መሆኑ ለዓለም ሕዝብና ለመንግሥታት ማህበር ለማስረዳት በብዙ እንደረዳቸው የገለጸ ነበር።[8] የንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ደርሶ አርበኞችን ማስፈንጠዙ እና ደብዳቤዉም ለሕዝብ ግልጽ መደረጉ፣ ቅስቀሳ ለማካሄድ መሆኑን ይገነዘቧል።

በዚህ የተነሣ ጥቃቱን እንደገና አጠናከረ። በጥር ወር 1931 ዓ.ም እንቅስቃሴ አደረገ። ጠላት የአርበኞችን እንቅስቃሴ ነቅቶ መጠበቅ ሥራው እንደመሆኑ፣ በአውሮፓ በመካሄድ ላይ የነበረው ሁኔታ አስጊ በነበረበት በዛን ጊዜ አርበኞች ማህበር ማቋቋማቸውን፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ማግኘታቸውን፣ ሕዝብ ማስተባበራቸውን ሲሰማ፣ በቀላል እንዳይለቃቸው አውቀው ተዘጋጅተው ነበርና ጀምጉዳ ከተባለው ቦታ ተዘጋጅተው ጠበቁት። አደጋ ጥለው ከባድ ጉዳት አደረሱበት። ብዙ ወታደር ጨርሰው፣ ብዙ መሣሪያ ማርከው፣ ወደ መጣበት መልሰው አባረሩት።

ጠላት በተጉለት ሲንቀሳቀስ፣ አርበኞች ሞጃ ዋሻ ውስጥ ተከተቱ። ጠላት ይህንን ሰምቶ መጋቢት 15 ቀን 1931 ዓ.ም ከበባቸው። ሁኔታው አስቃቂ ሆነ። ሰብረው ለመውጣት አቅማቸው የሚፈቅድ አልነበረም። አቶ ወልደ ገብርኤል የተባሉ ጀግና፣ በሕይወታቸው ቆርጠው እና ጥቂት ጓደኞቻቸውን ይዘው ፈጥነው በመድረስ ከበባውን በጦር ሰብረው ወገኖቻቸውን ከጥፋት አዳኑ። እንደ እኔ፣ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

በዚሁ ወር ከአርበኞች ጋር በተደረገው ስምምነት ጠላት ደንገዜ፣ ሸሎ መሽጐት የነበረውን ምሽግ ለቅቆ ቆሎ ማርገፊያ፣ ማማ ምድር ወደሚባለው ሄደ። በኋላ፤ እርቅ በፈረሰ ጊዜ፤ አርበኞች በዚህ ምሽግ ላይ ለስድስት ቀን ከበባ አካሂደው አሣሩን አሳይተውታል።

ራስ አበበ ወደ ተጉለት ተሻግረው፣ ከዚያም ወደ ቡልጋ፣ ለመዝ፣ ጉይአና ሰገድ ከተባሉት ቦታዎች መካከል ደረሱ። የጠላት ጦር ይህንን ሰምቶ ወደ አንቀላፊኝ ገሠገሠ። በሃምሣ አለቃ በላይነህ የሚመራው አርበኛ በግሥጋሴ ደርሶ አያፍሩባ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጣለበት። በረዶ እንደመታው ቅጠል አራገፈው፤ ራስ አበበን ለማጥቃት በማለት የተንቀሳቀሰበትን ዓላማውን አፈረሰበት።

እርቅ በፈረሰ ጊዜ ለጠላት ከንቱ ምክር እየመከረ፣ የባንዳን ሁኔታ እያጠናከረ፣ የሰላድንጋይን ምሽግ የሙጥኝ ብሎ ተቀምጦ የነበረውን፣ ወልደገብርኤል የተባለውን የጠላት መሣሪያ ማስታገስ አስፈለገ። በመሆኑም አንድ የአርበኛ ቡድን ከተጉለት ተንቀሳቅሶ ሚያዝያ 23 ቀን 1931 ዓ.ም በድንገት ደርሶ ፀጥ አድርጐት ወደ ቦታው ተመለሰ። አንድ ኢትዮጵያዊ በዚህ ዓይነት መገደሉ የሚያሳዝነው ይኖር ይሆናል። ባይገደል ግን እሱ በሚቆሰቁሰው ጦርነት እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን መሞታቸው ይቀጥላል። እሱም ተመክሮ ያልታገሠ በመሆኑ ከዚህ መጥፎ ግብሩ አይታቀብም ነበር። ስለዚህ የተወሰደው እርምጃ ተገቢ ነበር። ለነገሩ የተመካበት ጠላትም ሳይከላከልለት ቀረ።

ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ። ጣልያን ከሰላድንጋይና ከሣሲት ምሽግ ወታደር አዘመተ። በአንቀላፌኝ በኩል ወደ ዓባይ ቆላ ለመውረድ ሲግተለተል፣ አርበኛው አይካና ግፍጥጫ ከተባሉት ቦታዎች ጠብቆ በጥይት ሸነቆጠው። ጣልያንም ከሸንቆጣው የተረፈውን ወታደሩን አስከትሎ ወደ ምሽጉቹ ተመለሰ። ጣልያን ምሽግ እየሠራ፣ ባንዳ ምሽግ እየተጠጋ አስቸገረ። ይህንን ሁኔታ ለማስታገስ የመንዝ አርበኛ እርምጃ ወሰደ። በተለይም ሃምሣ አለቃ ታደሰ በላይነህ የሚመሩት የወደደውን በመምክርና በማስረዳት፣ እምቢ ያለውን በጦር ኃይል በማጥቃት ወደነፃነት ተጋድሎ እንዲመለስ ለማድረግ ሠራዊቱ በቡድን ተከፋፍሎ ተንቀሳቀሰ። ከመሣቆ ተነስቶ፣ በመዘዘ በኩል አድርጐ፣ ታቦርና ዳግግት ያሉትን ሽማግሌዎች አማከረ። የደምፍላት የደረሰበት አርበኛ በወሰደው የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ብዙ ሰው አለቀ። ብዙ ንብረት ወደመ። ባንዳው ንግግር ሰብሮ ተኩስ በመክፈቱ የሞተ ሬሣው ፍትሐት እንዳይደረግለት፣ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይቀበር ተከለከለ። ምንም እርምጃው ከባድ ቢሆን፣ በመቀጣጫነት ጠቀመ። ሰው በምክርም፣ በቀለብም ረዳቸው። በተለይ አቶ ሞገስ ተሰማ የተባለ የጭዋ ልጅ፣ የመኪና ስፌት እውቀት ስለነበረው፣ የተቀዳደደው ልብሳቸውን በነፃ በመጥቀም ረዳቸው። ታርዘው የነበሩትንም በገንዘቡ ልብስ እየገዛ አለበሳቸው።

ከደግነት እልቂት ከተረፉት ባንዶች መካከል ጥቂቶች ደብረ ሲና ሄደው የደረሰባቸውን ጉዳት ለጌታቸው፣ ለጣልያን ነገሩ። ጣልያን ጦሩን እያግተለተለ በመሰቢት ተጉዞ እናዥጋ አፋፍ ላይ መትረየሱን ጠምዶ አንፈቀፈቀው። ደግነቱ አካባቢው ድንጋያማ ስለነበር አርበኞች ከእነዚያ ሥር እየተጠለሉ ከመዓቱ እንኳን ዳኑ። ተኩስ ድምጽ ሳያሰሙ፣ ገደሉን እየቧጠጡ ወጥተው አፍንጫው ላይ የነበረውን ጡምና የተባለውን በር ያዙበት። ጣልያን ይህንን ሲያይ ምንም ሳይወላዳ ሰተት ብሎ ደብረሲና ምሽግ ገባ።

መንገዶች ተዘግተው፣ ገበያ በመጥፋቱ ምክንያት፣ በአርበኛው ላይ ረሃብ ፀና። ይህንን ችግር ለመወጣት ለጦርነት አመች የሆኑትን ገደላ ገደል



ቦታዎች እየተወ ሕዝብ ወደ ሠፈረበት አካባቢ መሄድ ግድ ሆነበት። ቀድሞውኑ ለም የሆኑትን ቦታዎች እየለቀቀ የሄደው አገር እንዳይጠፋ፣ ሕዝብ እንዳያልቅ ነበር። ስለዚህ አንዱ የአርበኞች ቡድን ቆብ አስጥል ሄዶ ተቀመጠ። ጠላት ደግሞ ገስግሶ ደረሰ። ወሬውን ስለሰሙ ሊከባቸው የመጣውን ጦር እነሱ ከብበው እንደራቻ ወቁት። ማር ማረፊያ ደረስ አባረሩት።

የቆብ አስጥልን ጦርነት ወሬ ሲሰማ ጠላት ሌላ ጦር ሠርቶ እዚያው ቆብ አስጥል፣ ግም ውሃ ድረስ መጣ። አርበኞች ቦታ ይዘው ጠብቀው ደንገተኛ አደጋ በመጣል ብዙ ወታደሮች ገደሉበት። ጠላት ስለአየለባቸው፣ ሴት አምባ ወደ ተባለው መንደር ወረዱ። ወይራ አልዲት ከተባለው ቦታ የነበረው ጠላት እንዳያጠቃቸው፣ አመጤ መቀመጫ የተባለውን ተራራ ተገን አድርገው ወደ ጸሐና ወጡ። ከቆብ አስጥል ጀምሮ ይከታተላቸው የነበረው ጠላት ገሥግሦ ደረሰባቸው። እነሱም እንዳልለቀቃቸው ባዩ ጊዜ ጥለው መነጠሩት። እሱ በተራው ሲሸሽ፣ ጥፍጥፍ ድንጋይ ድረስ እያባረሩ በመሸንቆጥ ወንፈላቸውን ከፈሉት።

የቆሰለውም፣ የታመመውም፣ ያገግም በዛ በነበረበት ጊዜ፣ ጠላት አደጋ ጥሎ ለመፍጀት ተሾልኮ መጣ። ወይዘሮ ብርቅነሽ ወልደሥላሴ አይተውት ኖሮ "ልጄ እንግዶችህ መጡልህ" ብለው ልጃቸውን ሃምሣ አለቃ ታደሰ በላይነህን ቀሰቀሱ። እሱም ባልደረቦቹን ቀስቅሶ አንጥፎ በመጠበቅ፣ ባልተጠበቀበት ቦታ አደጋ ጥሎ ጠላቱን አዋረደው። ብዙ ምርኮም አገኘ።

የጠላት ጦር ከሰላድንጋይ መጣ። አርበኞች መጋቢት 2 ቀን 1931 ዓ.ም ሬት ሜዳ ላይ ግንባር ለግንባር ገጥመው ታላቅ ጉዳት አደረሱበት። ጠላት ጦርነቱን ያካሄደው በምድር በመድፍ፣ በሰማይ በአይሮፕላን እየታገዘ ነበር። አርበኞችም እርስበርሳቸው ተጋገዙ። በአጀና የወረደውን የጠላት ጦር፣ በልጅ መኰንን ጉሽሜ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው አርበኛ ዲማ ላይ ገጥሞ በመኀሸም ኃይሉን ቀነሰው። በሌሎች ጉራዎች የተሰለፈውም የጠላት ጦር እንደዚሁ ውርደት ተቀብሎ ወደጊላው ተመለሰ። በዚህ ጦርነት ብቻ 83 ኢጣልያውያን ቆስለዋል። የሞተው ባንዳ ከቁጥር አልገባም።

መጋቢት 5 ቀን 1931 ዓ.ም ጠላት በራስ አበበ ሠራዊት ላይ አደጋ ጣለ፤ አርበኞችም መክተው ተዋጉ። ውጊያው ከጥዋቱ አራት ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ቀጠለ። ቀን ሲመሽ አርበኞች በጀረት ሚት በኩል ወደ ናስ ወረዱ። ከዚያም መጋቢት 6 ቀን ወደ ቡልጋ ለመዘር ተነሱ።

ጠላት አርበኞችን ለማጥቃት ሌላ እንቅስቃሴ አድርጎ አሞራ ወይራ ከተባለው ቦታ ደረሰ። አርበኞቹ የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል እንዳይሰናከል ጠብቀው ሚያዝያ 24 ቀን 1931 ዓ.ም ገፍጥጫ ከተባለው ቦታ ላይ ገጠሙት፤ ከሁለቱም ወገን ሰው ሞተ። ጣልያንም ወደ አንቀላፌኝ ለመሄድ የነበረውን ሐሳብ ትቶ ወደ መጣበት ተመለሰ።[9]

በዚህ ወርና አመት፣ በቡልጋ የሚካሄደው ጦርነት ጠንክሮ ነበር። ጠላትም ከየአለበት ጦር እየሰበሰበ ወደዚያ ያለማቋረጥ ይልክ ነበር። ስለዚህ የመንዝ አርበኞች ይህንን ሁኔታ አጥንተው የማደናቀፊያ ስልት ቀየሱ። ከሰሜን የመጣውን ጦር ግንቦት 11 ቀን 1931 ዓ.ም ደብረ ብርሃን አጠገብ ልቺ በር እንደ ሠፈረ አደጋ ጥለው ጉዳት አደረሱበት። አርበኞችን በመበተን ወደ ቡልጋ የመሄድ ዓላማውን አሰናከሉበት።

በመንዝ አካባቢ የነበረው አርበኛ የበጋውን ወራት በእንዲህ አሳለፈ። በክረምት ወራት ጠላት እምብዛም ስለማይንቀሳቀስ ከቀለብ በስተቀር ሌላ ችግር አልነበረም። በነሐሴ የንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ከደረሰ በኋላ አርበኞች ከወሰዱት እርምጃ አንዱ ሕዝቡን ማሳመንና ማስተባበር እንደሆነ ተመልክተናል። በዚሁ መሠረት በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመራው ሠራዊት ከቀወት እስከ እናዥጋ፤ ከዚያም በደብረ ሲና አካባቢ አልፎና ሮቤን ተሻግሮ፣ የመኪና መንገዱን አቋርጦ እስከ ገደባ ድረስ ሄዶ አሣመነ። ሕዝቡም ያለ ችግር ተቀበለ። በሌላው ወገን የተሠማራው ቡድን ደግሞ ወደ ግድም ሄደ። ነገር ግን አቶ አልታየ የተባለ ባንዳ የአካባቢውን ሰው አሣብሮ ለመውጋት ስለከጀለ፣ አርበኞቹ በፍጥነት ደርሰው በጦር ኃይል እሱንና ጥቂት ተከታዮቹን ደመሰሱአቸው።

ክረምት እንደ መሆኑ መጠን የምግብ ችግር አጋጥሞ ነበር። ደግሞም ክረምት ሲጠባ የጠላት እንቅስቃሴ በአዲስ ኃይል ይጠበቅ ነበርና የመንዝና የተጉለት አርበኞች ምክር አደረጉ። በምክሩም ደጃዝማች አውራሪስ ከነሠራዊታቸው በተወሰነላቸው አካባቢ እንዲሠፍሩ፣ ልጅ ተፈሪ ዳኜ ከባልደረቦቻቸው ጋር ተጉለትና ደንገዜ እንዲሆኑ፣ ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ሰዎቻቸውን ይዘው ወደ ደጋው አገር ወደ አራድግ እንዲወጡ፣ ከጠላት ጥቃት የደረሰበት በቶሎ ድምፅ እንዲያሰማና ሁሉም እንዲረዳዱ ተወሰነ። በውሣኔው መሠረት ለመፈፀም አያት ሜዳ ላይ ተሰነባብተው ወደየቦታቸው ሄዱ።

ነሐሴ 29 ቀን 1931 ዓ.ም ዷት ከተባለው ቦታ ከቁም ነገር ያልተቆጠረ አንድ መለስተኛ ግጭት ከጠላት ጋር ተደረገ። ውጊያውም እምብዛም ሳይቆይ፣ ደፍረው ተኩስ ከከፈቱት የጠላት ወታደሮች ሰባቱ ሲገደሉ የቀሩት ሸሽተው አመለጡ። ውጤቱ ግን ከባድ ሆነ። ከአርበኞች ወገን አንድ ሰው ሞተ፤ ሌላ አንድ ሰው ቆሰለ። የቆሰሉት አርበኛ ጀግናው ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ሲሆኑ፣ የተመቱትም ከቆሰለው ከአሽከራቸው ሾልካ በወጣች ጥይት ነበር። እሱ ወዲያው ሲሞት፣ እሳቸው እስከ ጥቂት ቀን ድረስ ቆይተው ጳጉሜ 3 ቀን 1931 ዓ.ም አረፉ። ላሎ ምድር፣ ጠል እግዚአብሔር አብ በሰማዕትነት ደረጀ ፍትሃተ ነፍስ ተደርጎላቸው ተቀበሩ። አስቀድሞ ለጦር ጓደኞቻቸው አያት ሜዳ በተባለው ቦታ የሰጡአቸው ምክር "...ለመሠረታችሁት ሥራዎች ደምዳሚዎች ሁሉ ..." የሚል ነበር። ጠላትን



ሠላሳ ሦስት ጊዜ ግንባር ለግንባር ገጥመው ያንቀራጠጡት ጀግናው ልጅ ግዛቸው ኃይሌ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ የዜግነት ድርሻቸውን ተወጥተው አረፉ።[10]

በመንዝና በተጉለት በ1931 ዓ.ም የተካሄደው ትግል በዚህ ዓይነት ተጠናቅቆ የ1932 ዓ.ምቱ ተተካ። የጠላት የጦር ሥልት ደግሞ ከመስፋፋት ይልቅ የያዙትን ወደ መጠበቅ ዞረ፤ ቀደም ብሎ ያደርግ እንደነበረው አዘውትሮ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወሩ ተቀነሰ። ለባላገሩ እረፍት ሆነ። አርበኞችም በበኩላቸው ለመሰባሰብና እርስበርሳቸው ለመወያየት አመቻቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ስንቅና ትጥቅ የመመንተፍ ዕድላቸው ተቀነሰ። ይህንን ችግር ለማቃለል ምሽጎችን መተምተም ነበረባቸው። ጠላት ደግሞ ጠቡ እንዲባባስ አልፈለገም። ስለዚህ ሊከላከላቸው ያልቻለውን ምሽጎች በእርቅ ስም እያደረገ ለቀቀ።

ቀድሞ በሹክሹክታ ይሰማ የነበረውን የእርቅ ወሬ፣ ጣልያን በሬዲዮና በጋዜጣ ያናፍሰው ጀመር። ደህናው ሰው ሁሉ ልቡ ተከፈለ። ቀኛዝማች ታደሰ በላይነህ፣ በእሳቸው አስተባባሪነት ስር የነበረውን ሠራዊት ለመምራት ሁነኛውን ነገር እሳቸው ራሳቸው ከራስ አበበ ጋር ተገናኝተው ቃል ለቃል መነጋገር አስፈለጋቸው። ስለዚህ በቀኛዝማች ታደሰ በራሳቸው የሚመራ ቡድን ወደ ቡልጋ ለመሄድ ከአስቶ በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም ተነሳ። እምብራባርን አቋርጠው ጉር ሲደርሱ የጠላት ጦር ደም አይጠማሽ ከተባለው ቦታ ሠፍሮ አገኙ። እሳቸውን ለማጥቃት የተንቀሳቀሰ ጦር መሆኑን የኢጣልያንኛ ቋንቋ በሚያውቁት፣ አብረዋቸው በነበሩት አርበኛ፣ በግራዝማች አበበ አማካይነት ከንግግራቸው አረጋገጡ። ስለዚህ ድንገተኛ የጭለማ አደጋ በመጣል ሠፈሩን በጠበጡት። የጠላት ጦር እርስበርሱ ተዋጋ። ደም አይጠማሽ የጠላትን ደም በእጅጉ ጠጣች፤ እነሱ ግን እንኳን ሞት፣ ቁስለት ሳያገኛቸው መንገዳቸውን ቀጥለው በዥብ ዋሻ በኩል በማለፍ አስቶ አምባ ገቡ።

አስቶ አምባ ሲደርሱ ደግሞ ሌላ የጠላት ጦር አጋጠማቸው። ደም አይጠማሽ ከደረሰው አደጋ ወገኑን ለመርዳት የተንቀሳቀሰ ሳይሆን አልቀረም። በዚህ ጊዜ ደግሞ አርበኞች ጠላት በአካባቢአቸው መኖሩን አላወቁም። ጠላት ግን እነሱ መቃረባቸውን አውቆ ተኩስ በመክፈት አደጋ ጥሎ አቶ ይመኔ ወልደ ፃድቅ የተባሉትን የቂሮ በረት አርበኛ ጣለ። እነሱም በጥይት ቅብቅብ በማራወጥ ዋጋውን ከፈሉት። ከዚያም ቡድኑ ጉዞውን ቀጥሎ፣ በድንባሮ አድርጐ የመኪና መንገዱን በማቋረጥ ላጀ ግንድ ወጣ። ከዚያም አንኮበርን ወደ ግራ ትቶ በቆራ መስክ በማለፍ፣ ጠለስ ከተባለው ቦታ፣ ፊታውራሪ በፍርዴ ሀብተማርያም ከተባሉት የቡልጋ አርበኛ ጋር ተገናኘ። ከእሳቸው ምክርና እረፍት ከአደረገ በኋላ ጉዞውን ቀጥሎ ጌልጌላ ላይ ከራስ አበበ ጋር ተገናኘ።

ራስ አበበ ቡድኑን በክብር ተቀብለው አነጋገሩት። ቀኛዝማች ታደሰ ከራስ አበበ ጋር በግል ለመነጋገር ጠይቀው ደጃዝማች ዘውዱ አባኰራን፣ ከንቲባ ከበረ ኃይለሥላሴና ቀኛዝማች የማነ አባኮራን ባሉበት የምሥጢር ንግግር ተካሄደ። ቀኛዝማች ታደሰም አመጣጣቸው ከመንዝና ከተጉለት አርበኞች ተልከው እንደሆነ፣ መንገዳቸውም እጅግ አስቸጋሪና ታላቅ መስዋዕት የተከፈለበት እንደሆነ ገለጹ። ዋናው ችግር ጣልያን ከራስ አበበ ታርቄአለሁ እያለ በሚነዛው ወሬ የሕዝቡ መንፈስ እንደተናወጠ አስረዱ። አገላለጻቸው እልህ የተቀላቀለበት ነበር። ንግግራቸውን "...እንደዚህ የመሰለው ሐሳብ እንኳንስ ለእኛ፣ ለተተኪውስ ትውልድ ቢሆን ምን ይጠቅማል? ይዘናትስ የምንንከራተተው ሞት የተፈረደባት ነፍስን አይደለም?" በሚል ጥያቄ ደመደሙ።

ራስ አበበም በጥሞና ከአዳመጡ በኋላ እርቁ ለዘለቄታ አለመሆኑን አስረዱአቸው። የቆሰሉት እስኪድኑ፣ የታመሙት እስቲያገግሙ፣ ጥይት ያለቀባቸው የጐደለባቸውን እስኪያሟሉ፣ የጊዜ መፈለጊያ መሆኑን ገለፁላቸው። ለመንዝና ለተጉለት አርበኞች መልእክት እንደ ላኩባቸው ነገሯቸው፣ እሳቸው ግን ሁኔታውን እስኪገነዘቡ እንዲቆዩ ጋበዙአቸው።

ከጣልያን መንግሥት መልእክተኞች ጋር ንግግር የሚደረግበት ቀጠሮ ደርሶ ነበርና፣ ራስ አበበ ከጌልጌላ ወደ ማህበረ በኩር ሲወጡ ቀኛዝማች ታደሰም አብረው ወጡ። የጄነራል ናዚና የጄነራል ፍራንክ ተወካይ ሻለቃ ለኮቲ፣ ጉዳይ ፈፃሚዎቹን ይዞ በመቅረብ ያለውን ሰሙ። የአርበኛውን ስሜት ገመገሙ። ከዚህ በኋላ ከራስ አበበ ተሰናብተው ወደ አገራቸው በመመለስ ያለምንም ችግር ከባልደረቦቻቸው ጋር ተቀላቀሉ።

የእርቁ ምሥጢር በታወቀ ጊዜ፣ የመንዝና የተጉለት አርበኛ ልቡ ደነደነ። ጠላትና ግብረ አበሮቹ ይዘሩት የነበረው ወሬ ፍሬቢስ መሆኑ ተረጋገጠ። በአርበኞቹ ዘንድ ሁኔታውን ለሕዝብ ማስረዳት ስለሚቻልበት ዘዴ ምክር ተደረገ። ነገር ግን በዛ ረገድ ችግር አጋጠመ። በጠላት ስብከት ብዙ ሰው ተታልሎ ስለነበር ዝም ማለት የአርበኝነቱን ሥራ የሚጐዳ ሆነ። በይፋ ቢነገር ደግሞ ምሥጢሩ ለጠላት ደርሶ ሊያስገነግን ሆነ። በዚህ ላይ በክብረ በዓልና ሕዝብ በሚሰበሰብበት አደባባይ የእሱን ሐሳብ የሚቃወም ቃል እንዳይነገር ጣልያን ጥብቅ ቁጥጥር በሕዝብ ላይ ያካሂድ ነበር። ይህ ሁሉ ተመዛዝኖ በሁለቱም ወገን የነበረው አመለካከት ከባድ ስለነበር፣ በፉሊጥ እንዲነገር ተወሰነ።

በዚሁም መሰረት አዋጅ ተነገረ። አዋጁም አርበኞች ያቀረቡት ሐሳብ በጣልያን መንግሥት ተቀባይነት ካላአገኘ እርቁ እንደማይፀና ራስ አበበም አጥብቀው እየተከራከሩ እንደሆነ፣ በጣልያን በከንቱ የተገደሉት የእነ ቀኛዝማች አድማሴና የእነ ባላምባራስ ተምትም ደም እንዲወጣ እንደተጠየቀ የሚገልጽ ነበር። ከዚህም በስተቀር ገና ቁርጡ ባልታወቀ ነገር ወሬ ሲያወራ



የተገኘ ቤቱ በእሳት እንዲቃጠልና ንብረቱ እንዲዘረፍ፣ ለጠላት ሲሰብክ የተገኘ በሞት እንዲቀጣ የሚወስን አዋጅ ወጣ። ምንም አንዳንድ ወሬኛ ውስጥ ውስጡን ቢያንሾካሹክ፣ ወሬው በይፋ መነገሩ ቀረ። የጣልያንም ፕሮፓጋንዳ ከሰረ።

የዚህ አዋጅ መነገር የሕዝቡን መንፈስ ስላለወጠበት፣ ጠላት ተበሳጨ፤ አርበኞችን ከምድረ ገፅ ደምስሶ ለመገላገል አሰበ። ለዚህም አቶ ሣህሉ ወልደገብርኤል የተባለውን ባንዳ ምርኩዝ አድርጐ ተዘጋጀ። ግለሰቡንም ቀኛዝማች፣ ቀጥሎም ፊታውራሪ አለው። ከዚያም መጋቢት 5 ቀን 1932 ዓ.ም ድርገሚት አቦ በሚደረገው ክብረ በዓል ላይ አደጋ ለመጣል ተንቀሳቀሰ። ነገር ግን አቶ አጥናፌ ቀርቹ የተባሉ፣ ሰው በመላክ አርበኞች ወደ ክብረ በዓል እንዳይመጡ አደረጉ። ዕቅዱ ፈረሰ። በዕቅዱ መፍረስ የተናደደው ጠላት ወደ ምሽጉ ሲመለስ አርበኞቹ መሣቆ አዋጅ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጥለው ክፉኛ አጐሳቆሉት።

የመንዝና የተጉለት አርበኝነት በእንዲህ እንዳለ፣ በቡልጋ ወገን እርቅ ፈረሰ፤ ወሬውም ወዲያው ተሰማ። አርበኞች ጠላት በተከታታይ ለሚወስደው እርምጃ ተዘጋጁ።[11]

የእርቅ ንግግር ይደረግ በነበረበት ወቅት፣ በጄነራል ናዚ ትዕዛዝ አንዳንድ ምሽጐች ለአርበኞች በተለቀቁ ጊዜ፣ የላሎ ምድርን ምሽግ ልጅ ተፈሪ ዳኜ በየካቲት ወር 1932 ዓ.ም ተረክበው ነበር። እርቅ ከፈረሰም በኋላ አልለቀቁም ነበርና፣ ጣልያን አዘናግቶ ግንቦት 12 ቀን 1932 ዓ.ም ያዛቸው። እሳቸው በሰላም እንደተቀመጡ መያዛቸውን ምክንያት በማድረግ ስለተከራከሩ ቀወት እንዲቀመጡ ተወሰነ። የአያበርን ምሽግ እና መሣሪያ የተቀመጠበትን ቦታ ሲያጠኑ ከቆዩ በኋላ፣ በአንድ ጠመንጃና በጥቂት እጅ በምብ አደጋ ጥለው አንድ ካፒቴንና አንድ መቶ አለቃ ከብዙ ሐማሴንና ባንዳ ጋር ገደሉ። አንድ ባለውሃ መትረየስና ብዙ ጠመንጃ ማረኩ። ከዚያም በዝማሞ፣ ባይሞድ አድርገው ጥሞናን ገብተው አርበኝነታቸውን ቀጠሉ።[12]

እርቅ በፈረሰ ጊዜ ባልተመቻቸ ሁኔታ ላይ ከነበሩት አርበኞች ቡድን አንደኛው፣ በፊታውራሪ ወንድሜነህ ይመራ የነበረው ነው። እሱም አደጋውን ለማሳለፍ ፈንጣጣ ዋሻ ገባ። ይህ ቡድን እስከ ደብረ ብርሃን ድረስ እየተጠጋ በማጥቃት ጠላትን ቆልፎ የያዘ ነበርና ጠላት ምሥጢሩን አውቆ ከበበው። ከበባው ጠንካራ ሆነ። አርበኞቹም አጥብቀው ተከራከሩ። የጠላት ጦር የተንቀሳቀሰው በሁሉም አካባቢ በመሆኑ፣ እነሱም መልእክት ለማስተላለፍ ስለአልተመቻላቸው፣ ዕርዳታ ሊደርስላቸው አልቻለም። ስለዚህም በሙሉ አቅማቸው እየተከላከሉ ከበባውን ሰብረው በመውጣት ከመጀመሪያው ዙር ወጡ፤ ከሁለተኛው ዙር ክብ ደረሱ።

አርበኞቹ ስምንት ብቻ ሲሆኑ የጠላት ጦር ግን እጅግ ብዙ ነበርና አጠገባቸው የነበረውን ወንዝ ያለጥቋት ለመሻገር ከሁለት ተከፈሉ። አምስቱ

መትረየሱን ይዘው ወንዙን በመሻገር ከኋላ ለቀሩት ጠለላ እንዲሰጡ፤ እነሱ እስኪሻገሩ ደግሞ ሦስቱ ከለላ እንዲሰጡ ተስማሙ። ሆኖም መትረየሱን የያዘው ቡድን ወንዙን ገና ሲሻገር በድንገት ከጠላት እጅ ስለወደቀ፣ ዕቅዱ ሳይሠራ ቀረ። ሁለተኛው ቡድን፣ በመጀመሪያው ቡድን ላይ የደረሰበትን አደጋ ሳላወቀም ነበርና ወደ ወንዙ ተዘቀዘቀ። እሱም የመጀመሪያውን ቡድን ከያዘው የጠላት ጦር ላይ ወደቀ። ነገር ግን እንደፊተኛው ቡድን በቶሎ አልተማረከም፤ አጥብቆ ተከላከለ። የቡድኑ መሪ ፊታውራሪ ወንድምነህ ቢቆስሉም ከአንድ ጉጥ ሥር ሆነው እስከ ስምንት ሰዓት ድረስ ተዋጉ። ጥይታቸውን በጠላት ላይ አፍስሰው ሲጨርሱ በጠላት እጅ ወደቁ። በበቅሎ ተቀምጠው የምርኮ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። የጉዞአቸው መድረሻ ቀደም ብለው በተማረኩ ጊዜ ጓደኞቼን አባብዬ እመጣልሀለሁ ብለው አታልለውት ከነበረው ጣልያን ዘንድ ነበር። ይህ ደግሞ የሚቀበሉት ነገር አልነበረም። ስለዚህ ከአንድ የጠላት ወታደር ላይ ጠመንጃ ነጥቀው ለመታኮስ ሞከሩ፤ ጠመንጃው ጥይት አልነበረበትምና ሳይሆን ቀረ። በዚህ ጊዜ አያያዛቸውን ያየ የጠላት ወታደር የእጅ ቦምብ ወረወረባቸው። እሳቸውም የተጣለባቸውን ቦምብ ቀልበው በመወርወር ብዙ የጠላት ወታደሮች ገደሉ። የጠላት ወታደሮች በብዛት ስለተኮሱባቸው በአንድ ጥይት ከግንባራቸው ላይ ተመትተው ሞቱ። ጠላትን ሃያ ሦስት ጊዜ ግንባር ለግንባር ገጥመው የተዋጉትና መከራ ሥቃይ ያሳዩት ፊታውራሪ ወንድምነህ ገብረኪዳን፣ በሰላሣ ሰባት ዓመት ዕድሜአቸው፣ በእንዲህ ዓይነት የዜግነት ድርሻቸውን ተወጥተው፣ መጋቢት 8 ቀን 1932 ዓ.ም አረፉ።[13]

ክረምቱ ከመግባቱ አስቀድሞ ጣልያን አርበኞችን ከመንዝና ከተጉለት ለመገላገል ተንቀሳቀሰ። ዋናው አማካሪው አቶ ሣህሉ ወልደገብርኤል ሆነ። ከተጉለት በጐሬ ዋሻ፣ ከሰላድንጋይ በአሞራ ወይራ፣ ከወይራ በቆብ አስጥል፣ ከታቦር በመዘዝ፣ ከደብረ ሲና በመሶቢት በኩል ሌሊቱን ሲንኳተት አድሮ፣ ሰኔ 22 ቀን 1932 ዓ.ም ጥዋት፣ ወፍ ሲንጫጫ ተኩስ በመክፈት አደጋ ጣለ። አርበኞች ሁኔታውን እንደሰሙ እየተመካከሩ በሚያውቁት ሥርጥ እየተዘዋወሩ በጠመንጃና በመትረየስ ፈጁት። ከበባውን ሰብረው በመውጣት በወርቅ ዋሻ በኩል አድርገው በድንጋይ መዝጊያ አመለጡ። በግራና በቀኝ ያሉትን ሽንተረሮች መከታ እየሰጡ፣ የሚከታተላቸውን የጠላት ወታደር ረፈረፉት። ከበባውን ሰብረው ለመውጣት የተጠቀሙበት ሥልት ከባቢውን ራሱን ግራ አጋባው። ከእነሱ ወገን የሞተባቸውን ከጥሻ ውስጥ ደብቀው፣ አንድ ነጠላ ለአራት ወጥረው በመያዝ ሬሣ የተሸከሙ አስመስለው፣ ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

ከሮቢ ወንዝ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ጣልያን ሌላ አዲስ ጦር በካሚዎኖች አቀረበ። ከሙሉ ቀን ውጊያ በኋላ ከአዲስ ጦር ጋር መግጠም አደገኛ ሆነ። አርበኞች በፍጥነት ተመካክረው በመኪና ከመጣና ትኩስ ጉልበት



ካለው ጦር ጋር መግጠማቸውን ጥለው፣ ወደ ዋሉበት ወደ እንጨኔ ተመለሱ። ይህም የአሸነፊ መስሎት በነበረው የጠላት ጦር ላይ ድንጋጤ ፈጠረ። እነሱም እየተከላከሉ ወደ ጃሎ አቀኑ። ከዚያ ሲደርሱ ደግሞ ጠላት በር፣ በሩን ይዞ ጠበቃቸው። ይህኛው ከበባ ደግሞ ከፊተኛውም ፀናባቸው። በዚህ ጊዜ ቀኛዝማች ታደሰ በላይነህ የወንድ ሥራ ሠሩ፦ ወደ ጣልያን ዘንድ ሄዶ "...እኔ ታደሰ በላይነህ ነኝ። በር ልቀቅልኝ..." ብሎ የሚነግር መልእክተኛ ላኩ። ጣልያንም ምንም ሳይወላዳ የያዘውን ቦታ ለቆ ደብረ ሲና ከምሽጉ ገባ። በዚህ ዓይነት ቁርጠኛ እርምጃ፣ ያ የተከበበ አርበኛ ከእልቂት ዳነ።

ሰኔ 22 እና 23 ቀን 1932 ዓ.ም ቀንና ሌሊት በተካሄደው ጦርነት ብዙ የጠላት ወታደር ረገፈ። ከአርበኞችም ወገን ብዙዎች ሞቱ። በተለይ የግራዝማች አጐናፍር ኪዳኔን አስከሬን ከተደበቀበት ዋሻ ሰኔ 24 ቀን 1932 ዓ.ም ጠላት አግኝቶ መለጥ ከተባለው ቦታ እስከነበረው ምሽግ ድረስ በመውሰድ ሦስት ቀን ሙሉ ተጫወተበት።[14]

በ1932 ዓ.ም የመንዝና የተጉለት ሁኔታ እንደዚህ ከርሞ ክረምቱ ገባ። ክረምቱ ለአርበኞች የሕይወት፣ ለኢጣልያኖች የውድቀት፣ ለባንዶች የውርደት ነፋስ የነፈሰበት ነበር። በመሆኑም ሁሉም በየፊናው የሚዘጋጅበት፣ የሚመካከርበት ሆነ። የ1933 ዓ.ም ፍልሚያ ቀጠለ።

አርበኞች ጣልያን እነሱ እስከአሉበት ድረስ እስኪመጣ መጠበቃቸውን ትተው፣ እሱ እስከአለበት ድረስ እየሄዱ ማጥቃት ያዙ። በልጅ ተፈሪ ዳኜ የሚመራው ሠራዊት በጥቅምት ወር 1933 ዓ.ም ቆሎ ማርገፊያ በነበረው ጠላት ላይ አደጋ ጥሎ ጉዳት አደረሰበት። ይኸው ቡድን ተጉለት ተሻግሮ ህዳር 23 ቀን 1933 ዓ.ም ዋሊያ ተራራ ላይ መሽጐ የተቀመጠው ጣልያን ላይ ሌሊት አደጋ በመጣል፣ በምሽጉ ውስጥ የነበሩትን ነጮችና ታማኞቻቸውን ባንዶች ገድሎ ብዙ መሣሪያና ስንቅ ነጠቀ። ልጅ ተፈሪ ዳኜ በተያዙ ጊዜ አብረው ተይዘው ከነበሩት መካከል እንደገና ወደ አርበኝነት ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆን ከጣልያን ተጠግተው ይኖሩ የነበሩት፣ በጣልያን ተይዘው ደብረ ብርሃን ተወስደው ታሰሩ።

ይህ ቡድን እየተጠናከረ ከመሄዱ የተነሣ፣ በጠላት ላይ ጭንቀት በመፍጠር የማር ማረፊያን ምሽግ ቀን በቀን በኃይል ገብቶ መዘበረው። በዚህ ሁኔታ የተደናገጠው ጠላት፣ አካባቢውን ለመቆጣጠር ይረዳው ስለ መሰለው፣ ከአንድ ዓመት በፊት ለቅቆ የነበረውን፣ ሸሾ የተባለውን ምሽጉን ታህሣሥ 26 ቀን 1933 ዓ.ም ሌሊት ተሾልኮ በመግባት መልሶ ያዘው ። የሸሾ ምሽግ እንደገና በጠላት መያዝ የማይዋጥላቸው ስለሆነ፣ በልጅ ተፈሪ ዳኜ የሚመሩት አርበኞች ከየአሉበት ተጠራርተው በማግስቱ ታህሣሥ 27 ገጠሙት። የጠላት ወታደሮች ብዙ ነበሩ፤ አያሌ መትረየስም ጭነው ነበር። አርበኞች ግን ጥቂትና የያዙት ከነጠላ መሣሪያዎች ጋር አንድ ውሃ መትረየስ ብቻ ነበር። እሱውም ዪተማረከ ዕለት ዝናሩ ባለመገኘቱ ውግር

ከተባለ ቦታ በተገኘ ሌላ ዝናር የተገጠመ ነበር። በእሱው በርትተው በመዋጋት ሲያይሉበት፣ ጠላት አካባቢውን እሳት ለኩሶ በጭሱ ከለላ ለማምለጥ ሞከረ። አርበኞች እየተከታተሉ ሲያጠቁ ጭሱ ጋረዳቸው። ከጭሱ ወጥተው ጠላትን ለማጥቃት ሲገሰግሱ፣ ያደፈጠ አንድ የጠላት ወታደር ተኩሶ ስለመታቸው፣ የልጅ ተፈሪ ዳኜ ሕይወት በድንገት አለፈች። ሌሎች ጦርነቱን በመቀጠል ጠላትን ከአካባቢው አባረሩት::[15]

የጦርነቱ ሚዛን በኢጣልያ ላይ እንደ አደላ፣ እንዲሁም ንጉሠ ነገሥቱ እንደመጡ ታውቆ እያለ፣ በወዳጅ ዘመድ ምክር አልመለስ ብለው እስከ መጨረሻው ለጠላት በታማኝነት የቆሙ ባንዶች አልታጡም፤ በዛ አካባቢ ዋነኛው አቶ ሣህሉ ድፋዬ ይባል ነበር። በወገኖቹ ላይ ግፍ የሚሠራ ጨካኝ ሰው ነበርና፣ ጠላት መለዋን ሾመው። እሱም ለጠላት መከታ ሆኖ ስለቆመ፣ ጠላትን ለማጥቃት፣ አስቀድሞ እሱን ማስወገድ ግድ ሆነ። አርበኞች ጥር 18 ቀን 1933 ዓ.ም በወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ዋጋውን አገኘ::[16] በዚህ ዓይነት አካባቢው ለአርበኝነት ሥራ ክፍት ተደረገ፤ እነሱም ከመደበኛ ጠላታቸው ጋር ለመተናነቅ ቻሉ።

የንጉሠ ነገሥቱ ጉጃም መግባት እንደታወቀ  አርበኞች ይህንኑ መጋቢት 17 ቀን 1933 ዓ.ም ለሕዝብ በይፋ ገለፁ። ወዲያው የሮቤን ወንዝ ድልድይ ይዘው የጠላትን መኪናዎች በመስበርና ወታደሮቹን በመጨረስ ከባድ ጉዳት አደረሱበት። የጣልያን ጦር ከማሕል አገር ወደ ሰሜን የሸሸው በዚህ በር ነበር። አርበኞችም በየቦታው እየተዘዋወሩ አደጋ ጣሉበት፤ ነገር ግን ሊበግሩት አልቻሉም። አንዱ ሲያልቅ ሌላው ይተካል። አዝማሪና ውሃ ሙላት እንደ ተባለው ተረት ሆነባቸው። የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባን መጋቢት 27 ቀን 1933 ዓ.ም ሲይዝ ደግሞ ወታደር በመኪና እያሣፈረ በማባረር ስለወጋው፣ በዚያ መሥመር የሚጉርፈው የጣልያን ጦር ከመጠን በላይ ሆነ። አርበኛው ይህንን ጦር የማገድ አቅም አልነበረውም። ማገድ አስፈላጊ ሆኖም አላገኘውም፤ ለቀቀው።

በዚህ ጊዜ ጣልያን፣ እሱ ራሱ ከጣርማ በር በጨለንቆ በኩል ሠርቶት የነበረውን የመኪና መንገድ በደናሚት አፈንድቶ፣ እንደ አልነበረ አደረገው። የእሱ ሐሳብ የእንግሊዝን የማባረር ፍጥነት ለመቀነስ ነበር። ግን በቀኛዝማች ታደሰ በላይነህ የሚመራው አርበኛ ይህንን በተመለከተ ጊዜ፣ በጣርማ በር ተራራ ውስጥ ተፈልፍሎ የተሠራውን የመሬት ውስጥ የመኪና መንገድ ለማዳን ወሰነ። ጣልያን ዲናሚት ቀብሮ በማፈንዳት እንዳይዘጋው ተከላከለ። ለዚሁ ሥራ የተሠማሩትን ሠላሣ ስድስት ጣልያኖች በድንገት ደርሶ በመፍጀት ዋሻውን ከመፍረስ አዳነው::[17]



## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 209-219
2. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባላሸኝ ዘመን*፤ ገጽ 31::
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 210-241::
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 210-240፣ 87-94 እና 293::
5. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 241-252::
6. ፈለቀ ዳኜ፣ *5ቱን የመከራ ዓመትና ፍፃሜው፣ አጭር ማስታወሻ*፣ ገጽ 15-18::
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 151-155::
8. ፈለቀ ዳኜ፣ ገጽ 21::
9. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 458-463 እና ገጽ 155-158::
10. ዝኒከማሁ፣ ገጽ 254-264::
11. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 455-480::
12. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 266-267::
13. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 385-388::
14. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 486-488::
15. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 264-270::
16. ዝኒ ከማሁ::
17. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 491-497::

## ምዕራፍ ሠላሣ አንድ
## የጐጃም ጥዝጥዝ

ከጣልያን ወራሪዎች ጋር ትንቅንቅ ከተደረገባቸው አካባቢዎች አንዱ ጐጃም ነው። ይህ ክፍለ ሀገር ትንቅንቅ ያካሄደው ከወራሪው ጦር ጋር ብቻ አልነበረም። በውስጡም ከፍተኛ የአንድነት ማጣት ችግር አጋጥሞት ነበር። ከአጋጠሙት ችግሮች ዋና ዋናዎቹን መመልከት አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣል።

አንዱ የጐጃም ሕዝብ ችግር የልኡል ራስ ኃይሉ አቅዋም ነው። እኝህ ልዑል የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ በመሆናቸው በሕዝብ ላይ የነበራቸው ሚዛን ከባድ ነው። በሌላ ወገን ልጃቸው ወይዘሮ ሰብለወንጌል ልጅ ኢያሱን አግብተው እመቤት ሆይ ዓለም ፀሐይን ስለወለዱ፣ በአማቻቸው ከአልጋ መውረድ ቅር ተሰኝተዋል። በሦስተኛ በኩል ደግሞ ልጅ ኢያሱን ከሰላሌ እንዲያመልጡ አድርገዋል ተብለው ግዞት ተካሂዶባቸዋል፤ ሀብታቸውንም ተወርሰዋል። በአማቻቸው ከአልጋ መውረድ ተቆርቁረው አለመዋጋታቸው ከቁም ነገር አልተቆጠረላቸውም። በአራተኛው ወገን ደግሞ ጣልያኖች ከፍተኛ የሽንገላና የልምምጥ ሥራ አካሄደውባቸዋል። በጐጃም ላይ ሊያነግሡአቸው ቃል ገብተውላቸዋል። በእነዚህ ምክንያቶች ተሸንፈው ልባቸውን ወደ ወራሪው ወደ ጣልያን ሊያዘነብሉ ችለዋል።

የልኡሉ ከጣልያኖች ጋር የውስጥ ስምምነት ማድረጋቸው ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምሥጢር አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ፣ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ይዘዋቸው ከሄዱት መሣፍንቶች አንዱ እሳቸው ነበሩ። ድሬዳዋ አድርሰው ያውርዱአቸው እንጂ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሌላ ክፉ ነገር አላደረጉባቸውም። እሳቸውም ባለፈው ጊዜ የሠሩት ሥራ ሁሉ በደል መሆኑን አምነው፤ ወደፊት በሚቻላቸው ሁሉ እየሠሩ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ የመሐላ ቃል መስጠታቸው አልቀረም።[1] ነገር ግን ከቀድሞ ግብራቸው አልተመለሱም።

ሁለተኛም በደጃዝማች ገሠሠ በለው አሳዳሚነትና መሪነት ከጐጃም ጦር የሚበልጠው ጐንደር፣ ዳባት ከተባለው አገር ከጦርነቱ አስቀድሞ ተመልሶ አገሩ ገባ።[2] ገብቶም የጣልያን ጉዳይ ፈፃሚ ሆነ። የንጉሠ ነገሥቱ የማስፈራሪያ አዋጅ፣ የጳጳሱ የአቡነ ቄርሎስ ግዝት ውጤት ሳይሰጥ ቀረ።

እነዚህ ሁለት ታላላቅ ሁኔታዎች የሕዝቡን አንድነት አላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ኢጣልያ አቀብቁባ ከምትመለከታቸው ግዛቶች አንዱ ጐጃም ነበር። የሀገር ነፃነትን በተመለከተ የሕዝቡ አመለካከት እንደ መሪዎቹ ከጥቅም ጋር የተሣሠረ አልነበረም። ይህም በጠላት ዘንድ ጭምር የታወቀ ነበር።

የጐጃም ሕዝብ በዚህ ዓይነት ዝብርቅርቆሽ ውስጥ እንደአለ፣ የራስ እምሩ ጦር ከሽሬ፣ በጐንደር በኩል ተመልሶ ደረሰ። የጐጃም ሕዝብ እየረዳ፣ ስንቅና ክብት እየሰጠ ሸኘው። ያለ አንዳች ችግር ዓባይን አሻግሮ ወደ ወለጋ



ሸኘው፤ የቻለም አብሮ ሄደ። ይህ አደራረግ ለጣልያኖች አዲስ ምልክት ሰጣቸው። የጐጃም ሕዝብ ልቡ ከሀገሩ ነፃነት ጋር መሆኑን ተገነዘቡ፤ ስለዚህም ራስ ኃይሉን በአክብሮት ያዙ። ከፊትና ከኋላ በሞተር ሳይክል እያጀቡ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ላይ አንፈላሰሰው።

ጣልያን ከጐንደር ወደ ጐጃም በመጓዝ፣ በጎርጎራ በኩል አድርጐ ዞሮ በሚያዝያ ወር ብቸና፣ በጦር ኃይል እየጣሰና መንገድ እየጠረገ አንጀረን፣ ዳሞትን ያዘ። ከዚያም ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ደብረ ማርቆስ ገባ። ከዚያም በየደረሰበት ውጊያ ገጠመው። የጐጃም ሕዝብ ከጠላትና ከግበረ አበሮቹ በየቀኑ የሚንቆረቆርበትን የክህደት ምክር ከምንም ሳይቆጥር ተጋድሎውን ቀጠለ። በከሐዲ መሪዎቹ ምትክ ሌሎች፣ እንደነ በላይ ዘለቀ ያሉ ሀገር ወዳድ ጀግኖችን መረጠ። አዳዲሶቹ መሪዎቹም በመንፈስ እየጠነከሩ ሄዱ። ሀቀኝነታቸውን፣ ለሕዝብ ታማኝ መሆናቸውን፣ ሀገር ወዳድ መሆናቸውን በግብር እያረጋገጡለት ሄዱ። አርበኞችም እስከ ሞት ድረስ ተከተሉአቸው። በአንፃሩ ግን ከሐዲዎቹ በሕዝብ ዘንድ እየቀለሉ፣ በኢጣልያኖችም ዘንድ እየተዋረዱ ሄዱ። ዝርዝሩን ወደፊት እናገኘዋለን።

በጐጃም ምድር የመጀመሪያው የጦር እንቅስቃሴ በግንቦት ወር 1928 ዓ.ም፣ ብቸና ላይ ታየ። በላይ ዘለቀ የተባለ ወጣት፣ በአንድ አደባባይ ላይ፡- "የሀገሬ ሰው ስማኝ! ጣልያን የሚሉት ነጭ ሀገራችንን ሊወር፣ ሚስትህን ልጅህን ሊደፍር፣ ሀብትህን ሊወርስ መጥቶአል። ብቸና ገብቶ መሣሪያ አስረክቡ እያለ ነው" በማለት ከባድ ጠላት መምጣቱን አስረዳ። ከዚያም አያይዞ የራሱን ውሳኔ ሰጠ። መሣሪያውን ለጠላት የሚያስረክበውን፣ ቤቱን እንደሚያቃጥልበት አስታወቀ። በላይ ዘለቀ ይህንን ያህል ታላቅ ውሣኔ ለሕዝብ ያስታወቀው፣ ከአራት መሰል ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ነበር። የጐጃም ጀግና የሐሳቡን ትልቅነት፣ የልቡን ቆራጥነት እንጂ፤ የእሱን ልጅነት አላየም። ብዙዎች ተከተሉት። እንደ አለውም አደረገ።

በዚህም ወቅት ለሀገራችን እንሙት በሚለው እና ለጣልያን ገብተን በሰላም እንኑር በሚለው መካከል ክርክር ተነስቶ ነበር። የክረምቱ መግባት የጠላትን እርምጃ ስለገታው፣ ሕዝብ በጉዳዩ ለማሰብ በቂ ጊዜ አገኘ። ነገር ግን ሕዝቡ ወደ አንድ ሐሳብ መጠቃለል አልቻለም፤ በየሐሳቡ ቆመ። አመንቺም ቀስ እያለ ሐሳቡን በማስተካከል፣ ከሁለት አንዱን ያዘ።

በቁጥር አነስተኛ የሆነው የአርበኛ ቡድን ጠላቱን በድፍረት መቋቋም ጀመረ። ግንቦት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ከደብረ ማርቆስ ወደ ብቸና ይጓዝ በነበረው የጠላት ወታደር ላይ አደጋ ጥሎ አራት ጣልያናውያንና ሁለት ባንዶች ገደለ። አንድ ሌላ ኢጣልያዊ አቆሰለ። ከአርበኞቹም አንድ ሰው ሞተ፤ ሌላ አንድ ሰው ቆሰለ። ብዙ ጠመንጃና ጥይት፣ የእጅ ቦምብ በአርበኞች ተማረከ። ይህ ሁኔታ መሣሪያ መረከብ ያለበት ከጣልያኖች ወደ

ኢትዮጵያውያን እንጂ፣ ከኢትዮጵያውያን ወደ ጣልያን ላለመሆኑ ማስረጃ ሆነ።

ውሎም ሳያድር በረንቲንና ለምጨንን በሚያዋስነው ቀይ ወንዝ ላይ አርበኞች ሌላ አደጋ ጥለው አንድ ጣልያናዊ መቶ አለቃ ገደሉ። ሌሎች ሁለት መቶ አለቆች አቆሰሉ።[3] ጥቂት ጣልያኖችን እየተከተለ የሚግበሰበሰው ባንዳ ብዙ ነው። በተለይም ገበሬው እየተገደደ ስለሚዘምት እሱን መግደል አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ አርበኞቹ ጠዝጥዝ በሚሉት ዘዴአቸው ከሩቅ በመሸመቅ እያነጣጠሩ ነጩን ለይቶ መምታትን ያዙ። ይህም ጥሩ ውጤት ሰጣቸው። ጣልያኖችም በበኩላቸው አዝሚሚያው ስለአሰጋቸው የሽንገላ ሥራቸውን አጠናከሩ።

የ19 ዓመት ዕድሜ የነበረው በላይ ዘለቀ ከስምንት ያልበለጡ የሥጋ ዘመዶቹን ይዞ የሀገር መከላከል ሥራውን ቀጠለ። በብቸና አውራጃ በከና በተባለ ቦታ የጦር ማሠልጠኛ አቋቋመ። ሥልጠናው ልዩ ልዩ መሣሪያዎችና መፍታትና ጠርጐ መልሶ መግጠም፣ አነጣጥሮ በመተኮስ ረገድ ዓይንን ማጥራት፣ ራስን ከጉዳት መጠበቅ፣ ጠላትን ማጥቃትና ይህንን የመሳሰሉትን ዘዴዎቹ ያጠቃለለ እንደነበር መገመት ይቻላል። ሠራዊቱ እየዳበረና ማሠልጠኛው እየጠነከረ ሲመጣ፣ የበላይ ዘለቀ አመራርም እየሠመረ ሄደ። ማሠልጠኛው በስምንት መትረየስና በአርባ ሁለት ወታደሮች በመዓልትና በሌሊት ይጠበቅ ስለነበር አልተደፈረም።

በላይ ዘለቀ መኖሪያውን በዋሻ ውስጥ አደረገ። ዋሻውንም አንድ መቶ ሰባ ምልምሎች እየተፈራረቁ በመዓልትና በሌሊት ነቅተው ይጠብቁ ጀመር። ይህ ጀግና ወጣት ለጦርነት የሚቸኩል አልነበረም። ዝርዝር ጥናት አድርጐ የተሻለውን የማጥቂያ ዘዴ ይመርጣል፤ ሠራዊቱንም በመልካም ምክር ያነሳሳል፤ እነሱም በሙሉ ልብ ይከተሉታል።

የበከናን ጦር ሠፈር ሁኔታ ከአጠና በኋላ ጣልያን ጦር ሠርቶ መጣ። ሐሳቡ በድንገት አደጋ ጥሎ የአርበኞቹን ጀምር በእንጭጩ ለመቅጨት ነበር። ሁኔታውን የተረዳ አርበኛ ለበላይ ዘለቀ ስለነገረው ፈጣን ምክር ተደረገ። አንዱ ሐሳብ ማሠልጠኛውን ለቅቆ፣ ሌላ የተሻለ ቦታ ይዞ መከላከል እንደሚሻል የሚያስገነዝብ ነበር። ነገር ግን በላይ ዘለቀ በዚህ ሐሳብ አልተስማማም፤ ግንባር ለግንባር ገጥሞ መዋጋትን መረጠ። ወደኋላ ማፈግፈግ ያባቶቹን ታሪክ ማስደፈርና ለእሱም ለራሱ ውርደት መስሎ ታየው። ጦሩን በፍጥነት ሰብስቦ "ዛሬ እኛ የኢትዮጵያ አርበኞች በጣልያን ወራሪ ጦር አንገት ላይ የምንቆምበት የተመረጠ ቀን ስለሆነ "...ፀሐይና ጨረቃ እንኳን እኛ ጠላቶቻችንን ትቢያ እስክናደርግ ድረስ በሶማ በረሃ ላይ እንዲቆሙ አዝዣለሁ" ብሎ ከጦርነቱ ገባ። ሠራዊቱም መሪውን በመከተል የመጣበትን ጠላት እንደ ጥሩ ጠጅ አጣጥሞ ጠጣው። አራት መትረየስ፣ ልዩ ልዩ ጠመንጃና ጥይት ማረከ። አርበኛው ልቡ ደነደነ።



ጣልያኖች በሠፈሩባቸው አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ ሁሉ የጣልያንን ምሥጢር እና ሐሳብ እያጠኑ ለአርበኞች ያቀብሉ ጀመር። ጣልያን በከን ከተባለው የጦር ሠፈር የደረሰበትን ወርደት ለመሸፈን ሌላ ጦር አዘጋጀ። ሐሳቡ በብቸና አውራጃ፣ ልዩ ስሙ አቢራ መልክ በተባለው የአርበኞች ሠፈር ላይ አደጋ ጥሎ ለመደምሰስ ነበር። ለዚህም ብዙ ባንዶች ሰብስቦ አሰልፎ ነበር። የጠላት አመጣጥ እንደ ታወቀ በላይ ዘለቀ ሠራዊቱን አዘጋጀ። ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ተኩስ ተከፈተ። ከፍተኛ ውጊያ ከተካሄደ በኋላ፣ ሠማ ነገም የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተማረከ። ብዙ የጣልያን ወታደሮች ሞቱ፣ ቆሰሉ። አያሌ መሣሪያ ተማረከ። ስማ ነገም እናት አገሩን ከድቶ ከጠላት ጐን በመቆም የብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖችን ደም በማፍሰሱ፣ ተፈርዶበት በስቅላት ተቀጣ። በላይ ዘለቀም የተገኘው ድል ለትውልድ የሚሸጋገርና የታሪክ ገጽ ሲያስታውሰው የሚኖር፣ ሕያው ሙያ መሆኑን ገልፆ "...ወራሪ ጠላታችንን ከመላው የኢትዮጵያ ግዛት ላይ ጠራርገን እስክናወድም ድረስ... ሠፊ ትግል ከፊታችን ይጠብቀናል። ...እንደዚህ በፍቅር ተሳስረን መሞት ለኛ ሠርጋችን እንጂ ሞት አይባልም። ሀያውነት ነው..." በማለት ጓደኞቹን ለበለጠ ትግል አነሳሳ።

ጣልያን የአርበኞችን እንቅስቃሴ ለመግታት አለመቻሉ እየታወቀው ስለሄደ፣ ገዥ በሆኑ ቦታዎች ላይ ምሽግ እየሠራ አካባቢዎችን መቆጣጠር ጀመረ። አርበኛው ይህንን ሲያይ ጠላት እሱ እስከ አለበት ድረስ መጥቶ እስኪወጋው መጠበቁን ትቶ ራሱ ጠላት እስከ አለበት ድረስ እየሄደ ማጥቃትን መረጠ።

ራስ ኃይሉን ማባባሉ ውጤት እንደ አላስገኘለት አየ። ራስ ኃይሉም ጣልያን በወገን ላይ የሚያካሄደው ጭፍጨፋ እየጐመዘዘው ሳይሄድ አልቀረም። አለመግባባትም ተፈጠረ፤ ራስም ፊቱን ማኮሳተር ጀመረ። ይህ የሰለቸው ጣልያናዊ አለቃው "ፊትህ የዝንጀሮ ይመስላል" ብሎ ቢያንጓጥጠው፤ ራስ ኃይሉ "የአንተ ደግሞ ቂጥዋን ይመስላል" ብሎ እንደመለሰለት ጉልቶ ይነገራል። ለነገሩ ታላቅ የድፍረት ንግግር ነበር። ስለዚህም ክብሩን እየቀነሰበት፣ በየጦሩ ሜዳ ያዘመተው ገባ። ግን ጦርነቱን በማስታገስ ወይም እሱ ራሱ ሞቶለት ፋታ ለማግኘት የፈለገው አለቃው አንዱን ማግኘት ሳይችል ስለ ቀረ፣ ራስ ኃይሉን በእሥረኝነት ወደ ሮም ላከው።

ጣልያን በዚህ ከላይ በተጠቀሰው ዓላማው መሰረት ደጀን ላይ መሸገ። በበላይ ዘለቀ የሚመራው አርበኛ ከበከና ተወርውሮ በመድረስ ከጥቅምት 1 እስከ 30 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ አንድ ወር ሙሉ ከበቦ ወጋው። ጣልያን መሽጐ የተቀመጠ ከመሆኑ ጋር፣ የነጭ ወታደርና ብዙ ባንዳ ነበረው። በአርበኞች በኩል ለጦርነቱ የተሠለፉት ያን ያህል ብዙ አልነበሩም። የአርበኞች ጥቃት ያስቆጣው ጠላት፣ ከአዲስ አበባ አይሮፕላን እያስነሳ

አካባቢውን አስደበደበ። ቢሆንም አርበኞች አልተበገሩም። ሃያ ሰባት ነጭ፣ በርካታ ሃማሴንና ባንዳ ገደሉ። ከእነሱም ወገን 300 ሞቱ፤ 130 ቆሰሉ። ከዚህ በኋላ አርበኞቹ ወደ ጦር ሠፈራቸው፣ ወደ በከና ተመለሱ።[4]

በሌላው ወገን ደግሞ በቡሬና በዳሞት በኩል የንጉሥ ተክለሃይማኖት የልጅ ልጅ፣ ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ጣልያንን ቀስፈው ያዙት። በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ችግር ስለአልነበረባቸው፣ ሥራቸው ተቃናላቸው። ጣልያንም መሽጐ ከተቀመጠባቸው ቦታዎች ውጭ መንቀሳቀስ አልቻለም። ነገር ግን የጠላት ሐሳብ፣ እሳቸውንም እንደ ራስ ኃይሉ በሽንገላ ወደው እንዲገቡለት ለማድረግ መሞከር ነበርና፣ ያንኑ ከመሞከር አልተቆጠበም።

የበላይ ዘለቀን እንቅስቃሴ በቅርብ ለመመልከትና በተመቸም ጊዜ ለማጥቃት እንዲቀናው፣ ጣልያን ከብቸና ባሻገር ጦር አሠፈረ። ይህ ድግስ ለእነሱ መሆኑን የተረዱት አርበኞች ከጦር ሠፈራቸው ገስግሰው ህዳር 5 ቀን 1929 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። አራት መቶ ባንዶች ደምስሰው የጦር ሠፈሩን አቃጠሉበት።

በታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ሻምበል ደቦኖ በሚባል ጣልያናዊ የሚመራ ጦር ብቸና ገባ። አርበኞች አርገሞር በተባለው ቦታ ስለጉዳዩ ምክር አደረጉ። እንበለው በሚለው አርበኛና የዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ይቃጠልብናል በሚሉት ካህናት መካከል የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ። በላይ ዘለቀ ጉባኤ ሰብስቦ የሁለቱም ወገን ከተደመጠ በኋላ ለካህናቱ ሀሳብ ብልጫ በመስጠት ውጊያው እንዲቀር ተደረገ። ካህናቱም በፊናቸው ከባድ አደጋ ሊጣልበት መሆኑን የሚያስረዳ ወሬ በሚያምነው ወዳጁ በኩል እንዲደርሰው በማድረግ ቦታውን በቶሎ ለቅቆ እንዲሄድ አደረጉ።[5] በካህናቱም በአርበኛውም ወገን የተሰጠው ውሣኔ መልካም ወጤት አስገኘ። ሕዝብም በይበልጥ ከአርበኞች ጋር ተባበረ።

እሳቸውም እንደዚሁ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ችግር ያልነበረባቸው ልጅ /ራስ/ ኃይሉ በለው፣ ደምበጫን ይዘው ጣልያንን መተናፈሻ አሳጡት። የጣልያን ሀሳብ የጐጃምን መሣፍንት ሸንግሎ ወደ እሱ እንዲገቡ ማድረግ ነበርና፣ ከጠላት ወገን የሚሠነዘርባቸው ጥቃት እምብዛም መራር አልነበረም።

ፀጋ ዳሞትን፣ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ኃይለ ኢየሱስ የሚመራው አርበኛ ተቆጣጠረ። ጠዝጥዝ በተባለው የሽምቅ ጦርነት በየቦታው የጣልያንን ጦር ይጠዘጥዘው ጀመር።

ደጃዝማች /ቢትወደድ/ መንገሻ በሕመም ምክንያት እያደረጉ ከጠበል ወደ ጠበል፣ ከአገር ወደ አገር እየተዘዋወሩ ሕዝብ ከአሳበሩ በኋላ፣ ዴንሣ በተባለው አገር ጦር ማንቀሳቀስ ጀመሩ። ሰኔ 19 ቀን 1929 ዓ.ም በዚሁ በተጠቀሰው ቦታ ጣልያንን ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት። ባለቤታቸው ወይዘሮ ሰብለ ወንጌል ኃይሉም ባላቸው የአባታቸውን የራስ ኃይሉን ዓላማ



እንደማይከተሉ ቁርጡን አወቁት። ጠላት ሕዝቡ እንዳልተገዛለት ባወቀ ጊዜ ቤቱን ማቃጠል፣ ከብቱን መዝረፍ ያዘ። በደጃዝማች /ቢትወድድ/ መንገሻ ጀምበሬ የሚመራው አርበኛ መልካና ዴንሣ፣ ደድቤ በተባለው ቀበሌ በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም ጠላትን ግንባር ለግንባር ገጦሞ ተዋጋው።

አንድ የአርበኞች ቡድን ከጉንደር፣ ከሰማዳ ወደ ጐጃም ተሻግሮ በዚያ ከነበሩ አርበኞች ጋር ተቀላቀለ። ከዚያም ነሐሴ 7 ቀን 1929 ዓ.ም ሾተል ማጠቢያ ከተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ተዋግቶ፣ ጠላትን ወደ መጣበት ወደ መርጦለማርያም አባረረው። ነሐሴ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጐምት በተባለው ቦታ አርበኞች ከጠላት ጋር ጦርነት አካሂደው ብዙ ጉዳት አደረሱበት። በእነሱም ላይ ግን ጉዳት ደረሰ፤ ብዙ ጀግኖች ወደቁ።

አርበኝነትን ለማጠናከር ከሚረዱት ዘዴዎች ዋነኛው በየቤተክርስቲያኑ ክብረ በዓል በሚደረግበት ጊዜ ለሕዝብ ንግግር በማድረግ ምክር መስጠት ነበር። በዚህ መሠረት ደጃዝማች /ቢትወደድ/ መንገሻ ጀምበሬ ነሐሴ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ዴንሣ በተባለው አገር ፣ በክበረ በዓል ላይ ለሜጫ፣ ለዴንሣ፣ ለአገው ምድር፣ ለአቸፈር፣ ለጐታና ለሰከለ ሕዝብ ንግግር አደረጉ። በንግግራቸውም ጣልያኖች በሕዝብ ላይ የሚፈፀሙትን ግፍ ዘረዘሩ። በአንድ ሕፃን ማሳደጊያ ጉዳይ የተጣሉ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለዳኝነት ቢቀርቡ፣ የባህር ዳሩ አገረ ገዥ ሕፃኑን በሽጉጥ ጥይት እንደገደለ፤ ጐንደር ከጣና ባህር ዳርቻ፣ ቅራጠ ከተባለው ቦታ ካህናቱን በመትረየስ ፈጅቶ ቤተክርስቲያኑን በእሳት እንደአቃጠለ፤ ያለአንዳች ጥፋት 5 ሰው እንደሰቀለ፤ አባ ተስፋ ማርያም ቆተባሉትን መነኩሴ ከነነፍሳቸው ሳይሞቱ እንደቀበረ፤ ሀሳቡ ሕዝቡን በባርነት አስገድዶ፣ ለባዕድ ባንዲራ አስግዶ፣ ሃይማኖትን አስክዶ ለመግዛት መሆኑን ዘርዝረው አስረዱ። ሕዝቡም አምርሮ ተከተላቸው።

የህዝቡን ትብብር በዚህ አይነት ካጠናከሩ በኋላ፣ ፈቡዕ ገበያ ከሚባለው ቦታ ሠራዊታቸውን ልከው በጣልያን ላይ ጦርነት አካሄዱ። የአራት ሻለቃ ጦር አውድመው፣ አንድ ሻለቃና አንድ መቶ አለቃ፣ ከ80 መትረየስና ከብዙ ጠመንጃ ጋር ማረኩ።[6]

ልጅ /ራስ/ ኃይሉ በለው የጠላትን ጦር በደምበጫ አካባቢ አላፈናፍን አሉት። በፊታውራሪ አያሌው መኰንን የሚመራው አርበኛ በባህር ዳር አካባቢ ያለውን ያዘ። ልጅ /ደጃዝማች/ በላይ ዘለቀ ብቸናንና እስከ ደጀን ድረስ ያለውን፤ አልፎ፣ አልፎ እስከ ደብረማርቆስ አካባቢ እየተጠጋ አስቸገረው። ዳንግላ የደጃዝማች /ቢትወደድ/ መንገሻ ጀምበሬ ሆነ። ፊታውራሪ አያሌው መኰንን ባህር ዳርን ያዙ። ፊታውራሪ ዘለቀ ብሩ የፍኖተ ሰላምን አካባቢ ድርሻቸው አደረጉ። ቡሬን የደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ሠራዊት ተቆጣጠረው። ፊታውራሪ ታፈረ ዘለቀና ወንድሞቻቸው የበለስን ወንዝና ዝብስትን ተቆጣጠሩ። ልጅ አደራ ደብረ ማይን ያዙ። በልጅ ደምሴ ዓለማየሁ የሚመራው አርበኛ በዳሞትና በሞጧ፤ በፊታውራሪ በየነ በሻው የሚመራው

በማቸከል የጠላትን ጦር ጠዘጠዘው። ሕዝብ ለአርበኞች የሚሰጠው ድጋፍ ቀስ በቀስ አደገ።

የ1929 ዓ.ም ሁኔታ በዚህ ዓይነት አልፎ የ1930 ዓ.ምቱ ትግል ተደቀነ። በጥቅምት ወር 1930 ዓ.ም ከደጉማ የተነሣው የጠላት ጦር ዘዝ ለመድረስ ሲሞክር አርበኛው ውጊያ ገጠመው። ከበለስ እስከ ቀላይ እየተከታተለ ወጋው። ነገር ግን አወዳደቃቸው የአርበኛውን ልቦና አላደከመውም።[7] በወቅቱ የጐጃሞች የውጊያ ስልት "ጠዝጥዝ" የሚባለው እንደመሆኑ፣ በየሄደበት እየተከተሉ ማጥቃትና መሣሪያ መቀማት የተሻለ ዘዴ ሆኖ ተገኘ።

የጠላት ጦር የበከናን የአርበኞች የጦር ሠፈር ለማውደም ከጅሎ እንቅስቃሴ አደረገ። አርበኞች ሁኔታውን አስቀድመው አውቀው በመረዳት፣ ታህሣሥ 4 ቀን 1930 ዓ.ም ተንቀሳቅሰው የጠላትን ጦር ከቀለበት ውስጥ በማስገባት በጨበጣ ውጊያ እረፈረፉት። ሁለት መቶ ወታደሮች ደመሰሱ፤ ሌሎች ሃምሣ አቆሰሉ። አምስት መትረየስ፣ ሁለት መቶ ሃምሣ ጠመንጃ ከአሥር ሺህ ጥይት ጋር ማረኩ። በአርበኞች ላይ ግን ምንም የረባ ጉዳት አልደረሰም። በዚህ ዓመት ታህሣሥ 7 ቀን በብችና አውራጃ፣ ልዩ ስሙ ሙጋ በተባለ ቦታ የነበረውን የጠላት ጦር ሠፈር አቃጠሉ። በዚህም ሦስት መቶ ወታደሮችና ብዙ መሣሪያ አጋዩ፤ ሌሎች ሁለት መቶ ባንዳዎችም ማረኩ።[8]

የጐጃም አርበኞች በዚህ ላይ እንደአሉ፣ የሸዋ አርበኛ በወሊጋ በኩል ዞሮ፣ ዓባይን ወንዝ ተሻግሮ የካቲት 19 ቀን 1930 ዓ.ም ቡሬ ከተማ ገባ። የሸዋን ሠራዊት ካህኑ በንሴብሆ፣ ወንዱ በሆታ፣ ሴቱ በእልልታ ተቀበለው። ደጃዝማች ነጋሽም፣ ነፍስን በሚመልስ ምግብ በረሃ የጎዳውን አርበኛ ነፍስ ዘሩበት። ታላቅ ደስታ ሆነ።

ይህም ስለተባለ ስጋት አልቀረም። ጠላት ኃይሉን በዚያው መጠን እንደሚያጠናክር፣ ጦርነቱም ከባድ እንደሚሆን፣ ሳይታለም የተፈታ ነበር። ጣልያንም እንደዚሁ አደረገ። ጄነራል ጋሊኒን የበላይ አዛዥ አድርጐ፣ ከሸዋና ከጐንደር ሃምሣ ሺህ ጦር አመጣ። አርበኞችን ለማጥቃት ጣልያን ከአንጀባራ ምሽግ መንቀሳቀስ ጀመረ። አካሄዱ ቤት እያቃጠለ፣ ሀብትና ከብቱን እየዘረፈ፣ ወንድና ሴት ሳይለይ ሰዉን እየፈጀ መሆኑ ቀደም ብሎ በፈፀመው ግብር ተረጋግጦ ነበርና፣ ዝም ብሎ መጠበቅ ሀገሩን ማስጠፋት ሆነ። ስለዚህ ወሬው እንደተሰማ አርበኛው ከቡሬ ተነስቶ የካቲት 26 ቀን 1930 ዓ.ም በግስጋሴ ከአንጀባራ ምሽግ ጥግ ድረስ ወጥቶ፣ ከወዲያ ወዲህ በመዘዋወር ተጠባበቀው። ጣልያንም የአርበኛውን ጥንካሬና ቁርጠኝነት ሲረዳ ተመልሶ ወደ ምሽጉ ገባ።

ጣልያን ከሸዋ፣ ከጐንደር፣ ከባህር ዳርና ከዳንግላ ጦር ወደ ሰከላ አዘመተ። አርበኛውም ከግምጃ ቤት ገስግሶ በመሄድ አድም ከተባለ ቦታ ሆኖ



ጠበቀው። መጋቢት 11 ቀን 1930 ዓ.ም በደጃዝማች ነጋሽ የታዘዘ ቡድን ሄዶ ገጠመው። በዚህ ውጊያ የጠላት ጦር ሲያመዝን፣ የሸዋው ጦር ደርሶ ከጠላት ጦር 300 የሚያህለውን በቅጽበት አረገፈው። ጠላት አይሮፕላን አስመጥቶ ቢያስደበድብም አርበኛው አልተበገረም። በሃምሣ ሺህ የሚገመት ጠላቱን በ700 ቤልጅግ ጠመንጃና በ1 መትረየስ አባረረው። በተከታታይ የመጣውን የጠላት ጦር መጋቢት 17 እና 18 ቀን 1930 ዓ.ም ሜጫና አቸፈር ላይ ወግቶ ጉዳትም አደረሰበት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በደጃዝማች ነጋሽና በወይዘሮ ሰብለ ወንጌል መካከል ቅያሜ ተፈጠረ። እነ ደጃዝማች ገሠሠ ከድተው ከጦር ግንባር በተመለሱ ጊዜ የሸዋ ጦር እንደወጋቸው እየተደረገ ተነገረ። የራስ ኃይሉም ተፅዕኖ በረታ። በዚህ ምክንያት አርበኛው በጦር ላይ ነገር ተጨመረበት። ይህም ሆኖ የጐጃም ሕዝብ ድጋፉን አልቀነሰበትም። የሀበሻ ልብ ይከፋፈል እንጂ፣ በወራሪው ጣልያን ጉዳይ ልቡ አንድ ነው።

ጄነራል ጋልያኒ ጦሩን እንደገና አሰባስቦ አንጀባራ ከተባለው ምሽግ ገባ። አርበኛውም በበኩሉ ፈጠም ከተባለው ወንዝ ላይ ምሽግ ሠርቶ ጠበቀው። ጣልያን አርበኞች የነበሩበትን አካባቢ በአይሮፕላን ከአስደበደበ በኂላ ጉዞ ጀመረ። ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ባላገር አርበኞችን ከጀርባቸው ለመውጋት መከጀሉ ስለታወቀ ከጣልያን ጋር ግንባር ለግንባር መግጠም የማይጠቅም ሆነ። ስለዚህ ጋልያኒ ሰተት ብሎ ቡሬ ከተማ ገባ። ከዚያም ጉዞውን ወደ ጐጃም ቀጠለ። በዚህ ሁኔታ አርበኛው ተበሳጨ። መጋቢት 18 ቀን 1930 ዓ.ም ኢማሎግ ላይ የተደረገው ውጊያ ሳይመልሰው ቀርቶ፣ ቡሬ ድረስ ሄዶ ገጠመው። አንድ ሻምበልና ብዙ ነጮች፣ ብዙ ባንዳም ገደለበት።

ከአርበኞች የነበረውን አማኔ የተባለውን ሀገር ጣልያን ሚያዝያ 20 ቀን 1930 ዓ.ም ሙሉ ቀን በአይሮፕላን ደበደበው። ብዙ ጉዳትም አደረሰ። ስለዚህ አርበኞቹ ጠልያ ወደ ተባለ ቦታ፣ ከዚያም ወደ ወንበራ ተጓዙ። ጣልያንም በሌሊት ጭምር አደጋ በመጣል ጉግሣ እስከተባለው ቦታ ድረስ ተከታተላቸው።

ጠላት አለፋ ኳኳ በተባለው ቀበሌ በነበሩ አርበኞች ላይ በ1930 ዓ.ም አደጋ ጣለ። አርበኞች ለመካላከል ቢሞክሩም መቋቋም አልቻሉም። መሪአቸው ልጅ አበራ በሪሁን በሮምታ በተተኮሰባቸው ጥይት ተመትተው ወደቁ። ሚስትየዋ ተተክተው ሲያዋጉ እሳቸውም ተመትተው ወደቁ። ጠላት የባልና ሚስቱን ራስ ቆርጦ አለፋ በመውሰድ ጊጤ ተጫወተበት። የአለፋና የአቸፈር አርበኞች ይህንን ሲሰሙ በፍጥነትና በእልህ ተንቀሳቅሰው፣ የይስማላን ምሽግ መይመዱን አጠፉት።

በዚህም ጊዜ ላይ በአርበኛው መካከል እንደገና የሀሳብ ልዩነት ተቀሰቀሰ። ፍሬ ነገሩ እንሰደድ፤ እዚሁ እንዋጋ የሚል ነበር። የሸዋው እንጂ የጐጃሙ አርበኛ የስደት ፍላጐት ሊልነበረውምና፣ ከደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ

ፈፋ ከተባለው ቦታ ዝም ብለው ተለዩ። የሸዋው ቡድን ጉዞውን ቀጥሎ ግንቦት 16 ቀን 1930 ዓ.ም ወንበራ ገባ። ወንበራ ላይ ምክር ተደርጎም አንዱ ወገን ወደ ሱዳን ጠረፍ እንሂድ አለ። የሰጠውም ምክንያት ሥራችንን እና ሁኔታችንን ለማስታወቅ፣ እርዳታና አመራር ለማግኘት የሚል ነበር። እንዲሁም ከደረሰበት ቅጥቃጤ ጥቂት ዕረፍት ለማግኘትና የቆሰለው፣ የታመመው እንዲታከም የሚል ስለነበረበት፣ ወደ ሱዳን መሄድን የመረጠው በዛ። ሌላው ወገን ደግሞ ክፉውንም፣ ደጉንም በሀገሬ በረሃ እቀበለዋለሁ እንጂ ወደ ባዕድ አልሄድም ባይ ሆነ። ዕርቅ የማይቻል በመሆኑም፣ እያንዳንዱ እንደ ፍላጎቱ እንዲያደርግ ስምምነት ተደረሰ። ሚያዝያ 27 ቀን 1930 ዓ.ም ከሸዋ አርበኛ የሚበልጠው ተገምሶ ወደ ጠረፉ ለመሄድ ተነሣ።

የአርበኞችን መለያየት ጣልያን ደርሶበት ነበርና፣ በሀገር ውስጥ ለመዋጋት ባሰበው አርበኛ ላይ ከፍተኛ ክትትል አደረገ። ወደ ሸዋ ተመልሶ እንዳይገባ መንገዱን አጠረበት። ምንም ከጐንደር፣ ከሞጣና ከወለጋ የተሻገረው፣ ከዚያው ከጐጃም ከተውጣጣው ጦር ጋር በመተባበር ቢሆን፤ እነደጃዝማች ገሠሠ በከዱ ጊዜ ተዋግቶ ነበርና ለሸዋ ሠራዊት በጐጃም ምድር አርበኝነት መቀጠል የማይሆንለት ሆነ። የሀገሬውም አስተሳሰብ ተከፋፈለ። ባላገሩ ሀብቱን፣ ንብረቱን ለመጠበቅ ሲል ወደ ጠላት (ወደ ሠላማዊነት) አዘነበለ። አርበኛውም እየጐጠ ገባ። ከሸዋ የተሻገረው ከዚያ መቆየት የማይሆንለት ሆነ። ስለዚህ እንደገና ወደ ወለጋ ተመልሶ ለመሻገር ወስኖ ጉዞውን በግስጋሴ ቀጠለ።

ሚያዝያ 30 ቀን 1930 ዓ.ም እሑድ ከዓባይ አፋፍ ሲደርስ ጠላት ቀድሞ ሲጠብቀው አገኘ። ይህንን በር አርበኛው በኃይል ሰብሮ ማለፍ ስለነበረበት፣ በብርታት ተዋግቶ ጐራውን በማስለቀቅ ከወንዙ ገባ። በዚህ ጊዜ ከጐጃም ወገን አዲስ የጠላት ጦር ደረሰበት። ከወለጋ ወገን ደግሞ ሌላ ጦር መጣበት። ሁለቱንም እየተከላከለ ወንዙን ተሻግሮ ወደ ግንደበረት የሚያደርስ መንገድ ያዘ። በጦርነቱም፣ በውሃውም ብዙ ሰው አለቀበት።[9] ወደ ግንደበረት የሚወስደውን መንገድ ትቶ ወደ ወለጋ በረሃ ለበረሃ በመጓዝ፣ ለሀገሩ ሲል በፈቃዱ ከመረጠው ሥቃይ ውስጥ ገባ። ምክንያቱም ግንደ በረት በከባድ የጠላት ጦር ተይዞ ነበርና።

ሌላኛው፣ ወደ ሱዳን የሚሄደው ቡድን፣ ዝግጅት አድርጐ ጉዞውን ቀጠለ። ከዝግጅቱ ዋነኛው ቀኛዝማች እጅጋ ከተባለው ሰው ጥቃት እንዳይደርስበት መጠንቀቅ ነበር። ይህ ሰው ልቡን ከጠላት አፉን ከአርበኞች አድርጐ፣ ምቹ ጊዜ በመጠበቅ ላይ ነበር። ይህንን ሁኔታ አርበኞቹ ተረድተውት ነበርና፣ ወደ ሱዳን በሚሄዱበት ጊዜ እጁን ይዘው ጉዞ ጀመሩ። ሀገሬውም ሊያድነው፣ ጣልያንም ሊደርስለት አልቻለም። እሱም ይህንን በተረዳ ጊዜ በደሉን አምኖ፣ በመሐላ እርቅ ሆኖ፣ ተለቀቀ። የታመነ መሪ



ሰጥቶ ሸኛቸው። አርበኛው በሰላም መንገዱን ቀጥሎ ግንቦት 26 ቀን 1930 ዓ.ም ከተመኘው ከሱዳን ጠረፍ ደረሰ።[10]

ጣልያን በጐጃም ያሉ አርበኞችን ለማጥፋት በማሰብ በዋና ዋናዎቹ ላይ ማለሙን ቀጠለ። ልጅ በላይ ዘለቀ በዲማ ጊዮርጊስ፣ አቤ በተባለው ዋሻ ሱባኤ በያዙበት ጊዜ፣ አደጋ ጥሎ ለማጥፋት ከበባ አደረገ። እሳቸው ግን ከበባውን በኃይል ሰብረው በመውጣት አመለጡት። ለምጨን በተባለውም ቦታ እንደዚሁ ሆነ። ከዚህ በኋላ በበላይ ዘለቀ ሠፈር ምክር ተደረገ። የአርበኛውን ኃይል የሚያጠናክርና ለሥምሪቱ ሥምሪት የሚሰጥ ድልድል ተሠራ። እስከ ደጃዝማች ድረስ ሹመት ተሰጠ። ለእያንዳንዱ እንደሙያው፣ እንደጀግንነቱ ሹመት ሰጡ። ሁሉን ለእኛ ሰጠህ ለአንተስ ምን ቀረህ? ተብለው ቢጠየቁ፣ እናቴ "በላይ ብላኝ የለ" አሉ ይባላል።

በድልድሉ መሠረት አርበኛው በአሥራ አራት ደጃዝማቾች፣ በአምስት ፊታውራሪዎች የሚመራና አንድ በጀሮንድ ያለው ሆነ። ይህም ድልድል ሠራዊቱን አጠናከረው። እንግማ በረንታ፣ እናርጅ እናውጋ፣ ጉበያ ሊበን፣ ቁንባት፣ አዋባል፣ ናይጭ የተባሉትን አምስት አካባቢዎች በቁጥጥር ሥር አዋሉ። የእሳቸውም የጦር ስም አባ ኮስትር ሆነ።

ጫኔ ተረፈ የተባለ ሰው ከአርበኞች ከድቶ ለጣልያን ገባ። ከዚያም ግብረ አበሮቹን ይዞ በደጀን ወረዳ፣ ልዩ ስሙ ሸበል በረንታ በተባለ አካባቢ ከዋሻ ገባ። ይህ ሰው የአርበኞቹን ምሥጢር ያውቅ ስለነበር፣ ጠላትነቱ አደገኛ ሆነ። አርበኞች በነሐሴ 1930 ዓ.ም ከበባ አድርገው ሊያጠቁት ቢሞክሩ ሳይሳካላቸው ቀረ። አደሙ የተባለውን አርበኛ ገድሎ አመለጠ። ይህ እንደ ተሰማ በላይ ዘለቀ ጦራቸውን ይዘው ገስግሰው በመድረስ፣ ነሐሴ 29 ቀን 1930 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። በተካሄደው ውጊያ ጫኔ ቆስሎ ሲያመልጥ፣ ብዙ ግብረ አበሮቹ ሞቱ። ሁለት መቶ ሰማንያ ጠመንጃና አራት መትረየስ ማርከው ወደ ጦር ሠፈራቸው፣ ወደ በከና ተመለሱ።

በዚሁ በ1930 ዓ.ም ወረካዩ ከተባለው ቦታ ላይ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። የበላይ ዘለቀ ባለቤት ወይዘሮ ሸክሚቱ ዓለማየሁ ከሃምሣ አርበኞች ጋር ወደቁ። በአባ ኮስትር በላይ ዘለቀ የሚመራው አርበኛ፣ በዚሁ በነሐሴ ወር 1930 ዓ.ም ደብረ ወርቅ ጨጨ፣ አያልፉሽ ከሚባል ቦታ በጣልያን ላይ አደጋ ጣለ። ከማታው 12 እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት በተደረገው ትንቅንቅ አንድ መቶ አለቃና ሠላሣ ሦስት ጣልያናዊያን ወታደሮች ከብዙ ባንዳ ጋር ተደመሰሱ። አንድ ቢዘንቲ የውሃ መትረየስ፣ ሃያ ሁለት አልመን መትረየስና ሰማንያ ሁለት ጠመንጃ ከእነጥይቱ ተማረከ።

የአርበኛውን ቡድን እናወድማለን በማለት እየፎከረ፣ ከደብረ ማርቆስ አንድ ክፍለ ጦር ተንቀሳቀሰ። በበላይ ዘለቀ የሚመራው ሠራዊት እነብሴ ከተባለው ቦታ አንጥፎ ጠብቆ አመድ አደረገው። የተረፈው የጠላት ጦር ቅስሙ ተሰበረ፤ ፎክሮ ከወጣበት ከተማ ተሸልኮ ገባ።

የሆነለት መስሎት ጣልያን ወደ ኮስታራው ወደ በላይ ዘለቀ መልዕክተኞች ላከ። መልእክቱም እሱ ልጃቸውን ከእሥራት ሊፈታላቸውና የጐጃምን ገዥነት ሊሰጣቸው ቃል የሚሰጥና፣ በላይ ዘለቀም በሰላም እንዲገቡለት የሚጠይቅ ነበር። ኮምጣጣው በላይ ዘለቀ ግን "...እናት አገሬን ለጥቅም መሸጥ...የሞት ሞት ነው..." በማለት መልእክተኞቹን ለፍርድ አቀረቡአቸው። የጣልያን መልእክተኞች ሆነው የመጡት ሁለት ሹማምንቶች ብዙ አርበኞችን ያስጨፈጨፉ ነበሩና፣ ሠራዊቱ ይሙት በቃ እየፈረደ በስቅላት እንዲቀጡ ወሰነ። እጅጉ ለማ እና አደራ ያለው ወዲያው የእርቅ ጥያቄ ላቀረበላቸው ጣልያን ከመልእክተኞቹ ጋር በላከው አስተርጓሚው እጅ የመልስ ደብዳቤ ፃፉለት። ቃሉም "...ወደድክም ጠላህም ጐጃም የራሴ አገር ነው።...እናት አገሬን ኢትዮጵያን በአንድ ልጇ አልለውጣትም።...የተወለዳችሁበትን ቀን እንድትረግሙ ያደረግን ጀግኖች መሆናችንን እራስህ አትክደውም..." የሚል ኃይለ ቃል ነበረበት። ከዚህም በስተቀር ደብዳቤው በዚያው ቀን ብቸና አቅራቢያ የነበረውን ምሽግ የሚደመስስ ሠራዊት መላኩን የሚገልጽ ነበር። የብቸና ምሽግ ዕለቱን ተደመሰሰ። ሁለት መቶ የጠላት ወታደሮች ሞቱ፣ ሃምሣ ቆሰሉ፣ አንድ መቶ ተማረኩ፣ ምሽጉ ተዘረፈ። ልጅቱን ደግሞ ልመንህ ዋጋዬ የተባለው የደብረ ማርቆስ የወህኒ ቤት፣ ሰርቆ ቦክና በመውሰድ ለአባትዋ አስረከበ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ ሚያዝያ 23 ቀን 1931 ከሱዳን ተመልሰው ጐጃም ገቡ። የመጡበትም ለጐጃም ሕዝብ ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተላከ መልእክትና የመልእክት ማስተላለፊያ ሬዲዮ ይዘው ነበር። ሬዲዮውም ሰከላ፣ ሣንጌ ከተባለው ቦታ ተቋቁሞ ሥራ ጀመረ። ይህንን ያየ ባንዳ ከጣልያን እየከዳ ከአርበኞቹ ጋር መቀላቀል ጀመረ። ሻለቃ /ራስ/ መሥፍንም ከደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ጋር በአገው ምድር በደጋ ዳሞት፣ በሰከላ፣ በጣሊያ፣ በልጀምበራ፣ በአዴት፣ በሜጫ፣ በአቸፈር፣ በጉታ እየተዘዋወሩ ሕዝቡን አስተባበሩ። ሕዝቡም በየሥፍራው ያደፈጠውን የጣልያን ጦር ከተሸሸገበት ምሽግ እየቀሰቀሰ ያሰቃየው ጀመር።[11]

ከሱዳን ጠረፍ የሚሰማው ወሬ የሕዝቡን ልቡና የሚቀሰቅስ እየሆነ ሄደ። ይህ ሁኔታ ጣልያኖችን አሰጋቸው። በእሥራት ስም ወደ ሮም የተወሰደውን ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትን ጣሊያኖች መልሰው አመጡት። ከአርበኞች ጋር በሚደረገው የእርቅ ንግግር፣ በሽምግልና እንዲገባ አደረጉት። ይህም እንደ አልሠራና ሁኔታው እየከበደ እንደሄደ ሲረዱ፣ ድርሻውን እንዲወጣ ወደ ጐጃም መልሰው ላኩት። ጣልያኖች በጐጃም ሕዝብ ላይ የመደለያ ወሬ አዘነሙበት። ጠላት በያለበት መግለጫ መስጠት፣ አዋጅ ማውጣት ያዘ። ለምሣሌ ግንቦት 10 ቀን 1931 ዓ.ም ጀነራል ሊዊጂ ፍሩሺ ባወጣው ቃል "የጐጃም ሕዝብ ስማ ስማ" በማለት ይጀምርና "በሀሲናዬ ሁሉ እንድትታዘዙና እንድትገቡ ብጣጣር...አልሰማኝ አላችሁ..." በማለት ይማረር



እና፣ አሁንም እንዲገቡለት ልምምጡን ይቀጥላል። ነገር ግን የጐጃም ሕዝብ፣ ጠላት ልምምጥ ያበዛው እሱን ወድዶት ሳይሆን ተጨንቆ መሆኑን አወቀ።

ጣልያን በአማራው ሕዝብ ላይ የሚያካሂደውን ውትወታ በመቀጠል ነሐሴ 17 ቀን 1931 ዓ.ም ሌላ አዋጅ አወጣ። ይህ ደግሞ መሬት የሕዝብ መሆኑን መንግሥት በትክክል እንዳአወቀ፣ ጭቃ አበሉን እንዲቀበል፣ የወረዳ ገዥ ለመንግሥት ከሚገባው ከአሥር እጅ ሁለቱን እንዲወሰድ፣ ዳኝነትና አፈርሣታ እንደ ጥንቱ እንዲሆን፤ የነጭ፣ የጥቁር ማር፣ የምልምል፣ የበሬ ጫንቃ፣ የጢስ ጨው፣ የዓመት በዓል፣ የደምበኛ /የጦም/ ቆሎ እንደተፋቀ የሚገልጽ እና አማኝ የሆነ እስከ ጥቅምት 15 ቀን 1932 ዓ.ም ቀርቦ እንዲመዘገብ የሚያዝ ነበር። ይህንን ያላደረገ ከርስቱና ከጉልቱ እንደሚነቀል የሚገልጽ ነበር። ግን ይኸም እንደሌሎች አዋጆች ውጤት አልሰጠም።

የ1931 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ 1932 ዓ.ም ባተ። ህዳር 12 ቀን 1932 ዓ.ም ከእንጀባራና ከቡሬ የጠላት ጦር ተንቀሳቀሰ። ዓላማው አሁንም አርበኞችን ለማጥፋት ነው። አርበኞች ፈጣም ከተባለው ወንዝ ላይ ገጠሙት። ውጤቱ ለጠላት ፈጣን ሆነበት። አንዱ ዋና የፍልሚያ ቦታ አቸፈር ሆነ። ጣልያኖች ባወጡት የጦር ማስታወቂያ፣ ይህ ቦታ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል። በዚኅ ሽሞን የአውሮፕላን ጦርነት እየተጋጋመ ሲሄድ፣ ከእሱ ጋር በማስታከክ በአማራው አገር ስለሚካሄደው ጦርነት መግለጫ ያወጡ ጀመር።[12] ይህ ደግሞ ለአርበኛው የልብ ልብ ሰጠው። ትግሉን በበለጠ ብርታት ቀጠለ።

በኰሎኔል ቶሌራ የሚመራ የኢጣልያን ጦር መጣ። አርበኞችም ጳጉሜ 5 ቀን 1932 ዓ.ም አቸፈር፣ ዝብነት ላይ ገጠሙት። ከሱዳን በአዛዥ ከበደ ተሰማ አስተዳዳሪነት፣ በብርጋዴየር ሳንድፎርድ መሪነት የመጣው የእንግሊዝ ነፃ አውጭ ጦርም በውጊያው ለመጀመሪያ ጊዜ ተካፋይ ሆነ። ጣልያን በአለው መሣሪያ ሁሉ ድብደባ አካሄደ። ነገሩ ግን ውጤት አላስገኘበትም።

ከዚህ በኋላ ወሣኙ የ1933 ዓ.ም ፍልሚያ ተጀመረ። የጐጃም አርበኛ ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው መመሪያ መሠረት መሥራት ጀመረ። በዚህ ግንባር የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል አዛዥ ከበደ ተሰማ ሲሆኑ፣ በእንግሊዝ በኩል ብርጋዲየር ሳንድፎርድ ነበሩ። ሆኖም ከእንግሊዝ ወገን የሚሰጠው አመራር የእነሱን የበላይነት የማጠናከር ባህርይ አመጣ። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያውያኑ በኩል ቅሬታ ስለአስከተለ፣ በሀገር ውስጥ ዘዴ መሥራት ግድ ሆነ። ለማጥቃቱ ሥራ አዲስ ድልድል ተሠራ። በድልድሉም የአቸፈር ጦር በፈታውራሪ አያሌው መኰንን እየተመራ እስከ አለፋ ድረስ እንዲገባ ተመደበ። የጉታ፣ የሰከላና የአንሹሽ አርበኛ በደጃዝማች መንገሻ መሪነት በስተግራ በኩል እንዲያጠቃ ተወሰነ። የኪኰራና የደርቤቲ አርበኛ በእነ ፊታውራሪ አደመ አስተባባሪነት የፈንግላን ምሽግ ከብቦ እንዲያጠቃ ታዘዘ።

ባህር ዳር የነበረው የጣልያን ጦር እንዳያመልጥ የሚጫ በር በአራት ፊታውራሪዎች በሚመራ የአርበኛ ሠራዊት እንዲታጠር ተደረገ። በዚሁ በታሰበው ዓይነት ተፈፀመ። ይኼኛው ሥልት በሀገር ውስጥ የጦር ዘዴ የተቀመመ በመሆኑ፣ ጥሩ ውጤት አስገኘ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ስለሚገቡበት በር በአርበኛውና በነፃ አወጭው ጦር መካከል ምክር ተደረገ። ዝርዝር ጥናት ከተካሄደ በኋላ፣ በወንበርማ በኩል እንዲገቡ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ሃሣቡም በአዛዥ ከበደ ተሰማ ፊርማ ጥቅምት 4 ቀን 1933 ዓ.ም በተፃፈ ማስታወሻ ለንጉሠ ነገሥቱ ተላከ። ወንበርማ ለንጉሠ ነገሥቱ መግቢያ እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያት፡-

1ኛ.ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ያለበት በመሆኑ ለጠላት አይሮፕላን አደጋ አለማስጋቱ፣

2ኛ.የጠላት ጦር ገብቶ እንዳያጠቃ ለማገድ ምቹ በመሆኑ፣

3ኛ.ቀደም ብሎም የጠላት ጦር ሊገባ ሞክሮ ተሸንፎ የቀረ በመሆኑ፣

4ኛ.ለእንግሊዝ አይሮፕላን ማረፊያ የሚሆን ሠፊ ሜዳ መኖሩ፣

5ኛ.ክባቢው የዓባይ ወንዝ በመሆኑ ሊሻገር አለመቻሉ፣ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱም ሃሳቡን ስለተቀበሉ፣ ዝግጅቱ ቀጠለ። ለአርበኞች የትብብር መጠየቂያ ደብዳቤዎች በየአስተባባሪዎቻቸው ስም ተፃፈ። አብዛኛው በአዛዥ ከበደ ተሰማ የተፈረመ ሲሆን፣ አንዳንዱ በንጉሠ ነገሥቱ የተፈረመ ነበር።[13] ጥሪው አብዛኛውን የጐጃም አርበኛ ሲያስደስት አንዳንዱን ቅር ማሰኘቱ አልቀረም። ለበላይ ዘለቀ የተፃፈው ደብዳቤ ሲደርስ የሆነውን መመልከት ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል።

አባ ኮስትር ሁለት የጥሪ ደብዳቤዎች ደረሱአቸው፤ እሳቸው ግን ምላሽ ሳይሰጡ ቆዩ። መልስ ያልሰጡትም፡- «ንጉሡ ሀገራቸውን ለጠላት አስረክበው የኮበለሉ ሰው ናቸው። እሳቸው ዘንድ መሄድ የለብኝም።» የሚል ጠንካራ አቅዋም ስለነበራቸው ነው። ለሦስተኛ ጊዜ ጥሪ ሲደርሳቸው፣ ጉዳዩን ለሠራዊቱ አቀረቡት። ደብዳቤው በአደባባይ ተነበበ። ሠራዊቱም በጉዳዩ ከመከረበት በኋላ፣ ከአንድ ድምዳሜ ላይ ደረሰ። ድምዳሜውም፡- "...ለእኛ አይጠቅሙንም... የተጋደልነው ለእናት ሀገራችን እንጂ ሥልጣን ለመፈለግ አይደለም። ...ሀገራችን ከጠላት ከተላቀቀች በሰላም አርሰን እንበላለን..." የሚል ነበር። ይህ አመለካከት በሠራዊቱ መካከል የድምፅ ብልጫ ስለአገኘ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ጥሪ ተቀባይነት አገኘ።[14]

የትብብር መቀስቀሻው ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥቱ በቀጥታ ከተፃፈላቸው ሰዎች አንዱ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ለተፃፈለት፣ ራስ ኃይሉ የሰጠው መልስ ይዘቱ አልታወቀም። ነገር ግን ከአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ጥቅምት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ለተፃፈለት ደብዳቤ፣ በፀሐፊው በቀኛዝማች ተገኘ ፊርማ የሰጠው መልስ ጥሪውን መቀበሉን አያመለክትም።



አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ በሰጡት ትንታኔ "...ምልክቱን ይላኩብኝ ብዬ ለጠየቅሁዋቸው ጥያቄ በሚገባ መለሱልኝ..." ይላሉ እንጂ፤ ልዑሉ የሰጠው የእምቢታ (መልስ) ነው። አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ተቆራኝተዋቸው እንደነበር ከመጥቀስ ጋር፡- "... ከዚያ መከራ አውጥቶ ከሞት አትርፎ፤ ሀገሬን ሰጥቶ ለዚህ ላበቃኝ ለኃያሉ የጣልያን መንግሥት ምን ውለታ ልመልስለት?..." ብሎ እስከ መጠየቅ የደረሰ ነበር። በግብር የታየውም፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ከጣልያን ጐን መቆሙን ነው።

አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ለባንዳ መሪዎችም በርካታ ደብዳቤዎች ጽፈዋል። ከእነዚህም ደብዳቤዎች አብዛኞቹ ንጉሠ ነገሥቱ ከእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ አግኝተው መምጣታቸውን፣ እሳቸውም ከንጉሠ ነገሥቱ ታዝዘው ጐጃም ምድር መግባታቸውን እያበሠሩ "...ሲሆን ሥራ ሠርተህ ራስህንና ወገኖችህን መክረህ ሰዓቱ ሳያልፍ ከጠላት ተለይ። እንዳትዘነጋና በኋላ ፀፀት እንዳይሆንብህ..." የሚል ምክር ያዘሉ ነበሩ። በብዙ ወገን ተቀባይነት አገኙ። ብዙ ሰው ከጣልያን እየከዳ ወደ አርበኞች ዞረ። ለሆዱ ያደረ ነውና፣ አንዳንድ ሥራ በመሥራት በአዲሱ ሥርዓት ውስጥ ክብር ለማግኘት ተፍጨረጨረ።

ጣልያንም በበኩሉ ወሬ በመንዛቱ ረገድ ሥራ አልፈታም። የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ይረጭ ጀመር። ንጉሠ ነገሥቱ በእንግሊዝ አይሮፕላን የሚያስበትኑትን ፅሑፍ የሚመስል እያዘጋጀ በአይሮፕላን በተነ። ከሚጣለው ወረቀት አብዛኛው በእርግጥም ንጉሠ ነገሥቱን የሚያጥላላ፣ የኢጣልያንን ድል አድራጊነት የሚነግርና የእንግሊዝን መሸነፍ የሚተነብይ ቢሆንም፣ አንዳንዱ ከጣልያን ይልቅ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነበር። ለዚህ ሁኔታ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚገባው ህዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም ለሸዋ ሕዝብ የተጣለው ነው። ይህ ወረቀት በጠላት የተበተነ ነው ከማለት ይልቅ፣ ከጠላት መባረር በኋላ የንጉሠ ነገሥቱን ክብር ለመጠበቅ ሲባል የተደረገ አሠራር ነው ማለቱ ይቀላል። ዝርዝሩን ከፅሑፉ ከራሱ መመልከት ይበቃል።

ንጉሠ ነገሥቱና መልእክተኛቸው አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ለፃፉአቸው ደብዳቤዎች ማስተባበያ ጣልያን ወረቀት መበተኑን ከዚህ በላይ አይተናል። አሁን ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱና ወኪሎቻቸው፣ ጣልያን የበተነውን የሀሰት ወረቀት ለማርከስ ሌላ ወረቀት እያዘጋጁ መበተን ነበረባቸው። የጣልያን ደብደቤ ቃል በፍፁም ሀሰት መሆኑን የሚገልፅ ያዋጅ ቃል በየገበያው እንዲነገር ተደረገ። ደብዳቤውም ለአርበኞች መሪዎች በብዛት ተፃፈ። ጐጃም የሁለትዮሽ ፕሮፓጋንዳ ሜዳ ሆነች፤ ምንም ተባለ ም ግን፣ የሕዝቡ ልብ በኢትዮጵያ ነፃነት ላይ ፀና።

ሌላው ሥራ በአርበኞች መካከል የነበረውን የርስበርስ መቃቃር ማስታገስና ሀገርን ነፃ በማውጣቱ ሥራ ላይ እንዲያተኩሩ የማድረጉ ሥራ ሆነ። ይህም አሰልችና አድካሚ ነበር። አስታራቂ የመኖሩን ያህል፣ ነገር

አጋጋሚም ነበርና የሀገሬው በነገር መታመስ ቀላል አልሆነም። በልጅ በላይ ዘለቀና በልጅ ኃይሉ በለው መካከል ያለውን ቅራኔ፣ በወቅቱ እርቅም ሊፈታው አልቻለም። ከልጅ አያሌው ደስታ ጥር 18 ቀን 1933 ዓ.ም ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ የተፃፈውን መመርመር ግንዛቤ ያስጨብጣል። ከዚህ በተረፈ ግን የተደረገው ጥረት ጥሩ ውጤት ስለሰጠ የጐጃም አርበኞች የተባበረ ክንዳቸውን በጠላት ላይ አነሱ።

ጦርነቱ ተፋፋመ። ጥር 8 ቀን 1933 ዓ.ም ለጣልያን ባደረው በደጃዝማች ማሞ ኃይለሚካኤል የሚመራ 12 ሺህ የጠላት ጦር አርበኞችን ለማጥቃት በደጃዝማች ነጋሽ ላይ አደጋ ጣለ። አርበኞችም ከጥዋት እስከ ሰባት ሰዓት ወግተው ስለአባረሩት፣ ተመልሶ ቡሬ ገባ። ብቸና ከተማ የነበረው ጦር በአንድ መቶ ሃምሣ አራት ካሚዮን ተሳፍሮ ጥር 13 እና 20 ቀን 1933 ዓ.ም ደብረ ማርቆስ ገባ። ነገር ግን በወሎ ተሻግሮ ተባብሮ ለመመከት የሞከረውን የጣልያን ጦር በላይ ዘለቀ ወንድሞቻቸውን ልከው በመውጋት አቆሙት። ስለዚህ ምሥራቅ ጐጃም ላይ የነበረው የጠላት ጦር ብቻውን ቀረ።

ንጉሠ ነገሥቱ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም አሜድላ ከምትባለው የኢትዮጵያ ግዛት ገቡ። ይህም በጐጃም ሕዝብ ዘንድ በፍጥነት ታወቀ። የእንግሊዝን የበላይነት ለማጠናከር ይጣጣር በነበረው በሳንድፎርድ ምትክ ሀቀኛው ኮሎኔል/ጄነራል/ ሎርድ ዊንጌት የካቲት 8 ቀን 1933 ዓ.ም ተተካ። ለጐጃም ሕዝብም ከንጉሠ ነገሥቱ ምክር አዘል አዋጅና መመሪያ በተደጋጋሚ መጣለት። ምክሩም የጐጃም ሕዝብ በጐፍላ ጥጃ እንደምትታለብ ላም በራስ ኃይሉ እየተታለለ ከጣልያን እጅ እንደገና እንዳይወድቅ የሚያስገነዝብ ነበር። በተለይ የካቲት 12 ቀን 1933 ዓ.ም የወጣው "ፍርድና ሰላም ይገኜ ደርሻለሁ" በሚል ቃል የሚደመድም ነበር።

ከንጉሠ ነገሥቱ ተልከው፣ ፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል የካቲት 17 ቀን 1933 ዓ.ም መሸንቲ ላይ ጦርነት አድርገው፣ በዚያ የነበረውን የጠላት ግምጃ ቤት ያዙ። ከዚያም በሜጫ፣ በሠርጾ አድርገው ባህር ዳር ገቡ። ጣልያን ሠርጾ መስክ እንደሠፈረ በፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል ሠራዊት ላይ መጋቢት 1933 ዓ.ም አደጋ ጣለ። ከፍተኛ ውጊያ ተካሄደ። በዚህ ወቅት በእንግሊዞች የተተኮሰ በምባርድ በጠላት አካባቢ የእሳት ቃጠሎ ስለአስነሣ፣ ጠላት ወደ መጣበት ተመለሰ።

አርበኛው በየደረሰበት ጣልያንን ይጠዘጥዘው ጀመር። ጣልያን ደግሞ የሚያዋጣውን እያጠና እንደየአካባቢው ሁኔታ ተገቢውን አደረገ። ትናንሽ ምሽጐችን እየለቀቀ ከትላልቆቹ ገባ። ከዚያም ከዋና፣ ከዋና ከተሞች ተሰበሰበ። የአርበኛው አገር የማስለቀቅ እርምጃ በዚያው መጠን



ተፋጠነ፤ የንጉሠ ነገሥቱም አመጣጥ ተቀላጠፈ። ጠላትም በአንዳንድ ቦታ እየተከማቸ ለመከላከል ሞከረ።

በባህር ዳርና በአካባቢው የነበረው ጣልያን፣ በአለው አቅም ተናንቆ የአርበኞችን ከበባ በመስበር ጐንደር ገባ። በምሥራቅ ጐጃም አካባቢ የነበረው ተሰብስቦ ደብረ ማርቆስን ላለማስነካት ሞከረ። ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት አካሄደ። ከሱዳን የመጣው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ከእንግሊዝ ነፃ አውጭ ጦር ጋር በመሆን፣ እንደዚሁም የጐጃም አርበኛ ከያለበት በመሰባሰብ፣ በአንድነት ጉን፣ ለጉን ሆኖ ተዋጋ፤ ድልም አደረገ።[15]

በጨረቃ ጦርነት ድል መሆናቸው በዚያ አካባቢ ለነበሩ ጣልያኖች ታላቅ ጭንቅ ፈጠረባቸው። ጄነራል ናዚ ከጐንደር በአይሮፕላን ገስግሶ ደብረ ማርቆስ ገባ። ነገር ግን ሌላ ጦር ሠርቶ መመከት አልሆነለትም። ዕቅዱ ከንቱ መሆኑን ሲረዳ፣ ጦሩንና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ትቶ፣ በመጣበት አይሮፕላን ወደ ጐንደር በረረ።[16]

ስለዚህ በምሥራቅ ጐጃም የነበረው የጣልያን ጦር ለንጉሠ ነገሥቱ ቦታ መልቀቅ ግድ ሆነበት። ከመማረክ ይልቅ ሀገሩን መልቀቁን መረጠ። ራስ ኃይሉ ተክለ ኃይማኖት፣ የደብረ ማርቆስን ከተማ እንዲጠብቅ አድርጐ ጣሊያን ወደ ሸዋና ወደ ወሎ ተጓዘ። በላይ ዘለቀ ከወሎ ወደ ጐጃም ለመሻገር የከጀለውን የጣልያን ጦር ለማገድ የሞከሩትን ያህል፣ ከጐጃም ወደ ወሎ የሚሸሸውን ጦር ለማቆም አልፈለጉም። ሀገር ጥሎ መሄዱ፣ ልበላይ ዘለቀ ጉዳይ ያለበት አልመሰላቸውም። ነገር ግን ዝም ብለው መልቀቃቸው ከጥፋት ተቆጥሮ በኰሎኔል /ጄነራል/ ዊንጌት በኩል ክስ እንዲመሠረትባቸው ለማድረግ ተሞከረ። ይህም በተከታታይ ለደረሰባቸው ግጭት ከርከርሻ (የነገር መነሳሻ) ሆነ።[17]

በጐጃም ከነበረው የጣልያን ጦር አብዛኛው ወደ ሸዋ ምድር ተሻገረ። አሁን የቀረው ደብረ ማርቆስን መያዝ ሆነ። በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ውስጥ ምክር ተደረገ። ምክሩም ብዙም ሳያከራክር ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት መልዕክት እንዲላክና አሳቡ እንዲታወቅ ተቆረጠ። ወዲያው አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ተላኩ። እሳቸውም ራስ ኃይሉን አነጋግረውት "...እኔ የግርማዊነትዎ ቤት ጠባቂ ነኝና... ቤትዎን እንዲረከቡን" የሚል ቃልና አውቶሞቢሉን ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጋር አድርጎ ላከ። በደጃዝማች /ራስ ቢትወደድ/ እንዳልካቸው መሪነት አሳሽ ተልኮ የሁኔታውን አስተማማኝነት ከአጠና በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ እለቱን ገብተው በከተማይቱ አደባባይ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ተከሉ። በዚሁ ዕለት የእንግሊዝ ጦር፣ የኢትዮጵያን መናገሻ ከተማ አስለቅቆ አዲስ

አበባ መግባቱ ከምሽቱ በ3 ሰዓት በንጉሠ ነገሥቱ፣ ለመኳንንቱ ተነግሮ ታላቅ ደስታ ሆነ።[18]

የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ጦር እየገፋ ሲመጣና ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ማርቆስ ወደ መናገሻ ከተማዋ መግቢያቸው እየተቃረበ ሲሄድ፣ ፊታውራሪ ታምራት (የተባለ) ግበረ አበሮቹን ይዞ ጎንደር እና ጐጃምን እንዲያገናኝ በዓባይ ወንዝ ላይ ያሠሩትን ድልድይ ሠበረ። ሆኖም የድልድዩ አሠራር እጅ ጠንካራ ነበርና፣ ቢያስቸግረው ቅባ ኑግ እያስነጠረ፣ በላዩ እያፈሰሰ፣ ሲርስለት በዶማ አስቆፈረው፣ በመራጃ አስደበደበው። በድልድዩ መካከል ታላቅ መናወጥ ሆነና የድልድዩ ቋሚ ሠረገላ ተሠበረ፣ ድልድዩ በከፊል ፈረሰ። ሲፈርስም ታምራትና ግብረ አበሮቹ ከታች፣ የድልድዩ ፍራሽ ከላይ ሆነው እየተምዘገዘጉ ከዓባይ ወንዝ ገብተው አለቁ።[19] ሕዝብ፡- በታምራት ላይ ታምር ታየ በሚል ሁኔታውን ተረዳው።

ጠላት ከጐጃም ምድር ተባረረ፣ በሕዝብ ዘንድም ታላቅ ደስታ ሆነ። ሚያዝያ 13 ቀን 1933 ዓ.ም በደብረ ማርቆስ ከተማ ንጉሠ ነገሥቱ በተቀመጡበት አደባባይ ታላቅ ሠልፍ ተደረገ። መኳንንቱና እጨጌው፣ የእንግሊዝ የጦር መኰንኖች ቦታ ቦታ ተሰጥቶአቸው በአደባባይ ተገኝተው ነበር። የጐጃም አርበኛ በየአስተባባሪዎቹ መሪነት እየተሰለፈ፣ 5 ዓመት ሙሉ የተጋደለበትን መሣሪያውን እያነገበ፣ በሽለላ፣ በቀረርቶ፣ በፉከራ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት አለፈ። ዘግይቶ የደረሰውና ባለግርማው ሠራዊት የበላይ ዘለቀ ነበር። እሳቸው ራሳቸው ቁምጣ ሱሪ ለብሰው፣ አንገት ዝናራቸውን ታጥቀው፣ መውዜራቸውን ከትከሻቸው ላይ አድርገው ከሠራዊታቸው ማሀል ነበሩ። እንደ ሥርዓቱ ፎክረው፣ እጅ ነስተው በአደባባዩ ከነበሩት መኳንንትና የጦር አለቆች ጋር ተቀላቀሉ። ሠራዊቱ እየፎከረ፣ እያቅራራ፣ እየሸለለ አለፈ። በላይ ዘለቀ ታላቅ ግርማ የተጐናፀፉት 133 ቢዘንት መትረየስ፣ 127 አልመን መትረየስ እንዲሁም ሙሉ ትጥቅ ያለው ሠራዊት ይዘው በመግባታቸው ነበር።[20]

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፣ አንደኛ መፅሐፍ ገጽ 245።
2. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 135።
3. አበራ ጀምበሬ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 23-28 እና ገጽ 43።
4. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 8-12።
5. አበራ ጀምበሬ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 48።



6. ሞገስ ክፍሌ፣ *የምስሎኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 143-146።
7. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 388-389።
8. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 13።
9. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 345-349።
10. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ*፣ ገጽ 38-48።
11. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 360።
12. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 222-230።
13. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 252-263።
14. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 23።
15. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 322-377።
16. መኰንን እንዳልካቸው፣ *መጽሐፍ የዓለምን ምሬት ማጣፈጫ ማር ነው*፣ ገጽ 353።
17. አበራ ጀምበሬ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 189።
18. መኰንን እንዳልካቸው፣ ገጽ 353-354።
19. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 189።
20. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 23።

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት
# የወሎ ትግል

የልጅ ኢያሱ ምኒልክ ከአልጋ መውረድ ልባቸውን ከአቆሰለው አገሮች ዋናው ወሎ ነው፡፡ ከእሳቸው ወገን ቆሞ በሸዋ፣ በቶራ፣ በሰገሌ፣ በወሎም መቅደላ ተዋግቶላቸዋል፡፡ ምንም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሚስት፣ እቴጌ መነን አስፋው የልጅ ኢያሱ እህት፣ የወይዘሮ ሥኂን ሚካኤል ልጅ ቢሆኑ፣ ስሜቱ አልበረደለትም፡፡ ብዙዎቹ መኳንንቶች በእሥራት በግዞት ላይ እንደቆዩ ነበሩ፡፡

ወሎ የስሜት ችግር እንደአለ፣ የጣልያን ወረራ ደረሰ፡፡ ጣልያን ብዙ የማባባል፣ የመሸንገል ሥራ አካሄደበት፡፡ ገንዘብና መሣሪያ እየሠጠ ከእሱ ጐን እንዲቆም ጐተጐተው፡፡ የደቡብ የኢትዮጵያ ጦር፣ በላዩ ወደ ሰሜን ተጓዘበት፡፡ ድል ሆኖ ሲመለስም፣ እንደዚሁ ተጓዘበት፡፡ የጣልያን ጦር ደግሞ ደፍጥጦት በላዩ ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ ወረደበት፡፡ ብዙዎች ከጠላት ወገን ቆሙ፡፡

ምንም የልብ ቁስለት ቢኖርበት፣ ጦር ቢፈራረቅበት፣ የጠላትን አገዛዝ ወድዶ አሜን ብሎ አልተቀበለም፡፡ ጣልያንም በቦምብ ደበደበው፣ በእሳት ገሞራ ለበለበው እንጂ፣ ችግሩን አላየለትም፡፡ እንደ ወገን ቆጥሮ አልራራለትም፡፡ ከዚህ ሁሉ ችግር ጋር እየተናነቀ፣ ከጠላት ጋር ተጋድሎ ያዘ፡፡ ድርጅቱን ቀስ፣ በቀስ አጠናከረ፡፡

ጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጣልያን በተከዜ ወንዝ አካባቢ ያለውን አርበኛ ለመደምሰስ እያጉረመረመ መጣ፡፡ ከተከዜ ወንዝ ወደ ወሎ ወገን ያለውን ጠርዝ ያዘ፡፡ ከጐንደር ወገን የተንቀሳቀሰው፣ ከደጐማ ተነስቶ በበለሳ አድርጐ ሠፈረ፡፡ አርበኞች ከየአሉበት ተሰባስበው ቀጥ፣ ቀጥ እያሉ ከቆሙት የቂሊሣ ተራሮች ላይ ወጡ፡፡ የደመና ፍላጭ የሚመስል መርግ ከየአፋፉ ላይ ጠርዙን ብቅ እያደረጉ አጠመዱ፡፡ ብዙ ለመምሰል ሲመሽ በየቦታው እሳት አነደዱ፡፡ መሣሪያ ያለው መሣሪያውን ያዘ፡፡ መሣሪያ የሌለው ዱላውን፣ ጦሩን፣ ድንጋይና ወንጭፉን ይዞ ለውጊያ ተዘጋጀ፡፡ የጣልያን ጦርና አርበኛ ተፋጠጠ፡፡ ምንም ተራሮቻቸውን ጥግ ቢያደርጉ አርበኞች እጅግ ተሳቅቀው ነበር፡፡ ሁለቱም ወገን ተብረክርኮ ጦርነቱን የሚከፍት ጠፋ፡፡

በዚህ ወቅት ባላምባራስ ይግዛው አመራ የተባሉ ጀግና ተንደርድረው ከጣልያኑ ጦር ውስጥ በመግባት አንዱን ኢጣልያዊ ወታደር ያዙት፡፡ በትንቅንቁ ውስጥ አርበኛው ጣልያኑን በሽጉጥ መቱት፤ እሱም ጆሮአቸውን ነክሶ ያዘ፡፡ ሁለቱም ተያይዘው ሲወድቁ፣ ባላምባራስ በሽጉጥ በመድገም ተገላገሉት፡፡ አርበኛው በየፊናው እየፈከረ ከጠላት መካካል ገባ፡፡ መርግና ናዳም ተላቀቁ፡፡ ብዙ ከተራኮቱ በኋላ፣ ድል የአርበኛው ሆነ፡፡ አምስት ታላላቅ አርበኞች ወደቁ፤ ከጣልያን ወገን ያለቀው ግን ይበዛ ነበር፡፡ ጣልያን ከያለበት እየካከመ ወደየመጣበት ተመለሰ፡፡ ድሉም የቂሊሣ ተራሮች ድል ተባለ፡፡



በላስታ የሚንቀሳቀሰውን አርበኛ ከሚያስተባብሩት መሪዎች አንዱ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ኃይሉ ነበሩ፡፡ የራስ ካሣ ልጅ በመሆናቸው አገሩ አበረላቸው፡፡ እሳቸውም የተከዜን ወንዝ ይዘው ለብዙ ጊዜ ወዲያ ወዲህ ሳይሉ ተቀመጡ፡፡ ሁኔታቸው በግራዚያኒ የራሱን ትኩረት ስለሳበ ከነሐሴ 27 ቀን 1928 ዓ.ም( ስፕቴምበር 1 ቀን 1936 እ.ኤ.አ) ጀምሮ በእሳቸው ላይ ልዩ ክትትል እንዲደረግ የአካባቢውን ባለሥልጣኖች ይወተውት ጀመር፡፡ በዚህ ቀን በቁጥር 33 ያስተላለፈው ቴሌግራም "...ላስታ... ብርቱ እንደመሆኑ መጠን... ሰው በሙሉ ያመጠ ነው፡፡ ስለዚህ...አገሩን በሙሉ በዘዴ መደምሰስ ያስፈልጋል፡፡...ይልቁንም እንደ ዝናም በሰው ገላ ላይ የሚርከፈከፍ ጋዝ ተዘምቶ /ተመትቶ/ የተሞከረ አገር ስለሆነ ነው..." ይልና ለደጃዝማች ወንድ ወሰን ካሣ ደብዳቤ እንደፃፍላቸው፣ እሳቸው ግን እንዳልመጡ ይናገራል፡፡

መስከረም 2 ቀን 1929 ዓ.ም (ሴፕቴምበር 12 ቀን 1936 እ.ኤ.አ) ባስተላለፈው ቴሌግራም ደግሞ፣ መስከረም 1 ቀን 1929 ዓ.ም፤ በዋዜማው መሆኑ ነው፤ ብልብላ በተባለው ቦታ የጣልያን ጦር ዘምቶ ብዙ አርበኞች ከነመሳሪያቸው ተማርከው በጥይት እንደ ተደበደቡ ያስረዳና፣ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ግን ከብልብላ ደቡብ፣ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ወደሚገኘው ወደ ነአኩቶ ለአብ፣ ከዚያም ወደ ላሊበላ እንደሚያመሩ ይገልፃል፡፡ ከዚህም በስተቀር በዚሁ ቀን ለምክር ቤት፣ በቁጥር 15808 ባስተላለፈው ቴሌግራም፣ በማግስቱ ጥዋት፤ ማለትም መስከረም 3 ቀን 1929 ዓ.ም፤ በአሥመራ አይሮፕላን ማረፊያ ያሉት መጠባበቂያ አይሮፕላኖች ሁሉ የላሊበላና የብልብላን ቀበሌዎች በኤፐሪት ጋዝ እንደሚመርዙት ይገልፃል፡፡

ከብዙ ጉትጎታ በኋላ በወሎና በጐንደር የነበሩ የጣልያን ባለሥልጣኖች የግራዚያኒን ፈቃድ ለመፈፀም በደጃዝማች ወንድ በወሰን ኃይሉ ካሣ ላይ ተንቀሳቀሱ፡፡ በህዳር ወር 1929 ዓ.ም፣ ታድነው እንዲገደሉ የሚል ትዕዛዝ ከአማራ አገር ገዥ ወጣ፡፡ ከደብረ ታቦር በአንድ ኰሎኔል የሚመራ ጦር ወደ ተከዜ ዘመተ፡፡ ከበላሳ በአንድ መቶ አለቃ የሚመራ ሌላ ጦር፣ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ተከዜን ተመልክቶ ዘመተ፡፡ የሰቆጣው ገዥ ከሰሜን ወደ ደቡብ በተከዜ ማዶ ተሰለፈ፡፡ ከወሎ፣ የጣልያን ጦር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ተሰልፎ፣ የተከዜን ወንዝ ከምንጩ ጀምሮ እየመረመረ ወረደ፡፡ ጭንቅ ሆነ፡፡

የበጌምድር ሰው የደጃዝማች ወንድበወሰንን ነፍስ ለማዳን በሚችለው ሁሉ ሞከረ፡፡ ሕዝቡ ምሥጢር አመላለሰላቸው፤ መኳንንቱ የጠላትን ሹማምንት በምክር አሳሳተ፡፡ ወታደሩ የጣልያንን ክንድ አላላውስ ብሎ አጥብቆ ደበቃቸው፤ ምሥጢሩ እንዳይታወቅ አደረገላቸው፡፡ እሳቸው ወዴትም ሳይንቀሳቀሱ በተከዜ ወንዝ ውስጥ ተቀመጡ፡፡ የደብረ ታቦሩ፣ የበለሳውና የሰቆጣው የጣልያን ጦር ጥቂት ጊዜ ከአያቸውና አካባቢውን ከመረመረ በኋላ፣

ወደየቦታው ተመለሰ። ከወሎ የዘመተው ግን በየጊዜው እየተለዋወጠ አደኑን ቀጠለ።

ከጊዜ ብዛት ረሃብ ከበደ፤ ከደጃዝማች ወንድበወሰን ቃፊሮች አንዱ ምግብ ፍለጋ ወደ መንደር ሲሄድ፣ በባንዶች ተያዘ። ምሥጢሩን ለመጠበቅ የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። የዚሁ አገር ሰው ነኝ አለ። ቤቱን እንዲያሳይ ተገድዶ ራቅ ወደ አለው ቤት ቢሄድ የሌላ ሰው ቤት ሆነበት። ሕዝቡ ቢጠየቅ፣ የሚያውቀው ሰው ታጣ። እንግዳ መሆኑ ስለታወቀ ወደ ጦር አዛዥ አቀረቡት። የጦር አዛዥ የነበረው ጣልያናዊ ሻምበል በሥቃይ እንዲመረመር ቢያደርግም፣ አልተበገረም። ወደ እሱ ወደ ራሱ አስቀርቦ አባበለው። ደጃዝማች የሚገኙበትን ቦታ ቢያሳይ ከፍ ያለ ሹመት፣ ገንዘብና ሽልማት እንደሚሰጠው እያደረገ ተለማመጠው። ምሥጢሩን ካልነገረ ግን እንደማይለቀው እየገለጸ አስፈራራው። ምንም ቢሆን ሰው ነውና፣ ሰውየው ተሸነፈ፤ ምሥጢሩን አወጣ።

የጣልያን ጦር ወደ ተጠቆመው ቦታ ፈጥኖ ሄደ። ከበባ አድርጎም ተኩስ ተከፈተ። ግራዝማች መለሰ ሐማሴናይ እና አቶ ካሣ ወልደማርያም የተባሉት፣ በሁለት በር የተሰለፉት መትረየስ ተኳሾች ስለወደቁ፣ ሁለቱም በር ተከፈተ። የጨበጣ ውጊያ ተካሄደ። ደጃዝማች ወንድበወሰን መሣሪያ በመለዋወጥ እየተታኮሱ በማሕል ገቡ። የተቻላቸውን ያህል የጠላት ወታደር አራግፈው ጥይት ሲያልቅባቸው፣ ቀጥ ብለው ቆሙ። በእጅ ቦምብ ብቻ የጨበጣ ውጊያ እንዲካሄድ አዘዙ። ከውጭ ዕርዳታ ሳይደርስላቸው በመቅረቱ ሙሉ ቀን ተዋግተው ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ተማረኩ። መማረካቸው በጥሩንባ ተለፈፈ።

የጣልያን ወታደሮች ተማራኪውን ደጃዝማች ወንድበወሰን (ኃይሉ) ካሣን፣ ከኢጣሊያው ጦር አዛዥ፣ ከሻምበል ዘንሉ አቀረቡአቸው። እሱም ወንበር አስመጣና አክብሮት በሚመስል አኳኋን ከወንበሩ ላይ አስቀመጣቸው። ዕድሜአቸውን ጠይቆ፣ ወዲያው ከወንበሩ ላይ እንደአሉ ከግንባራቸው ላይ በጥይት መትቶ ገደላቸው። ከዚያው ከወደቁበት ቦታ አፈርና ድንጋይ አስለብሶአቸው በፍጥነት ወደ ጦር ሠፈሩ ሄደ። ደጃዝማች ወንድበወሰን በዚህ ዓይነት ታህሣሥ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ሞቱ።

ግን ታሪካቸው በዚህ ብቻ አላበቃም። የአስከሬናቸው ውዝግብ ቀጠለ። ፎቶግራፍ ሳያነሳቸው በመቅረቱ ቅሬታ ስለተሰማው፣ በማግስቱ ጥዋት ወደ መቃብራቸው ሄዶ ከተቀበሩበት አስወጥቶ ፎቶግራፍ አንስቶአቸው ሄደ። በዚያ አካባቢ የነበሩት ሰዎች መልሰው ቀበሩአቸው። በሦስተኛ ቀን አሽከሮቻቸው ሬሣቸውን በሌሊት አውጥተው ከቅዱስ ሃርቤ ቤተክርስቲያን፣ ከመቅደሱ አግብተው በሰማዕትነት ደረጃ ቀበሩአቸው። የጦር አዛዡ ሻምበል ለሠራው የጀግንነት ሥራ የፎቶግራፍ ማስረጃ ብቻ በቂ እንደ ማይሆን ታወቀው፤ ከአለቆቹም ዘለፋ ደረሰበት። ራሳቸውን ለመቁረጥ ከመቃብራቸው



ቢሄድ፣ አስከሬናቸው ጠፋ። ሕዝቡን አስጨንቆ ያዘ፤ ሠላሳ ሠባት ሰው ገደለ። ስምንቱ ፈታውራሪዎች ነበሩ። በዚህ ዓይነት ምሥጢሩን አግኝቶ፣ ሬሳቸውን ለሦስተኛ ጊዜ አውጥቶ፣ ራሳቸውን ቆርጦ ወሰደ፤ በድናቸውን ከሜዳ ላይ ጥሎት ሄደ። ካህናቱም፡-

*ወሥጋሆሙ ለእግብርቲክ ለአራዊተ ገይም*
*ወከአው ደሞሙ ከመማይ አውዶ*
*ወኃጥኡ ዘይቀብሮሙ፣*

በሚለው የዳዊት ምስባክ ፍትሐት አድርገው ለአራተኛ ጊዜ ተቀበሩ።

እዚህ ላይ ደጃዝማቹ ቦታ ሳይለውጡ ለምን ከአንድ ቦታ ተቀምጠው ጠላትን ጠበቁት? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል። የላስታንና የበጌምድርን አገረ ገዥነት ሳላገኝ አልገባም ብለው ለእህታቸው ወረቀት ጽፈው ነበር ይባላል። ይህ እውነት ከሆነ፣ ከጣልያኖች ጋር የውስጥ ግንኙነት ነበራቸው ማለት ነው። ትንቅንቁም ለሹመት እንጂ፣ ለሀገር ነፃነት አልነበረም ማለት ነው። ሆኖም እዚህ ላይ ከስማ በለው ግምት ያለፈ መናገር አይቻልም።

የጠላት ሀሳብ በዋግና በላስታ አካባቢ የነበሩትን አርበኞች መደምሰስ ነበር። በዚሁ ሐሳብ መሠረት ከወሎ ጦር አንቀሳቀሰ። የወሎና የበጌምድር አርበኞች ተባብረው ጥቅምት 12 ቀን 1930 ዓ.ም ወገል ጤና ወግተው፣ አሸንፈው፣ ወደ መጣበት ወደ የጁ መለሱት። አርበኛው ኃይሉን እያሰባሰበ፣ እየተጠናከረ ሄደ። በዚያ አካባቢ ብቸኛ አስተባባሪ ሆነው የቆሙት ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ነበሩ። የዋግሹም ከበደ ልጅ በመሆናቸው ሕዝብ አበረላቸው። እሳቸውም ሰቆጣን ከጣልያን አስለቅቀው ለመያዝ አሰቡ። የሰቆጣ መለቀቅ በዚያ አካባቢ ለነበረው አርበኛ ማዕከል ሆኖ ጦርነቱን ለማስፋፋት የሚረዳ ነበር። ስለዚህ በሐሳቡ ሰው ተባበረ።

ሰቆጣን የማጥቃቱ ሥራ በጥቅምት 1930 ዓ.ም ተካሄደ። አርበኛው በብርታትና በብዛት አጠቃ። የጣላትም ጦር መሸነፍ፣ እልቂት መሆኑን ስለተረዳ በአለው አቅም ሁሉ ተከላከለ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ሲካሄድ፣ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ተመትተው ሞቱ። አርበኞች አስከሬናቸውን ማዳን ሳይቻላቸው ቀርቶ፣ በጠላት እጅ ወደቀ። ጣልያንም ራሳቸውን ቆርጦ ከአገር አገር እያዞረ ጊጤ ተጫወተበት። አስከሬናቸውን በሽምግልና ዕድሜ ላይ ለነበሩት ለአባታቸው ለዋግሹም ከበደ አቀረበላቸው። ዋግሹም ከበደ የልጃቸውን አስከሬን ተረክበው "ለመሆኑ ስንታችሁን ገድሎ ሞተ?" ብለው ጠየቁ። ጠላትም ሳይግደረደር፡- "ሺህ" ብሎ መለሰላቸው።[1] የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ መሞት፣ ትግሉን አልገታውም። አሽከሮቻቸውና ባለቤታቸው ወደ ቤገምድር ተሻግረው ትግላቸውን ቀጠሉ። ልጃቸው፣ ልጅ ወሰን ኃይሉ በእግራቸው ተተኩ። እሳቸውንም ሕዝብ ተከተላቸው።

በበላይ ዘለቀ የሚመራው የጐጃም አርበኛ፣ በአንድ ወቅት ዓባይን ተሻግሮ፣ ወሎ ግዛት ልዩ ስሙ ዛሞድ ጫቀታ የነበረውን የጣልያን ጦር አጥቅቶ ነበር። በዛ የጠላትን ጦር ሠፈር በቦምብ አቃጥሎ፣ ጦሩን ደምስሶ፣ ሦስት የውሃ መትረየስ ከአንድ ሺህ ጠመንጃ ጋር ማርኮ ወደ ሠፈሩ ወደ በከና ተመልሷል።

ጥር 13 ቀን 1930 ዓ.ም ደግሞ ጓሜዳ ላይ ጦርነት ተደረገ። የጦርነቱ ዓላማ ማይንት፣ አጅበር ላይ የነበረውን የጠላት ጦር በማባረር አካባቢውን በአርበኛው ቁጥጥር ሥር ለማስገባት ነበር። በጦርነቱ በቀኛዝማች /ደጃዝማች/ መንግሥቱ ጉሹ የሚመራ አርበኛ ከበጌምድር ተሻግሮ ተካፋይ ሆኖ ነበር። ፎክሮ በመምጣት የገጠመውን የጠላት ጦር አርበኛው አሸንፎ፣ ብዙ ወታደር ፈጅቶ አባረረው። ሰባ አምስት ምንሽር ጠመንጃ ተማረከ። ከአርበኞችም ወገን ሰባት ጀግኖች ወደቁ። ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚሁ ቦታ በመነቃነቅ ግንቦት 2 ቀን 1930 ዓ.ም ሌላ አደጋ ጫቀታ በተባለው ምሽግ ላይ ጣለ። ብዙ የጠላት ወታደር ፈጅቶ፣ ሰባት መትረየስና ሦስት መቶ ጠመንጃ ከ50 ሺህ ጥይት ጋር ማርኮ፣ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ወደ ጦር ሠፈሩ ተመለሰ።[2] እነዚህ ሁለት ጦርነቶች የተሳኩት የአካባቢው የወሎ ሕዝብ ስለተባበረ መሆኑ ሊገለጽ ይገባል።

አርበኞች ላስታ፣ አብጣ የነበረውን የጠላት ምሽግ ሰብሮ ለማጥቃት ከየነበሩበት ተንቀሳቅሰው ሰኔ 8 ቀን 1930 ዓ.ም ምሽጉን አጠቁ። ጠላትም ጦሩን ከምሽጉ አስወጥቶ ከሜዳ ላይ ገጠማቸው። አርበኞች በኃይል ስለወጉት መሸሽ ግድ ሆነበት። ወደ ምሽጉ ለመግባት ሲፍገመገም አርበኞቹ ተቀላቅለው የጨበጣ ውጊያ በማካሄድ ከምሽጉ ተደባልቀው ገቡ። ከገቡም በኋላ ጠላትን አጥቅተው ወታደሩን በመፍጀትና በመማረክ ምሽጉን ያዙ። ብዙ ኢጣልያኖች ሞቱ። የተረፉትም ተማርከው፣ ከአርበኛው ጠቅላላ ጉባዔ ቀርበው፣ በፍርድ ተገደሉ። ሹምባሽ ዘለቀ የተባለው ባንዳ ግን በልዩ የርህራሄ አስተያየት ተለቀቀ። ብዙ የጦር መሣሪያ ተማረከ። አሥራ አራት አርበኞች ሞቱ፤ ሌሎች አራት ቆሰሉ።

ጣልያን በለሣን በማጥፋት እሥረኞችን የሚያስለቅቅ ጦር ባንቀሳቀሰ ጊዜ፣ በዋግና በላስታ የነበረውም ጦር እንዲረዳ ታዘዘ። በዚህ ትዕዛዝ የተንቀሳቀሰውን የጠላት ጦር የዋግ፣ የላስታና የሰቆጣ አርበኞች ከቃሊሣ እና ከቆላ መልዛ ከመጡ ወንድሞቻቸው ጋር በመተባበር፣ በሊፍላ በርና በአዘይ በር፣ በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ወግተው መለሱት። መሽጐ የተቀመጠውን የጠላት ጦር የዋግና የላስታ አርበኞች በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ወግተው ምሽጉን አስለቅቀዋል፤ ብዙ በመግደልም የጦር መሣሪያ ማርከዋል። በዚህ ጦርነት የቋሊሣ፣ የቆላ መልዛና የመና አርበኞች እንደረዱ በታሪክ ተመዝግቦአል።



ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን በመግደሉ፣ ጭንቅላታቸውን ቆርጦ ለሀገር በማሳየቱ፣ ሀገሩን አስደንግጦ ጭጭ ያሰኘለት መስሎት ነበር። ነገር ግን የልጅ ወሰን ኃይሉ በእግራቸው መተካት አሰጋው። ቀስ በቀስ የአርበኞች መጠናከርም እያየለ ሄደ። ስለዚህ ሕዝቡን ለማረጋጋት ግንቦት 13 ቀን 1931 ዓ.ም አዋጅ አወጣ። የአዋጁን ሁኔታ በቅርበት መመርመር ደግ ነው።

አዋጁ የወጣው ከጐንደር ከተማ ሲሆን፣ የአማራው አገር ማዕከል፣ አድራሻው በተለይ ለላስታና ለዋግ ሕዝብ ነበር። የተፈረመው በጄነራል ፍሩሽ የአማራ አገረ ገዥ ነበር። ቃሉም። "የኢጣልያ መንግሥት... የናንተን አገር ሕዝብ በብርቱ ከመቅጣት ደረሰ..." ይልና ያለፈውን ይተርካል። ከዚያም በማያያዝ "...ከቅጣት ያመለጡት ሰዎች ከቅጣት እንድትወጡ ያነሷሷችኋል። ...አንዳንድ መንደሮች ከተከዜ ያሉ ሊዋጉ ለተነሱት ሽፍቶች አገዙ..." እያለ የወቅቱን ሁኔታ ይዘረዝራል። ከዚያም በመቀጠል "...የኢጣልያ መንግሥት የሚገዛችሁ ሊጠቅማችሁ ነው እንጂ ሊጐዳችሁ አይደለም። ...እኔ ዕለት ዕለት የምሠራው...ሰላምና መልካም አኗኗር ለማምጣት ነው..." እያለ ይሸነግላል። ከዚያም ያ መልካም ሥራና ጥሩ ሥልት በጣልያን መሣሪያና ኃይል ተጠብቆ እንደሚኖር እያስረዳ ከፍተኛ ዛቻ ይዝታል። ነገር ግን አዋጁ የላስታና የዋግን አርበኞች አልበገራቸውም።

በአባታቸው በደጃዝማች ኃይሉ ከበደ እግር የተተኩት ልጅ ወሰን ኃይሉ እየተጠናከሩ ሄዱ። ሕዝብም አበረላቸው። ከላስታም አልፈው ከበጌምድር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ፈለጉ። ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ እንዲያገኙአቸው አደረጉ። ሁለቱም የአርበኛ አስተባባሪዎች ሠራዊታቸውን ይዘው መሽሓ ከተባለው ቦታ ላይ ነሐሴ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ተገናኙ። የሁለቱ መሪዎች መገናኘትና መመካከር በየሠራዊታቸው መካካል አዲስ ስሜት ፈጠረ። "...እንከዳም፤ ለሀገራችን ነፃነት እንሞታለን..." እያለ አንድ፣ በአንድ ከመሪዎቹ ፊት እየቀረበ መስቀል እየመታ ማለ። አርበኛው አንድ ልብ ሆነ።

ይህ ሁኔታ ጠላትን ስላሰጋው፣ በእንጭጩ ለመቅጨት ሞከረ። ብዙ ባንዳ ቆጥሮ፣ በወስከንቢት አካባቢ ያለውን ገበሬ አስከትሎ፣ ታላቅ ጦር ሠርቶ መጣ። አርበኞችም ከያሉበት ተሰብስበው መሽሐ፣ አይጠጠር ከተባለው ቦታ ነሐሴ 19 ቀን 1931 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጠሙትና ከባድ ውጊያ ተካሄደ። ፊታውራሪ ደምስ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ከ41 ግብረ አበሮቹ፣ ከነመሣሪያቸው ተማረኩ። ልጅ ወሰንም ምርኮአቸውን ይዘው ወደ ጦር ሠፈራቸው፣ ወደ ቋሊሣ ተመለሱ።

ፊታውራሪ ኃይሉ ክብረት የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ የቅርብ ወዳጅ ሲሆኑ፤ በማይጨው ጦርነት ደርሶባቸው የነበረው ቁስል እንደ ጠገገላቸው የጦር አዛዥ ለመሆን ቻሉ። ፊታውራሪ ኃይሉ እስከ ካርቱም ድረስ እየሄዱ መልዕክት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ያቀብሉ ነበር። ከዚህም በስተቀር የንጉሠ

ንገሥቱን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጠቅልለው ይዘው እንደኖሩ ይነገርላቸዋል።[3]

ሁኔታዎች በዚህ ዓይነት በመልካም ሁኔታ በመካሄድ ላይ እንደአሉ፣ መሸሐ ላይ የተደረገው ስምምነት እየላላ ሄደ። ውሎ አድሮም በልጅ ወሰን ኃይሉና በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ መካከል መቃቃር ደረሰና ግንኙታቸው ተቋረጠ። ሁለቱም እየትውልዳቸው ተመለከቱ። ደጃዝማች ነጋሽ ወደ ሀገር ነፃነት ተመለከቱ፤ ልጅ ወሰን ሥልጣንን፣ የበላይነትን ተመኙ። ለሰሜን አርበኞች የበላይ ለመሆን ከጀሉ።

ጥር 8 ቀን 1932 ዓ.ም ከልጅ ወሰን፣ ለደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ አንድ ደብዳቤ ተፃፈ። የዚህ ደብዳቤ መዘዝ ከፍተኛ ስለሆነ፣ ይዘቱን ቀረብ ብሎ መመርመር ይጠቅማል። ወረቀቱ ማዕረግ ሳይጠቅስ ይድረስ ለዳግማዊ ነጋሽ ወርቅነህ ብሎ ይጀምራል። ሰላምታ የለበትም። ከፊታውራሪ ካሣ ነአኩቶ ጋር ስለተደረገው ግጭት ማዘናቸውን ይገልጽና፣ አሉባልታ ገብቶበታል ማለት ነው፤ "…በየዳ መጥቼ ልቀመጥ ነኝና ሣቢ ላይ ቤት አሠርተው የፎጋይን አበል አስገብተው እንዲቆዩኝ" ይልና፣ የቆላው የብረት አለቅነት በፊታውራሪ ካሣ ነአኩቶ ሆኖ እየታዘዘ እንዲቆይ የሚል ነበር።

ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ይህ ወረቀት ሲደርሳቸው ጥር 10 ቀን 1932 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ መልስ ሰጡ። እሱንም በቅርበት ማየት የነገሩን ሁኔታ ለመገንዘብ ይረዳል። ደብዳቤው "ለበኩር ልጅ ወሰን" ብሎ ይጀምራል። ቢመጡ ደስ እንደሚላቸው ይገልጽና፣ ስለካሣ ነአኩቶ ሹመትና ስለ ቤቱ ሥራ የተሰማቸውን ቅሬታ ይገልፃል። የልጅ ወሰንን ሐሳብ አለመቀበላቸውን ያስረዳል። ምክንያቱንም ሲያብራራ "…እርስዎ በዋግ እኔ በስሜን ሆነን እየተረዳዳን ጠላትን ልንወጋ የተማማልነው ቀርቶ አዲስ ነገር በመፈጠሩ ነው…" ይላል።

ወዲያው ልጅ ወሰን በየዳ ተሻግረው ጥር 17 ቀን 1933 ዓ.ም ከደጃዝማች ነጋሽ ጋር ጦርነት ገጠሙ። ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ሌሊቱ ሦስት ሰዓት በብርቱ ተዋግተው ተሸነፉ። በሽማግሌ ብርታት በር ተለቆላቸው ከሞት፣ ከመቁሰልና ከምርኮ የተረፉ ሰዎቻቸውን ይዘው ሣህላ ወደ ተባለው ቦታ ሄዱ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ወደቀ። ደጃዝማች ነጋሽ አሥራ ስምንት ሰው ቢሞትባቸውም፣ ድልና ብዙ ምርኮ አገኙ።[4]

የወገንን ኃይል የሚቀንስ፣ ክብሩን የሚያጕድፍ፣ የጠላትን ልብ የሚያደነድን፣ ወገንን የሚያሳዝንና መጥፎ የሆነ ሥራ ተሠራ። በዚህ ሥራ በታሪክ ፊት ተጠያቂ የሚሆኑት ልጅ ወሰን ኃይሉ ናቸው። አወዳደቃቸውም በከፊል ከዚሁ ግጭት በመነጨ ቅሬታ፣ ጠላት ባጠቃቸው ጊዜ ከስሜን አርበኞች ዕርዳታ ባለማግኘታቸው ሳይሆን አልቀረም። በዚህ ዝብርቅርቅ ውስጥ ለሀገር የመከላከል ሥራ ቀዘቀዘ። ልጅ ወሰን ኃይሉ በሚጽፉአቸው



ደብዳቤዎች ላይ "…የአርበኞች ጦር መሪ፣ ለነፃነቱ ተከራካሪ" እያሉ ይፈርሙበት የነበረው መፈክር፣ ከዳር ሳይደርስ ቀረ።

ሁኔታዎች በእንዲህ እያለ የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት እየተሰማ ሄደ። በወሎ በኩል የሚሠራው ሥራ የሚያሳዝን መሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ ይገነዘቡ ጀመር። የደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱ ምኒልክ ወደ ወሎ ለመሻገር መከጀል ደግሞ ሌላ ችግር ስለሆነ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ህዳር 28 ቀን 1933 ዓ.ም መመሪያ ተሰጠ። መመሪያውም፦ "…ደጃዝማች መንገሻ አበያ…የተገኘውን ያህል መሣሪያ ተቀብሎ በቶሎ እንዲሄድ /ወደ ወሎ/ …ዮሐንስ ወደ ወሎ ለመሄድ አስቀድሞ ወደ እኛ መጥቶ እንዲነጋገር…" የሚል ነበር። የካቲት 12 ቀን በፃፉት በሌላ ደብዳቤ ደግሞ ወደ ጐጃም እንዲመጣ እንደፃፉለት ገልፀዋል።[5]

የወሎ አርበኛ ይህንን ድጋፍ ሲያገኝ ስለተበራታ፣ ጠላትን ከየምሽጉ እያስወጣ አባረረው። በወሎ ከነበረው የጣልያን ጦር ጥቂቱ ወደ ጐንደር ሲሻገር የበዛው ወደ ደሴ፣ ወልድያ፣ ኮረም እየተጠቃለለ ወደ ሰሜን ገሠገሠ። ከጐጃም ወደ ሸዋ ከመጣው ደግሞ አንዱ ክፍል በሰላሌና በመርሐ ቤቴ አድርጐ ደሴ በመግባት ተጠቃልሎ ጉዞውን ጀመረ።

ይህ እንደታወቀ ከምሥራቅ በሐረርጌ በኩል አዲስ አበባ ከገባው የእንግሊዝ ጦር አንዱ ክፍል አዲስ አበባ ሲጠብቅ፣ ሌላው ክፍል ወደ ሰሜን የወጣውን ጣልያንን እያባረረ ገሠገሠ። ደሴን አስለቀቀ። ከዚያም ዋናውን መንገድ ተከትሎ ወደ ትግራይ ወጣ። የወሎ አርበኛ ጠላቱን ከየተደበቀበት ጉጥ፣ ከየመሸገበት ምሽግ እያስወጣ በተንቃ፣ በደላንታ፣ በዋድላ፣ በዋይንት የነበረውን ጠላት በማባረር ጣልያንን ከማህሉ አገር ለማስወጣት በተደረገው ትግል ዋና ሚና ተጫወተ።


## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Richard Greenfield, *Ethiopia a New Political History*, p.244
2. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ከስትር*፣ ገጽ 14።
3. Greenfield, pp.185-244.
4. *ገሪማ ታፈረ*፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 158-195 እና 215።
5. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 325 እና ገጽ 372።

# ምዕራፍ ሠላሳ ሶስት
# የትግራይ ተጋድሎ

በ1928 ዓ.ም ጦርነቱ የተከፈተው ትግራይ ላይ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ የጦርነቱ የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ እሱ ሆነ፡፡ የማሐል አገሩ ጦር በግሥጋሴ ቢዘምትም ለጥቃት አልደረሰለትም፡፡ በአድዋ፣ በሐውዜን፣ በመቀሌ፣ በጕንዲ ተራራ /ዋንቲ ጉንዲ/ ብቻውን ተዋጋ፡፡ የማሐል አገር ከደረሰለትም በኋላ በተንቤን፣ በሽሬ፣ በአምባራደም፣ በዓቢይ አዲ፣ በሰለከለካ፣ በአፍጋጋ፣ በደብረ ነጋድያን፣ በዛበን ቀርከሀታና በሌሎችም ብዙ ቦታዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ቆሞ ደጋግሞ ተዋጋ፡፡ በማይጨው የጦር ሜዳም እንደዚሁ ድርሻውን ተወጣ፡፡

ጠላት ከሌሎቹ ክፍላተ ሀገር ሁሉ አስቀድሞ የገባበትና በየቦታው የተጥለቀለቀበት ሀገር ትግራይ በመሆኑ የተነሣ፣ ጦርነቱ ያደረሰበት ጉዳት ከሁሉም የከፋ ነበር፡፡ የሰዉ እልቂት ከፍተኛ ነው፤ የሀብቱ ውድመት፣ አይነገርም፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የጠላት ስብከት አንዳንዶችን አታልሎ ነበር፡፡ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ መክዳትም ልብ የሚፈትን ነበር፡፡

ቢሆንም የትግራይ ሕዝብ በቃኝ ብሎ ከትግሉ ጐራ አልወጣም፤ ጦርነቱን ቀጠለ፡፡ የትግራይ ሠራዊት ከማይጨው ሽንፈት በኋላ ወደ ማሐል አገር ከሚጓዘው የኢትዮጵያ ጦር ጋር አብሮ ተጓዘ፡፡ ቦታ መርጠን፣ ጊዜ ለውጠን ደግመን እንዋጋለን የሚለውን ሐሳብ በማመን ቆይቶ፣ ላስታ ሲደረስ መከረ፡፡ በምክሩም ሀገራችንን ጥለን ወዴት እንሄዳለን አለ፡፡ ስለዚህም ተመልሶ በሀገሩ ላይ ሆኖ ለመከራከር ወሰነ፡፡ ሠራዊቱ ራስ ሥዩምን መሪ አድርጐ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡ ሙጃ ከሚባለው ቦታ ተነስቶ በላስታ አድርጐ ፀለምት ገባ፡፡ ጣልያን በሌሎች የአርበኞች መሪዎች ባደረገው ዓይነት በራስ /ልዑል ራስ/ ሥዩም መንገሻም ላይ ተፅዕኖ አሳደረ፡፡ ከአልገቡለት ሕዝቡን እንደሚፈጅ፣ ሀገሩን እንደሚያጠፋ ዛተ፡፡ ከገቡ ግን እሳቸውን በክብር እንደሚያስተዳድራቸው፣ ሕይወታቸውንም እንደማይነካ ቃል ገባ፡፡ በአርበኛው ዘንድ ምክር ተደረገ፡፡ በምክሩ ላይ ደጃዝማች ገብረ መድህን ዘርኡ፣ ደጃዝማች ዓባይ ካሣ፣ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ገብረመድህን አንደም ከነሠራዊታቸው ተካፋይ ነበሩ፡፡

እኩሉ እንግባ ሲል፣ ከፊሉ አይደረግም አለ፡፡ ክርክሩም እየጠነከረ ሲሄድ ራስ /ልዑል ራስ/ ወደ ጣልያን መግባትን የመደገፍ አዝማሚያ አሳዩ፡፡ በዚህ የተናደዱት ደጃዝማች ዓባይ ካሣ "የዮሐንስን ዘውድ ለቅቀሖ እንደምን ለጣልያን ይገባሉ" ብለው ተቆጡ፡፡ እሳቸው ግን በበኩላቸው አርበኝነት ቀጠሉ፡፡ ደጃዝማች ገብረ መድህን ዘራኡ አርባ ዓመት የገዛሁትን አገር ለጣልያን አልለቅም በማለት ቃላቸውን ጠብቀው በአርበኝነት ከጠላት ጋር ሲከራከሩ ቆይተው፣ መርሐ ቤቴ፣ ሸዋ ሞቱ፡፡ በምክሩ ግን ሁሉም እንደፍላጐቱ እንዲያደርግ ተወስኖ በሰላም ሠራዊቱ ተለያየ፡፡



ራስ /ልዑል ራስ/ ሥዩም ለጣልያን ህዳር 7 ቀን 1929 ዓ.ም ገባ፡፡ ጣልያን በክብር ተቀብሎ ቃሉን በመጠበቅ ወደ አዲስ አበባ አመጣው፡፡ ከራስ ኃይሉ ቀጥሎ ባለምዋል አደረገው፡፡

ደጃዝማች ከበደ ካሣ፣ አቶ/ደጃዝማች/ ገብረ ሕይወት መሸሻ አርበኝነታቸውን ቀጠሉ፡፡ በየካቲት ወር 1929 ዓ.ም ራማ ላይ አደጋ ጥለው በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ፡፡[1] በአቶ /ደጃዝማች/ ገብረ ሕይወት መሸሻ የሚመራው አርበኛ ከማይጨው ጦር ሜዳ በሰሬንጋ፣ በሣምሬ፣ በአበርገሌ አድርጐ ተከዜ ወንዝ ገባ፡፡ ከዚያም የተከዜ ወንዝን ተሻግሮ ፀለምት ወደተባለው አገር ገባ፡፡ ጥቂት እረፍት ከአደረገ በኋላ፣ ድማም ጫራ ከተባለው ቦታ ትግሉን ጀመረ፡፡ ከዚያም የወረኢሉ፣ የአሰቦና የተከዜ ወንዞች ከሚገናኙበት ቦታ የጠላትን ጦር ግንባር ለግንባር ገጥሞ መልካም ውጤት አገኘ፡፡

በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ የሚመራው ጦር ከማይጨው ሽንፈት በኋላ በላስታ አድርጐ ወደጠለምት ሄደ፡፡ ከዚያም ተከዜን ተሻግሮ በተንቤን አውራጃ ወደ አበርገሎ ሄደ፡፡ መንገዱን ዘግቶ በመያዝ አላስገባም ያለውን የጠላት ጦር፣ የግራ ክንፉን በመስበር ወደ አምራ አመራ፡፡ ከዚያም ወርኤ ሸለቆ ገብቶ በየቦታው በመዘዋወር ጠላትን ማጥቃቱን ቀጠለ፡፡ በሰኔ ወር 1928 ዓ.ም በአድዋ አውራጃ ጉምቱ ከተባለው ቀበሌ በደረሰ የጠላት ጦር ላይ፣ ከየአቅጣጫው ተኩስ በመክፈት ጉዳት አደረሰ፡፡ በህዳር 12 ቀን 1929 ዓ.ም በክብረ በዓል ላይ አርበኞችን ለማጥቃት ጠላት በእንዳባገሪማ ደብርና በእንዳማርያም ሸዊቶ በኩል መጣ፡፡ አርበኛው ሁኔታውን ቀደም ብሎ በመረዳት በዓዲ ጭዋ በኩል የተኩስ ቅብብሎሽ እያደረገ፣ ከቦታ ወደ ቦታ በመፈናጠር በዓሉን ለማክበር ከመጣው ሕዝብ ነጥሎ አምባ ሰማዕታ ከተባለው ጫካማ ተረተር ጐትቶ አስገባው፡፡ ከዚያ በኋላ በተካሄደው ጦርነት ከጠላት ወገን ብዙ ሰዎች ተገደሉ፣ ሌሎች ብዙዎች ቆሰሉ፡፡ በጥር ወር 1932 ዓ.ም ደግሞ ይኸው የአርበኞች ቡድን ከአድዋ ወደ ተንቤን ሲጓዝ፣ ፍላፍል በሚባል ሸለቆ ውስጥ፤ እንዲሁም በሐምሌ ወር ደግሞ ወርኢ ድልድይ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ ጥንቃቄና ፍጥነት በተመላበት አሠራር አደጋ በመጣል በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት አደረሰ፡፡

አምባላጌ ተራራ ላይ ወጥቶ የመሸገው ጦር የሚመራው በጣልያን ምሥራቅ አፍሪካ ገዥ በዱክ ደ አዖስታ፣ እንደሁም በኤርትራና በትግራይ ገዥ በጄነራል ፍሩስኪ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ጦር የሚመራው በራስ /ልዑል/ ሥዩም ነበር፡፡ በምክትል አዛዡ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ የሚመራው አርበኛ ወደ ተራራው ለመጠጋት አደባ አምባ ሲደርስ፣ የጠላት ጦር ተኩስ ከፈተበት፤ በመድፍ እያሸጋገረ ደበደበው፡፡ በግንባር በመጋፈጥ ፈንታ ከለላ በመያዝ እስኪመሽ ጠብቆ በጭለማ ሽፋን ግንባሩን በማስፋት ወደ

አፀላ ገንዝ ገባ። ከዚያም እንዳ ቂርቆስን በተረተሩ እየተሳበ ተጠግቶ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 1933 ዓ.ም ተኩስ ከፈተ።

የአምባላጌ ጦርነት ከባድ ሆነ። ለኢጣልያኖች በ1933 ዓ.ም ይህንን ተራራ መልቀቅ በ1928 ዓ.ም የመያዙን ያህል ቀላል አልነበረም። ከማለቅ ወይም ከመማረክ በስተቀር ሌላ ሦስተኛ ምርጫ አልነበራቸውም። ስለዚህ የቻሉትን ያህል በርትተው ተዋጉ። ውጊያው እየተፋፋመ ሄደ። የእንግሊዝ ወታደር ከአዲስ አበባና ከአሥመራ ተጓጉዞ ደረሰ። ከሸዋ በእግሩ ከተጓዘው አርበኛ ከፊሉ ዱክ ደ አዎስታን እያባረረ ወደ ጐንደር ሲሻገር፣ ከፊሉ አምባላጌ ወጣ። ጦርነቱ እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1933 ዓ.ም ሳያቋርጥ ቀንና ሌሊት ተካሄደ። የኢትዮጵያ ሠራዊት በልዑል ራስ ሥዩም መሪነት በብርታት ተዋጋ። ረሃቡንና ውሃ ጥሙን፣ ብርዱን ከቁም ነገር አልቆጠረውም። ዓላማው ዱክ ደ አዎስታን መማረክና አምባለጌን መያዝ ብቻ ነበር።

ግንቦት 1 ቀን 1933 ዓ.ም በእንግሊዞችና በጣልያኖች መካከል ንግግር ተካሄደ። ድርድሩ ጣልያኖች ከነመሣሪያቸው ለእንግሊዝ እጅ ሊሰጡ ሆነ። ይህ በምሥጢር የተደረገው ስምምነት በአርበኞች ዘንድ ሲሰማ ቁጣ አስነሳ። ጦርነቱ ቀጥሎ የጣልያኑ ጄነራል ከእነተከታዮቹ ተገደለ። ጦርነቱ አልበርድ ስላለ የእንግሊዙ የጦር አዛዥ ራስ /ልዑል/ ሥዩምን ማነጋገር ግድ ሆነበት። ስለውጊያውና ስለምርኮው ከፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ ጋር እንዲነጋገር ከስምምነት ተደረገ። የኢትዮጵያ የአርበኞች አለቆችና የእንግሊዝ የጦር መኰንኖች ተነጋግረው ጣልያኖች እጃቸውን ሰጥተው ለጥበቃ ወደ እንግሊዞች እንዲተላለፉ፤ መኪናዎችንና መድፎችን እንግሊዞች እንዲረከቡ፤ መትረየስና ቀላል የጣር መሣሪያ የመሳሰለው ግን በማራኪዎች፣ በኢትዮጵያውያን እጅ እንዲሆን ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ውጊያው በዚህ ስምምነት መሠረት ቆሞ ዱክ ደ አዎስታና ጄነራል ፍሩስኪ እጃቸውን ሰጥተው የአምባላጌ ውጊያ ከፍፃሜ ደረሰ።[2] ጣልያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝዋ ዕቅድ በዚሁ ፉርሽ ሆነ።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ከጄነራል ቃለክርስቶስ አባይ የተገኘ።
2. የደጃዝማች ዓባይ ካሣ የሕይወት ታሪክ፤ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር ጽህፈት ቤት።



## ምዕራፍ ሠላሣ አራት
## የጐንደር ተጋድሎ

በወግ አጥባቂው በዳግማዊ ምኒልክ ወገንና በተራማጁ በንጉሥ ተፈሪ ተከታዮች መካከል የተቀሰቀሰው የሐሳብ ልዩነት፣ መጋቢት 22 ቀን 1929 ዓ.ም ቋና፣ አንቺም ከተባለው ቦታ አዋጋ።[1] ምንም በሥልጣን ሽሚያ የሚካሄድ የርስበርስ ጦርነት በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ የተለመደ ነገር ቢሆን፣ ይህ ጦርነት በጐንደር ሕዝብ ላይ የጣለው የስሜት ተፅዕኖ ቀላል አልነበረም። ለዚህም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩ።

ጦርነቱ የተካሄደው ከሰማይ ከአይሮፕላን በሚጣል ቦምብ፣ ከምድር በመድፍ ነበር። እጅ ለመስጠት ታስቦ የነበረው ሐሳብ በማንኛው ወገን ፊርሶ ተኩስ እንደተከፈተና ጦርነት እንደተካሄደ፣ ግልጽ አልነበረም። ራስ ጉግሣ ከሞቱ በኋላ ሬሳቸው ተቆራርጦ ነበር። ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደግሞ በሦስተኛው ቀን፣ ማለትም መጋቢት 24 ቀን 1929 ዓ.ም ሞቱ።[2] ቀድሞውንም ራስ ጉግሣ የተንቀሳቀሱት የኃይማኖት ሕጸጽ የተከሰተ መስሎአቸው ነበር። የቀድሞ ሚስታቸው እንደ መሆናቸው መጠን፣ የልዑል ራስ ተፈሪ አስገዳጅነት በተቀላቀለበት ሁኔታ የንጉሥነት ዘውድ መጫን (ባለ ሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽነት ዘውድ መጫን)፣ በራስ ጉግሣ ልቡና ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ አልቀረም።[3] ከዚህ ውጭ ለጎንደር ከጠላት የቀረበለትም ሽንገላ ቀላል አልነበረም።

ጐንደር በእነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች የተሰማውን ቅሬታ ጠጥቶ፣ ጣልያን ጉራ ሰብሮ በገባ ጊዜ የሀገር መከላከል ሥራውን ቀጠለ። የጣልያን ጦር መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጐንደር ከተማ ገባ። የማይጨው ጦርነት ማግስት ማለት ነው። የገባው አንዱ ክፍል በጄነራል እስትራችኒ መሪነት ከአሥመራ ተነስቶ፣ የመረብን ወንዝ ተሻግሮ ኡምሐጀር ከገባ በኋላ፣ በሽጺጽ በኩል ቀጥታውን መሥመር ይዞ በእግር በመጓዝ ነበር። ይህ በር በኢትዮጵያ በኩል ተከላካይ ስለአልቆመበት ያለአንዳች ችግር ሰተት ብሎ ገባ። ገብቶም ሠፈሩን ቀድሞ የጣልያን ቆንሲል ከነበረበት፣ ቸቸላ ከተባለው ቦታ አደረገ። ሌላው ክፍል ደግሞ በጄነራል ጉቤቶ መሪነት ከሽሬ ተነስቶ የተከዜን ወንዝ በመሻገር፣ በዳባት አድርጐ በዚሁ ቀን ከቀትር በኋላ በከተማይቱ ገባ። ሠፈሩን ደብረ ብርሃን አጠገብ ሐዋርያት ከተባለው ቦታ አደረገ።

ጐንደር ደነገጠ። ቀደም ብሎ በተላለፈ ትዕዛዝ መሠረት ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ያደረገው፣ ጥዋት የገባው ጄነራል እስትራችኒ ነበር። እሱም ብዙ ፎከረ፤ "...በሰማይም፣ በምድርም፣ በባህርም ያለው ሥልጣን ሁሉ ለኛ ተሰጥቶናል..." አለ። ሕዝቡ በቀጥታ ለጣልያን መንግሥት መገዛት እንደአለበት አስታወቀ። በአደባባይ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎችን ትዝብት እንኳን ከቁም ነገር ባለመቁጠር፣ ሌሎች መንግሥታት ኃያላን ነን የሚሉት እውነት አለመሆኑን አስታወቀ። ከዚያም ሀገር የመያዙን ሥራ አፋጠነ።

ከእምሐጀር ተከፍሎ ጠረፍ፣ ለጠረፍ የተጓዘው ጦር ሚያዝያ 4 ቀን መተማ፣ ሚያዝያ 21 ቀን 1928 ዓ.ም ደብረ ታቦር ገባ።

ጉንደሬ ሁሉ በየአካባቢው እየተሰበሰበ መከረ። የሚያዋጣውን ዘዴ ያፈላልግ ጀመር። በጉንዳ መረባ፣ በአርማጭሆ፣ በጠገዴ፣ በጭልጋ፣ በጫቆ፣ በመተማ፣ በሠራቆ፣ በቋየ ጋውላ፣ በአለፋ፣ በጸገዴ፣ በጸለሉ፣ በወልቃይት፣ በጠለምት፣ በወገራ፣ በጃንዋራ፣ በበለሣ፣ በከፋንዝ፣ በስሜን፣ በቦዛ፣ በቆላ ወገራ፣ በጭሀራ፣ በሰቀልት፣ በጉንደር፣ በጠደ፣ በደንብያ፣ በሚካኤል ደብር፣ በፎገራ፣ በመና መቅጣዋ፣ በቋሊሣ፣ በመልዛ፣ በእብናት፣ በፋርጣ፣ በሐሙስ ወንዝ፣ በአሞራ ገደል፣ በጥናፋ፣ በምክሬ፣ በሰዴ፣ በሙጃ፣ በአፈረዋናት፣ በአንጦ፣ በአንደቤት፣ በውደ፣ በጋይንት፣ በነገላ፣ በእስቴ፣ በወገራ፣ በከሰኔ፣ በድብ ባሕር፣ በተንከል በአዳኝ አገር፣ በሰሐሪ ያለ ጀግና የጉበዝ አለቃ እየመረጠ በበኩሉ ተንቀሳቀሰ።

ወሳኙ የመሣሪያ ጉዳይ ሆነ። ለዚህ ጉዳይ የተገኘው ዘዴ በእጅ ያለውን መሣሪያ ለጠላት አለማስገባት፣ እንደዚሁም በተገኘው ዓይነት መሣሪያ ከጠላት መንጠቅ፣ መማረክ ሆነ። ጠላት መሣሪያ አግቡ እያለ ያስተላለፈው ትዕዛዝ ሳይፈፀምለት በመቅረቱ እሱ ራሱ ሕዝቡን እያስገደደ ለመሰብሰብ ከጭልጋ ተነስቶ ወደ ጫቆ ዘመተ። አርበኞቹ ቤዛሆ ከተባለው ቦታ ገድበው ቆዩና፣ ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ጦርነት ገጠሙት። ጣልያንም መሣሪያ ከሕዝብ መሰብሰቡ ቀርቶ ከእሱ ከራሱ ጦር 15 ጠመንጃና 5 በቅሎች ተማረከበት። ይህም ለአርበኞች መልካም አጀማመር ሆነላቸው።

በመከላከሉ ሥራ ላይ የሚመቱትና የሚሞቱት የኤርትራ ልጆች፣ ሐማሴኖች ሆነው ስለተገኙ፣ በተያያዘም ግራዝማች /ራስ/ ውብነህ ጥቁር ሰው የገደለ ከገዳይ እንደማይቆጠርለት ስላወጁ፣ አቶ ብሬ ዘገየ ሣንጃ ወንዝ ላይ አንድ ኮሎኔልና ብዙ ጣልያናውያን ወታደሮች በሰኔ ወር 1928 ዓ.ም በመግደል በጉንደር የአርበኝነት ሥራ የመጀመሪያ ነጭ ገዳይ እሳቸው ሆኑ። ከዚያ በኋላ ነጭ የሚገድለው እየበዛ ሄደ።

ግንቦት 5 ቀን 1928 ዓ.ም በጉንደር ከተማ ትልቅ በዓል ተደረገ። በበዓሉ ላይ ጀነራል እስትራቺኒ ከካሚዮን ላይ ወጥቶ ቆመ፣ "ዛሬ ከዚህ የተሰበሰባችሁት ቪቶሪዮ ኢማኑኤል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውንና የኢጣልያ ነገሥታት በኢትዮጵያ ላይ ለትውልድ ትውልድ እያስተላለፉ እንዲነግሡባት ወዳችሁና አምናችሁ እንድትፈርሙ ነው" አለ። እንዲሁ እንዲደረግም አደረገ። የጉንደር ሕዝብ የጣልያንን ዓላማ በግልጽ ተረዳ።

ጉንደር የአማራ አገር ዋና ከተማ ሆነች። የአማራው አገር ወሎን፣ ጐጃምን፣ በጌምድርን እንዲያጠቃልል ተደረገ። በጉርጉራ በጀንዳ፣ በይልጊ፣ በአለፋ፣ በቋራ፣ በጉባ፣ በማጣቢያ፣ በመተማ፣ በጉደቤ፣ በጉንደዋ፣ በጭልጋ፣ በትክል ድንጋይ፣ በሣንጃ፣ ባደንቀዝ፣ በደጉማ፣ በሚካኤል ደብር፣ በይፋግ፣ በጣራ ገዳም፣ በቁልቋል በር፣ በደብረ ታቦር፣ በእስቴ፣ በሰማዳ፣ በአንቆሻ፣



በጋይንት፣ በሣቢ፣ ነገላ፣ በደብረ ሲና፣ በመቅጠዋ፣ በአጃ በፋሲለደስ፣ በእብናት፣ ኢጣልያውያን ገዥዎች፣ የጦር ባለሥልጣኖች ተመደቡ። የድልድሉ ዓላማ በተገኘው ዓይነት ዘዴ የአርበኞችን እንቅስቃሴ ከእንጭጩ ለመቅጨት ነበር።

አርበኛው፣ በጠላትን ሁኔታ ገነነ። የሀገር ውስጥ ጦርነት ከተነሣ በቀላል እንዳይለቀው አወቀ። ሕዝቡን እርስበርሱ የሚያለያይና አንድነቱን የሚበትን ስብከት ያዘ። ሰኔ 21 ቀን 1928 ዓ.ም ሻለቃ አጉሊኒ አውግሥቶ የደብረ ታቦርን ሕዝብ ሰብስቦ "...እስላሞች ኢትዮጵያ ሀገራችሁ ስትሆን በሃይማኖት ልዩነት የተነሣ ክርስቲያን ነን የሚሉት ሀበሾች የበታች አድርገው ክርስት ነቅለው ሲገዙአችሁና ሲያሰቃዩአችሁ ይኖሩ ነበር። ...ከእንግዲህ ...መከራችሁና ችግራችሁ፣ ጭንቀታችሁና ውርደታችሁ፣ ከእናንተ ተወገደ..." አላቸው።

ወደ ሁለተኛው ረድፍ ዞሮ ለድሆች እንዲህ አላቸው። "...ለመኳንንትና ለካህናት ገንዘባችሁንና ጉልበታችሁን ስትገብሩአቸው፣ ወዛችሁንና ደማችሁን ስታንጠባጥቡላቸው፣ የምትኖሩ ሕዝቦች ከዛሬ ጀምሮ መከራችሁ ተፋቀ። ...የእኩልነት መብት ይኸውና ዛሬ ወሰዳችሁ። ...ስለዚህ በቅንነት መገዛትና በታማኝነት ማገልገል ነው..." አላቸው።

ወደ መኳንንቱ ፊቱን አዞረ። ወደ አጠገባቸው ቀርቦ "...እናንተ የበጌምድር መኳንንትና ባላባቶች... የኢጣልያ መንግሥት የነበረባችሁን የተወላጅነት አኗኗር ከዛሬ ጀምሮ ሠርዞታል።... አንድ የሸዋ ሰው የበላይ ሆኖ ያዝዛችሁ ነበር። የሸዋ ሕዝብ ተገዥዎች ናችሁ እንጂ፣ እናንተ አማሮች ገዥዎች አልነበራችሁም።... ለቪቶሪዮ ኢማኑኤልና ...ለሞሶሎኒ በትክክል መገዛት ነው..." አላቸው።

ሌላው የጣልያን ሹም ደግሞ በሌላ ቀን የክርርንና የበጋ አገርን፣ የጋባን፣ የጭልጋን ቅማንቶች ሰብስቦ ከቢሮው አስገብቶ በእነሱና በጣልያኖች መካከል ተመሳሳይነት ያለው አፈታሪክ እንደ አለ ተረከላቸው። በኢጣልያ ወገን ሬሙሰና ሬሙሉሶ የተባሉትን የሮማን ከተማ የመሠረቱትን ሁለት ወንድማማቾች አጥብታ ያሳደገቻቸው ተኩላ እንደሆነችና፣ እንደዚሁም የቅማንቶችን አባት አይነርን ሰስ አጥብታ እንዳሳደገችው አስረዳቸው። ከትልቅ ዋርካ ሥር ሰስ ቁማ የተሣለበትን ትልቅ ሠሌዳ አውጥቶ አሳያቸው። አርማቸው አድርገው በየወረዳው ለሚገኘው ሕዝባቸው እንዲያሳዩት አዘዛቸው።

በየቦታው ይህንን የመሰለ፣ ሕዝብን እርስበርሱ የማለያያ ስብከት ሰበከ። በዚህ ስብከት የተታለሉት ወገኖች ጥቂት አልነበሩም። ነገር ግን ሁሉን ማታለል አልተቻለውም። ጣልያን የሚለው "ለእኔ ተገዙ" መሆኑ ግልጽ ሆነ። ቅማንቶች መክረው ቀኛዝማች ጣሹ እንግዳን አፈ ጉባዔ በማድረግ "የኢትዮጵያ መንግሥት በነበረበት ዘዜ የመንግሥቱን ሰንደቅ ዓላማ ተጠግተን